ብሩክ መኳንንት

ዲያቆን ዳንኤል ይፍሩ

ብሩክ መኳንንት ካዘጋጃቸው መጻሕፍት፡-

1. ከብሉይ ኪዳንና ከሐዲስ ኪዳን የተውጣጡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማውጫ፣ በ1986 ዓ.ም.
2. ማንቁት ቤተክርስቲያን፣ በ1987 ዓ.ም. /ስለ «ኦርቶዶክስ ተሐድሶ» አስከፊነት/ የሚገለጸው፤
3. መርኅ ለኢያሩሳሌም፣ በ1992 ዓ.ም. ናቸው።

<u>የመጽሐፉ ይዘት በከፊል</u>

- የመሲህ መምጣት
- ከስባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያን አንዱ የሆነው የምሥጢረ ተክሊልን ሥርዓት አፈጻፀሙን ጠንቅቀው ያውቃሉ?
- ሙሴ ጸሊም ማን ነው?
- የቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ሙሉ ታሪክ በአጭሩ፤
- መጽሐፍ ቅዱስን ማን ጻፈው? መቼ ተጻፈ?

በሚሉትና እንዲሁም ሌሎች ጠቃሚና አስተማሪ አርዕስቶችን ያካተተ መጻሕፍት ስለሆነ የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ወዳጆች ሁላችሁ መጽሐፉን አንብባችሁ፣ ተማሩና አስተምሩ፣ እወቁና አሳውቁ፣ ተረዱና አስረዱ፣ ትላችኋለች በመማጸን ድምጿን ከፍ አድርጋ በመጮህ ሃይማኖታችን «ኦርቶዶክስ ተዋህዶ»!

ዋጋ 8:00 ብር

ቼምበር ማተሚያ ቤት

መርሕ ለኢየሩሳሌም

መርኀ ለኢየሩሳሌም

ከ
ብሩክ መኳንንትና
ከዲያቆን ዳንኤል ይፍሩ

ሰኔ 1992 ዓ.ም
አዲስ አበባ

በድጋሚ ለማሳተም የአዘጋጆቹ መብት በሕግ
የተጠበቀ ነው፡፡



«እኔና አብ አንድ ነን»
ዮሐ. 10:30



አከፋፋይ
አቶ ሉሉ ውብአንተ

ምስጋና

የጉደለውን አሟልተው ረቂቁን በማረምና በማስተካከል ለተባበሩን ለኢቲሳ ገዳም ተክለሃይማኖት፣ ለዝቋላ ገዳም አበው መነኩሳት ላቅ ያለውን ምስጋናችንን ስናቀርብ ልዑል እግዚአብሔር ጽናቱን ይስጣችሁና መንግሥቱን ኢየሩሳሌም ሰማያዊትን ለመውረስ ያብቃችሁ አሜን!

በምክርና በሞራል፣ በሀሳብ ሲያበረታቱን ከነበሩት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተቆርቋሪ ከሆኑት ክርስቲያን ወገኖቻችን ጥቂቶቹን እነሆ

- አባ እንለብርሃን
- ሻምበል ይፍሩ ለአንተ ይደሩ
- ወ/ሮ ሰንደል አራምዴ
- ወ/ሮ እማዬ ታከለ
- ወ/ሮ ሙሉ ኃይሌ
- ወ/ር ሳሙኤል ይፍሩ
- ወ/ሮ ብርቄ ወንድሙ
- አቶ አለሙ መኰንን
- ወ/ት መሠረት አያሌው
- አቶ ወንድወሰን ካሣ
- ወ/ት አበባ መኮንን
- ወ/ር ዙፋኑ ገ/ማርያም

ለእነዚህ ስማችሁን ከላይ ለጠቀስናችሁ መካሮቻችን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ረድኤትና በረከት ይደርባችሁ፣ አይለያችሁ በማለት ምስጋናችንን እንገልጻለን።

ሙሉ በሙሉ የኮምፒዩትር ለቀማውን ረቂቁን በማስተካከል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላደረገችልን ለወ/ት ሐረገወይን ሽፈራው በቸሩ አምላካችን ስም ምስጋና እናቀርባለን።

መታሰበያነቷ

የእውቀት ባለቤት እግዚአብሔር አምላካችን ለዕዝራ ነቢይ ጥበብን ገላጭ ሀብቶ ዕውቀት በመስጠቱ የሚታወቀውን ፈጣኑንና ተራዳዩን መልአክ ቅዱስ ዑራኤልን እንደላከውና መልአኩም ለነቢዩ ዕዝራ እወቀትን ገላጭ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን እንደሰጠው ሁሉ ለእኛም ለዳካሞች ልጆቹ የዕወቀት መሠረታችን በመሆኑ፣ በዚሁ ደብር በማታው የሰርክ ትምህርት በመከታተላችን እንዲሁም በመራሄ ብርሃናት ሰንበት ት/ቤትና በሌሎች አድባራት የክትትል ኮርስ በመሰልጠን ጭምር በመታገዝ ባገኘነው አነስተኛ ዕውቀት ለዚህ ስለበቃን የመጽሐፉ መታሰቢያነቷ ለደብረ ጽጌ ቅዱስ ዑራኤል ቤተክርስቲያንና በተጨማሪም በዚሁ ደብር ለሚያገለግሉ «ለመራሄ ብርሃናት» ቅዱስ ዑራኤል ሰንበት ት/ቤት ይሁንልን፡፡

ወስበሐት ለእግዚአብሔር!

መቅድም

የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ተከታይ የሆነ ማንኛውም ክርስትያን እግዚአብሔር እንደፈቀደለት የአቅሙን ያክል መልካም ሥራ ሰርቶ ማለፍ ሃይማኖታዊ ግዴታው መሆኑ የታወቀ ነው፡፡

እነሆም አንድ ሰው ቀርቦ መመሕር ሆይ የዘለዓለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካምን ነገር ላድርግ በማለት ጠየቀው፡፡ ይህ ሰው የዘለዓለምን ሕይወት ለማግኘት መልካም ሥራ መስራት እንደሚያስፈልግ ያውቅ ነበርና፡፡ እኛም ሃይማኖት /እምነት/ አለን ካልን የግድ መልካም ስራ መስራት ይጠበቅብናል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን እምነት ብቻ ይዘው መልካም ሥራ መስራትን ከማይወዱት ከአጋንንት መሆን ነው፡፡ /ያዕ. 2:19/ ታዲያ በዚህ ጥያቄው መልስ የሰጠበት የእኛ የሁላችን ጌታ ... ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ትእዛዛትን ጠብቅ አለው፡፡ ስለዚህ የመልካም ሥራ ጥያቄው በትእዛዛቱ ላይ የሚያተኩር መሆኑን ነገረው፡፡

ከዚህ አንጻር በእግዚአብሔር ፈቃድ ይህችን መርጎ ለኢየሩሳሌም የተሰኘች መጽሐፍ ለክርስቲያን ወገኖቻችን ለንባብና ለእውቀት እንድትበቃ በድንግል ማርያም አማላጅነት አነሳስቶ ላስጀመረን አስጀምሮም ላስፈፀመን ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይድረሰው አሜን፡፡

መጽሐፉን ስናዘጋጅ መርጎ ለኢየሩሳሌም ብለን የተነሳንበት ምክንያት፡-

፩ በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም ትርጓሜ አንጻር /በምልጃዋ ተማምነው መልካም ሥራ መሥራት ለሚወዱ ሁሉ ኢየሩሳሌም ለማያዊት መርታ የምታገባ ናትና፤

፯ በውስጡ የተጻፉት የመልካም ሥራ ት/ት እኛም እንብበን ፈልጓን ከተጓዝንባት /በስራ ከተረጎምናት/ የሰማይ መንግስትን ለመውረስ እንደምንችል!

፰ ወደ ኢየሩሳሌም መመራት /ማምራት/ ማለትም ምድራዊቷ ኢየሩሳሌም ጌታችን ከልደቱ እስከ እርገቱ ድረስ የሰውን ልጅ በማዳን ቅዱስ ሥራውን የፈፀመባት ናትና:: እኛም ወደዚች ስፍራ መሄድ፣ መሳለም፣ መስገድ፣ ማየትና የጌታን መከራ መስቀል ቦታዎች መረዳት ማመን እንደዚሁም ፈለጉን ከተከተልን ወደ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት መግባት እንደምንችል!

፱ ኢየሩሳሌም /መንግስተ ሰማያት/ ለመግባት የምትመራ ስንል፣ ኢየሩሳሌም የት አለች? የት ቦታ? ለሚያሰኝ ጠያቂም የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናት የሚለው የጌታ ቃል ያስረግጥልናል በሚል ወንጌልን አምኖ በውስጡ የተነገረውን መልእክት ለፈፀመ ሁሉ መንግስተ ሰማያት በመካከላችሁ ያለች ተስፋ፣ ሰላም፣ ፍቅር፣ ደገኛይቱ ወንጌል ናት እንዳለው ያለ ነውና::

፲ አንድም መርጎ ለኢየሩሳሌም ስንል ልጅነትን /በጥምቀት/፣ ሕይወትን የምናገኝባት ከኃጢአት ታጥበን የምንድንባት በሰማያዊት ኢየሩሳሌም አምሳያ ለክርስትያኖች መሰብሰቢያ የሆነችው በምድር ያለች ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ናት:: ወደ ቅድስት ቤተክርስቲያን ት/ቷን ሰምተን ጥሪዋን አዳምጠን ተመርተን መጥተን የምትለንን እምነት ከምግባር ከሠራን /አስተባብረን ከያዝን/ ለቅዱስ ሥጋውና ለክቡር ደሙ ከበቃን ኢየሩሳሌምን ለመውረስ እንችላለንና::

መግለጫ

በዚህች መጸሕፍት ውስጥ በጐ ምግባር /እምነትን ከምግባር/ የሰሩ ከሚባሉት ቅዱሳን ጻድቃን አበው ውስጥ ታሪካቸው ብዙም የማይታወቁ የነበሩ ነገር ግን ቢታወቁና ፈለጋቸውን ልንከተላቸው ከሚገባን እነሆ እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ ለምዕመናን እንዲቀርቡ ሆነዋልና ደስ ይለናል::

እንደዚሁም እመቤታችንን ድንግል ማርያምን በአማላጅነቷ አምነን ዝም ብለን ልንቀመጥ ብቻ ሳይሆን አማልጅን እያልን እየተማፀንን መልካም ሥራን መሥራት እንዳለብን ስለእርሷም አማላጅነት በጥለቀት መማርና ማወቅ እንዳለብን ለማስጨበጥ፣ እንደዚሁም በአባ ሕርያቆስ እንደበት «መርጎ ለኢየሩሳሌም የተባለችውስ እንዴት? ለምን? ከምን አንጻር የሚሉትን መልስ ለማግኘት በመጠኑ ይዛለች::»

በመጨረሻም

ገና ብዙ መስራት እንደሚጠበቅብን ያህል ልንሰራ አልቻልምና፣ ይህችን መጽሐፍ የሚያነብና የሚይዛት ሁሉ ይህን መልካም የሆነ ጅማሮ በሰፊው ለማቅረብ እንድንችል ምዕመናን ወገኖቻችን ፀሎታችሁና ትብብራችሁ እንዳይለየን በድንግል ማርያም ስም አደራ እንላለን::

አዘጋጆቹ

ብሩክ መኳንንትና
ዲያቆን ዳንኤል ይፍሩ

ማውጫ

ገጽ

መቅድም 9

መግቢያ 15

ምዕራፍ ፩ ሃይማኖት 19

- ዶግማ 22
- ቀኖና 22
- ትውፊት 23
- የአዋልድ መጻሕፍት አስፈላጊነት 25
- አዋልድ መጻሕፍትን ማን ጻፉቸው? 27

ምዕራፍ ፪ የመሲህ መመጣት

- የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ታሪክ 29
- የኤልሳቤጥ ምስክርነት 29
- የክርስቶስ ልደት 30
- የክርስቶስ ከሕግ በታች መኖሩና እድገቱ 31
- የእመቤታችንና የጌታችን ስደት ወደ ግብፅ 31
- የክርስቶስ የሕፃንነቱ ጊዜ 32
- የክርስቶስ ጥምቀት 33
- የሐዋርያት መጠራት 34
- የመጀመሪያው ተዓምር 34
- ክርስቶስ ያስተማረው ትምህርት 34
- የጌታችን ተዓምር 35
- የኢየሱስ ክርስቶስ ማኅበራዊ ኑሮ 36
- የሐሙስ እራት 37

- የጌታችን መያዝ 37
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 38
  በመስቀል ላይ 39
- የጌታ መቃብር 40
- ትንሣዔው 41
- እርገቱ ....

ምዕራፍ ፫ ሙሴ ጸሊም ማነው?

- የአባታችን የሙሴ ጸሊም ገዳማዊ ሕይወቱ 44
- የአባ ሙሴ ጸሊም ዜና እረፍቱ 46
- ማጠቃለያ 47

ምዕራፍ ፬ መጽሐፍ ቅዱስ

- መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ቅዱስ ተባለ? 51
- ቅዱስ የሚለው ቅጽል ለምን ተቀጸለለት? 51
- መጽሐፍ ቅዳስን ማን ጻፈው? 51
- መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ተጻፈ? 52
- መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በምን ቋንቋ ተጻፈ? 54
- መጽሐፍ ቅዱስ ለምን በአንድ ጥራዝ እንዲዘጋጅ አስፈለገ? 55
- መጽሐፍ ቅዱስ በስንት ይከፈላል? 55
- መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን 58
- ትርጓሜ 61
- የመጽሐፍ ቅዱስ አመዳደብ 64
- የሁለቱ ኪዳናት ግንኙነት /አንድነት/ 65

ምዕራፍ ፮ ምሥጢረ ተክሊል
- ተክሊል ማለት ምን ማለት ነው?.. 67
- በቤተክርስቲያችን ስንት ዓይነት ሥርዓተ ተክሊል አለ? 67
- ስለ ቅዱስ ተክሊል በሕዝበ ክርስቲያኑ ዘንድ ምን አይነት ግንዛቤ አለ? በተጨማሪ የተለያዩ መጠይቆችን ያካተተ፤.............................. 68
- የቀለበቱ ምሥጢርና፣ የቀለበቱ ክብነት፣ መጐናጸፊያው የሚቀቡት ዘይት ምሳሌነቱ ምንድነው?.............. 75
- ማጠቃለያ 76

ምዕራፍ ፯ ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ማነው?
- የቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ የኢየሩሳለም ቆይታ 84
- ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ በምድረ ኢትዮጵያ 85
- የቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ የአሁኑ ቅዱስ ሥፍራ አሠራር ፍፃሜ 88
- የቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ የዚህ ዓለም ዕረፍት 90
- እግዚአብሔር አምላክ ለቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ የሰጠው ቃል ኪዳን 92

ምዕራፍ ፰ ሜሮን ምንድን ነው?.......................... 94
ምዕራፍ ፱ ቀንዲል ምንደን ነው?.......................... 97

መግቢያ

በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አንድነት እና ሦስትነት፣ በድንግል ማርያም አማላጅነት፣ በቅዱሳን መላእክት ጠባቂነት፤ ተራዳኢነት፣ በጻድቃን በሰማዕታት ፀሎት፣ በማመን መጸፍና ማንበብ እንጀምራለን አሜን::

መርጎ ለኢየሩሳሌም

መርጎ ለኢየሩሳሌም የሚለውን አርእስት ለመጽሐፉ ለመስጠት ያስቻለን በእግዚአብሔር አባታችን ቸርነት፣ ፈቃድ ሲሆን ትርጉሙንም ለመተንተን እንደሚከተለው እንመለከተዋለን - - - - -- - -

«መርጎ» - መርኃ መመሪያ ስጠ፣ መራ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ሲሆን «መሪ» ማለት ነው::

ለኢየሩሳሌም:- የሚለውን ደግሞ በቁሙ እንዳለ በመወሰድ በአማርኛው ስናስቀምጣው ለኢየሁሩሳሌም መሪ የሚል ይሆናል::

- ከርእሱ አንጻር ለመጥቀስ እንደተሞከረው ለኢየሩሳሌም መሪ ስንል በመጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱትን አንብበን ተርድተን በእምነት ሆነን በስራ ብንተረጉመው ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን እንደምንወርስ የሚያስገነዝበን ነው::

አንድም መርጎ ለኢየሩሳሌም ስንል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት አባ ህርያቆስ እንደተናገረው በቅዳሴዋ፣ በተዓምሯ፣ ማርያም ማለት መርጎ ለመንግስተ ሰማያት /መንግስተ ሰማያት መርታ የምታገባ/ ብሎ እንደተረጎመው ዓይነት ነው:: ይኸውም ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ሲባል መንግስተ ሰማያትን እንደሆነ የታመነ ነው::

አንድም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጌታችንን በማሕጸኗ ለዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በመሸከም ከተወለደ በኋላም ሴቶች ሁሉ ለአምላክ እናትነት በመሽከም ልዩ ጸጋና ሀብት የተሰጣት ስትሆን አምላክን ከሰዎች እንዲቀርበን፣ እንዲታረቀን /ምክንያተ ድኂን/ የድኅነታችን ምክንያት/ የሆነች በመሆኗ እኛም በሷ አድሮ እንደተወለደ እና እንዳዳነን አምነን ቅድስት እናቱንም ያከበርን እንደሆነ ሰማያዊት ኢየሩሳሌምን እንደምንወርስ እሙን ነው::

የንጉሥ ወንበር እንደሚከበር ለአምላክ ዙፋን የሆነች ዘለዓለማዊት ድንግልማ እንዴት መርታ ኢየሩሳሌም አታስገባ? ከተዓምሯ መጽሐፍ እንደምንረዳው «ወለዘጸወአ ስመኪ ወለዘገብረ ተዝካረኪ እምሕር ለኪ» /ስምሽን የጠራ መታሰቢያሽን፣ዝክርሽን ያዘከረውን እምርልሻለሁ/ በሚል ለጻድቃን በገባው ቃል ኪዳን መሠረት /ማቴ. 10:42/ ለቅድስት እናቱም ቃል ኪዳን ገብቶላታል:: እናም በደስታ፣ በተስፋ የጌታ ቃሉ የማይሻር፣ የማይለወጥ መሆኑን አምነን እንጠብቀዋለን::

በነቢዩ ዳዊት አንደበት ሲናገር ..... በአንቺ የሚኖሩ ሁሉ ደስ እንደሚላቸው ይነግራቸዋል እንዳለ /መዝ. 86:7/:: በእርሷ አማላጅነት አምነን ስንኖር ደስተኞች ነን:: አንድም ከመልክአ ወዳሴዋ እንደምናየው አባቶቻችን በሰዓታት ጸሎት .... ማርያም አብርሂ ነፍስ ዚአየ ዕውርተ፣___ከመ እርአይ መንገለ ጽድቅ እንተ ይመርሕ ፍኖተ እስመፍኖትኪ ያበውእ ገነተ::/ ማርያም የነፍሴን እውርነት አብሪልኝ፣ ወደ ጽድቅ የሚወስደኝን መንገድ እንዳይ፣ መንገድሽ ገነት ያስገባልና በማለት እንደሚማጸናት ግልጥ ነው::

የአምላክን እናት በመምሰል መከተል ወደ ልጅዋ እንደሚያቀርበን፣ ኢየሩሳሌምን እንደሚያወርሰን በማመን መርኅ ለኢየሩሳሌም ልንላት ችለናል::

ለምሳሌ፡ በመናገር፣ በሀሳብና በስራው የማይበድል ሰው ካለ የድንግል ማርያም በረከት ያደረበት ነው:: ግን ይህን የፈፀመ ሰው የት ተገኝቶ!

ሁለተኛም ንጽህናዋን ስናይ በነፍስም በስጋም ድንግል ተብላለች እስኪ ከሰው ወገን ይህ የተሟላለት የትኛው ሰው ነው? የአምላክን ትዕዛዝ በመፈጸምስ ምን ያህል ሰው ጽድቅን አግኝቷል ብለን ብንጠይቅ ከጥቂት ጻድቃን በስተቀር ወዬት ታይቶ!

ጌታ በሰማያዊት ኢየሩሳሌም ቅድመዓለም ሲያድርባት የነበረ ያለና የሚኖር፣ ድኅረዓለም በምድራዊቱ ኢየሩሳሌም የሰማዩን ሀገር በመሰለች በቅድስት ከተማ በድንግል ማህደር መጥቶ አደረ ለፀወር መኖሪያው አደረጋት ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰው ሆኖ ለዓለም ድኅነትን ሰጠ::

በቃና ዘገሊላም በሰርጉ በታደመ ጊዜ የወይን ጠጅ ቢያልቅ ለልጅዋ ከተማጸነችላቸው በኋላ ... ለአገልጋዮቹ የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ ስትል በገባላት የምልጃ ቃል ኪዳን መሠረት ጠይቃ መርታቸዋለች:: ልጅዋ /ኢየሱስም/ እናቱ በመራቻቸው መሠረት የድንጋይ ጋኖቹን ውሃ ሙሉአቸው አላቸው ..... ሞሉአቸውም የበለጠውን የወይን ጠጅም በተዓምራቱ አደረገላቸው:: /ዮሐ.2:5-8/

<u>ማጠቃለያ፡</u> ይህንን በመሳሰሉት ትምህርታዊ ቃል በመነሳት ነገርን ከሥሩ ውሃን ከጥሩ እንዲል ድንግል ማርያምን መርኅ ለኢየሩሳሌም በማለት አበው ማስቀመጣቸውን በመናገር በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ፍሬ የሆኑ ቃላት መልካም ፍሬን፣ ጣፋጭ ፍሬን እንድናፈራ የሚመሩን፣ የሚነግሩን፣ የሚያሳዩን በመሆናቸው መነሻው በማንበብ፣

መድረሻው በሥራ፣ በመተርጐም ከፈፀምነውና ካደረግነው ኢየሩሳሌም መርታ እንደምታስገባን ለማንኛውም ለኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት አማኞች ሁሉ ግልጽ ነው:: እንግዲህ አንብቦ መረዳትና የተረዳነውንም በተግባር /በሥራ/ መተርጐም የእኛ ፋንታ ነው::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!

ከ
ብሩክ መኳንንትና
ከዲያቆን ዳንኤል ይፍሩ

ምዕራፍ አንድ
ሃይማኖት

ሃይማኖት ወይም እምነት፣ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች በመገለጡ የተገኘ አምላካዊ ስጦታ ነው:: ሃይማኖት፣ ፈጣሪና ፍጡር የሚገናኙበት ረቂቅ መንገድ ነው:: የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር ከሁሉ ፍጥረት ሰውን አክብሮ በመልኩና በምሳሌው ፈጠረው /ዘፍ. 1:26፣ ዘፍ.2:7/

አዳምን በምድር የእግዚአብሔር እንደራሴ /ባለሥልጣን/ አድርጐ ሾመው አዳም ግን ነጻነቱን በክፉ ምኞት ለውጦ የተሰጠውን ትዕዛዝ ስለሻረ የሥጋ ሞት የነፍስ ሞት ተፈረደበት /ዘፍ.2:17፣ዘፍ.3:19/ እግዚአብሔር ግን አዳም ወዴት ነህ በማለት የማዳኑን ደወል አሰማ /ዘፍ.3:10/ እንደሚያድነው ወደቀደመ ክብሩ እንደሚመልሰው ቃል ኪዳን ገባለት /ዘፍ.3:15

ከአዳም እስከ ክርስቶስ ልደት ያለው ዘመን የብሉይ ኪዳን ዘመን ይባላል:: በዚህ ዘመን እግዚአብሔር እራሱን በራእይ፣ በሕልም፣ በተዓምራት እንዲሁም በነብያት እያደረ ለሰው ልጆች ይገለጽ ነበር:: ምንም እንኳን ሰው በተፈጥሮው እግዚአብሔርን የማወቅና የማምለክ ዝንባሌ ቢኖርውም እግዚአብሔር በቸርነቱ ባይገለጽ ኖሮ ትክክለኛውን የሃይማኖት መንገድ ለማግኘት አይችልም ነበር:: ስለዚህ የሃይማኖት ምንጩና ባለቤቱ እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ አንዳንዶች የአምላክ ስጦታ መሆኑን በመዘንጋት የሰው ልጆች ከዕውቀት ማነስ፣ ከፍርሃትና፣ ከድንጋጤ ያመጡት ነው በማለት የተሳሳተ ትምህርት ይሰጣሉ:: ይህንን የክህደት ትምህርት ቤተክርስቲያናችን አጥብቃ ትቃወመዋለች ለምሳሌ የአባታችን የአብርሃምን ሕይወት መመልከት ይበቃል:: ዘፍ. 12 በሙሉ

መሃሪው አምላክ አስቀድሞ በሰጠው ተስፋ መሠረት ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ከ30 ዘመን በኋላ በአባቴ እመኑ፣ በእኔም እመኑ ዮሐ.14:1 ብሎ በማስተማር

ሃይማኖትን ገለፀ:: ሐዋርያትም ሃይማኖት አንድ መሆንዋን በሃይማኖትም ፀንተን እንድንቆም ጽፈዋል፣ ሰብከዋል:: ኤፌሶን 4:5፣ ኤርሚያስ 6:16 ተመልከት::

ሃይማኖት እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ /325 ዓ.ም/ ድረስ አንዲት ሆና ቆየች ከዚህ በኋላ መናፍቃን በሥጋዊ አስተሳሰብ ትምህርተ ሃይማኖት አዛቡ ከእነዚህ መናፍቃን ለመከላከል እና በተሳሳተ አስተሳሰባቸው እንዳይቀይሩዋት ለማጠር አባቶች ብዙ ጥረት አድርገዋል ከአሪዎሳውያን ለመለየት በኒቅያ ጉባኤ በ325 ዓ.ም ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተብላለች::

ቃሉ የግሪክ ሲሆን ኦርቶ ማለት ቀጥተኛ ማለት ነው:: ዶክስ ማለት ሃይማኖት ማለት ነው:: በ431 ዓ.ም ደግሞ በኤፌሶን በተደረገው ጉባኤ ተዋህዶ የሚለውን ተጨማሪ ስያሜ በማግኘት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ተብላለች:: ተዋህዶ ማለት አምላክ ሰው ሆነ፣ ሰው አምላክ ሆነ /አምላክ እንደኛ ፍጹም ሰው ሆነ የኛን ሥጋ ተዋህዶ ሰው ፍጹም አምላክ ሆነ ማለት ነው::/ ዮሐ. 1:14 ፊልጵስዩስ 2:6-8፣ ሮሜ.9:5::

ሃይማኖት በጊዜና በቦታ የማይለወጥ፣ የማይሻሻል፣ በመሆኑ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ካስተማረበት ዘመን ጀምሮ የመጣችውን ጥንታዊት ሃይማኖት ይዘን ቆይተናል:: እብራውያን 13:7 የጥንት /የቀደሙት/ አባቶቻችሁን የኑሮአቸውን ፍሬ እያያችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው:: የዘመኑ ትውልድም የሃይማኖታችንን ትምህርትና ታሪክ ማወቅ አለበት::

በጥሩ ሃይማኖት ማለት የሚታየውንና፣ የማይታየውን የፈጠረ የማይታይ አምላክ አለ ብሎ ማመን ለምንኖርበት ዓለም መጋቢና፣ አስተዳዳሪ አላት ብሎ ማመን ከሞት በኋላ ሕይወት፣ ከዓለም ፍጻሜ በኋላ ዘለአለማዊ ሕይወት አለ ብሎ ማመን፣ ሃይማኖት ይባላል::

በ451 ዓ.ም ፓፓሊዮንና ተከታዮቹ በኬልቄዶን ጉባኤ እራሳቸውን ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ብለው አቋቋሙ::

በ16 መቶ ክ/ዘመን ማርቲን ሉተር ፕሮቴስታንት በሚል መጠሪያ ስም እራሱን ከካቶሊክ አገለለ::

በ17መቶ ክ/ዘመን ሄንሪስ ስምንተኛ አንግሊካንቸርች አቋቋመ በዚህ ጊዜ ጥገናዊ ለውጥ በጳስዌት ወይም እየሱሳዊያን በማደራጀት አማኞችን ላለመነጠቅ ሙከራ እያደረገች ወደአፍሪካም ጉራ አለች::

በ18ኛው መቶ ክ/ዘመን አድቬንቲስት ብቅ አለ:: በዘመናዊ ዘዴ ያዘጋጀውም አሜሪካዊው ዊሊያም ሚለር ነው::

<u>አድቬንቲስት ድርጅት በ3 ይከፈላል::</u>

1. ዘሰቨን ዴይ ክርስቲያን ቸርች፣ ቅዳሜን ብቻ ሰንበት ብለው የሚያምኑ ናቸው::
2. ዘአድቬንቲስት ክርስቲያን ቸርች፣ ቅዳሜና እሁድን በሰንበትነታቸው የሚያምኑ ናቸው::
3. ዘአድቬንቲስት ክርስቲያን አፍ ጉድ አፍ ዘአብርሃሚክ ፌዝ የሚባሉ ናቸው::

በ1870 ዓ.ም ቻርልስ ራሰል ጅሆቫዊትነስ አደራጀ::

1ጢሞ. 4:1-2፣ እብ.13:73 1ዮሐ. 4:1-3፣ ሮሜ.16:17፣ ያዕ. 1:63 የሐዋርያ ሥራ 2:13-14::

<u>ዶግማ፣ ቀኖና፣ ትውፊት</u>

ቤተክርስቲያናችን አባላቷን ወይም ምዕመናኗን የምትመራበት ሦስት የትምህርት ዘርፎች ወይም መመሪያዎች አሏት:: እነርሱም:- ዶግማ፣ ቀኖና: ትውፊት: በመባል ይታወቃል::

ሀ. <u>ዶግማ፡-</u> ዶግማ ቃሉ የግሪክ ሲሆን ትርጉሙም እምነት ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ማለትም በ80 አሀዱ መጻሕፍት የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ ዶግማ ነው። ለምሳሌ ያህል በጥቂቱ ቢጠቀስ፡ አሥርቱ ትዕዛዛት፣ ፭ቱ ቃላተ ወንጌል፣ 5ቱ አዕማደ ምስጢር ከዶግማ ይመደባሉ።

ዶግማ የእግዚአብሔር ቃል እንደመሆኑ በጊዜና በዘመን አይሻርም፣ አይለወጥም፣ መጠን አይጨመርበትም፣ አይቀነስበትም፣ አይሻሻልም፣ መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት ቅዱሳን ሰዎች የተናገሩት የጻፉት የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ ሰው እንደፍላጎቱ ሊጨምርበት ሊቀንስበት ወይም ሊያሻሽለው አይችልም።

2ኛ ጴጥ. 1:20-21፣ ዕብ.1:1-3 በማቴዎስ 24:35 ላይ ጌታችን አምላካችን መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም ብሏል።

ለ. <u>ቀኖና፡-</u> እግዚአብሔር ሁሉን በሥርዓት ያደርጋል የእጁ ፍጥረት የሆኑት መላእክትና ሰውም በሥርዓት እንዲያመልኩት ሕግና ሥርዓቱን እንዲጠበቁ ይፈልጋል። 1ኛ ቆሮ. 11:34፣ 1ቆሮ.14:40፣ 2ቆሮ.2:6-83 1ጢሞ.1:20 ቆላ. 2:5፣ 2ተሰ.3:6-7፣ የሐዋርያት ሥራ 16:4።

ቀኖና የቃሉ አመጣጥ ሸንበቆ ከሚለው ትርጉም ነው የጥንት አባቶች ሸንበቆን ለርዝመት መለኪያ ይጠቀሙበት ነበር። ልክ እደዚሁ ሁሉ የክርስቲያኖችን ሥርዓታዊ ሕይወት መለኪያ ሆኖ እንዲያገለግል የቤተክርስቲያን አባቶቻችን ሊቃውንት በጉባኤ ወይም በሲኖዶስ የሚወስኑት ውሣኔ ቀኖና ይባላል። እንደወቅቱና እንደጊዜው ሁኔታ በጉባኤ ሲለወጥ ሊሻሻል ይችላል። የማይሻሻል ቀኖናም አለ።

ለምሳሌ፡ ፀሎተ ሃይማኖት አይሻሻልም፣

ጾም ዶግማ ሲሆን የጾም ጊዜ ቀኖና ነው። በዓል ዶግማ ሲሆን ጊዜው ቀኖና ነው። ጌታ ስለጾምና

ስለበዓል ወስኗልን እንጂ የምንጾምበትንና የምናከብርበትን ዝርዝር ሥርዓት አልወሰነልንም። ስለዚህ አባቶች /አበው/ በጉባኤ ቀኖናን ሰሩልን።

ቀኖናን አንቀበልም ለሚሉት በዮሐ. 15:1-5 እኔ የሕይወት ግንድ ነኝ እናንተ ቀርንጫፍ ናችሁ ይላል። ግንድ ፍሬ የሚሰጠው በቅርንጫፍ ላይ ነው። በቅርንጫፍ የተገኘ ፍሬ የግንዱ ፍሬ አይደለም ይባላልን? ገበሬ አርሶ፣ ሰብስቦ፣ አምርቶ በጎተራ ቢከት ካልተዘጋጀ ሊበላ ይችላል? አይችልም። ማቴ.12:33-37፣ ሉቃ. 6:43-45

ሐ. <u>ትውፊት</u>፡- ትውፊት «ተወፈየ» ከሚለው የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ቅብብል፣ ርክክብ ወይም ውርስ ማለት ነው። ይህ መንፈሳዊ ሀብት ከቀደሙት አባቶች በቅብብል ለእኛ ደርሷል። ትውፊት በአበው፣ ከነቢያት፣ ከጌታ፣ ከሐዋርያት፣ ጀምሮ የተነገረና በቃል ስትውልድ ሲተላለፍ ቆይቶ በኋላ የተጻፈ ነው፣ ትውፊት መጽሐፍ ከመጻፉ በፊትም የነበረ ነው። ከቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ቀደምትነት ያለው የሄኖክ መጽሐፍ ከመጻፉ በፊት ትውፊት ነበር። ለምሳሌ አቤልና ቃየን መሳዋዕት አቅርበዋል አቤል ከአባቱ ከአዳም በአገኘው ትምህርት መልካም መስዋዕት አቀረበ መጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን አባቶቻችን በትውፊት ስላስረዱን ነው የተቀበልነው። ስለዚህ ትውፊት ቀዳሚ የሃይማኖት መመሪያ ከመሆኑም በላይ ያለትውፊት መጽሐፍ ቅዱስም ሁሉንም የእግዘአብሔርን ቃል አሟልቶ አይሰጠንም መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉንም የእግዚአብሔርን ቃል አለመያዙን በሚከተሉት ጥቅሶች ለመረዳት ይቻላል። 1ኛነገ.11:41 የቀረውም የሰሎሞን ነገር ያደረገው ሁሉ ጥበቡም እነሆ በሰሎሞን ታሪክ መጽሐፍ ተጽፏል። ማር.1:21-22 ወደቅፍርናሆም .... በትምህርቱ ተገረሙ።

ዮሐ. 21:18፣ ዮሐ. 20:30፣ ዮሐ. 21:25 ከዚህ በተረፈ ያልተገለጠው በተዓምረ ኢየሱስ ውስጥ ይገኛል።

ማር. 16:15 የተላኩት ሐዋርያት ሁሉም ሲሆኑ በሐዲስ ኪዳን መጸሕፍት ላይ የምናገኘው የአምስቱን ሐዋርያት ብቻ ነው። የሌሎቹ የሐዋርያት ትመህርት የት ደረሰ?

2ተሰሎንቄ 2:15..... በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን የተማራችሁትን ወግ ያዙ።

ፊልጵስዮስ 4:8-9 «ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን የሰማችሁትንም ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ።»

2ኛ የዮሐንስ መልዕክት ቁጥር 12
3ኛ የዮሐንስ መልዕክት ቁጥር 13-14

ሉቃ. 24:27 ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ... ተረጐመላቸው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በሰንበትነት የተጠቀሰችው ቀዳሚት ነች በራእይ 1:10 ላይ የጌታ ቀን የተባለችው የክርስቲያኖች ሰንበት /እሁድ/ መሆንዋ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተገለጠም።

ቅዱስ ጳውሎስም 1ቆሮ 16:2 ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ብሎ ከመጠቆሙ በስተቀር እሁድ ሰንበት ናት አላለም። ስለዚህ የጌታ ቀን የተባለችው እሁድ መሆንዋን በትውፊት እናውቃለን።

2ጢሞ. 3:16-17 የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ... ለጽድቅ ጠቃሚ መሆኑ ተገልጧል።

2ጢሞ. 3:8 እያኔስና እያንበሬስም ሙሴን እንደተቃወሙት ... ዘፀ.7:11-13 ሙሴ የነዚህን ስም አልጻፈም ቅዱስ ጳውሎስ በትውፊት ስላገኘው ጽፎታል።

ይሁዳ ቁ.9 የመላዕክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ግን ከዲያቢሎስ ጋር በተከራከረ ጊዜ ... ይሁዳ ከየት አመጣው ከገድለ ሙሴ በትውፊት ነው።

ማቴ. 2:23 በነቢያት ናዝራዊ ይባላል። ናዝራዊ የሚለው በየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አይገኝም ማቴዎስ ከየት አመጣው በነቢያት ናዝራዊ ይባላል ብሎ ተናገረ ቢባል ከትውፊት ያገኘውን ነው።

ሉቃ.2:25-35 ስምዖን ... የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር ለስምዖን የተገለጠው /የተብራራው/ የጌታ ቃል ምን ነበር?

የትውፊት ወይም የአዋልድ መጸሕፍት የሚባሉት ድርሳን፣ ተዓምር፣ ገድል፣ መጽሐፈ ታሪክ፣ የትርጓሜ መጸሕፍት፣ ወዘተ... ናቸው።

የአዋልድ መጽሐፍት ጥቅምና አስፈላጊነት

የአዋልድ መጸህፍት በአጠቃላይ ሰው ፍጹምና ለበጐ ስራ ሁሉ ዝግጁ እንዲሆን ይጠቅማሉ። ለምሳሌ:-

ሀ. ትርጉም:-

፩ ንባቡ ያጠረውን አስረዝመው ያስረዳሉ። 1ኛቆሮ. 1:13 በወኑ ጳውሎስ ስለእናንተ ተሰቀለን ያለውን ቅዱስ ቄርሎስ «ብዙ ነቢያትና ጻድቃን ሞቱ ሞታቸው ግን የጠቀመው የለም ክርስቶስ ግን አለምን ሁሉ አዳነ» በማለት ገለጠው።

፪ በመጽሐፍ ቅዱስ የተመሰለውን ምሳሌ ተርጉመው ያስረዳሉ ማቴ.24:32 «ምሳሌውን ከበለስ ተማሩ» ያለውን ቅዱስ ያሬድ በዜማ መጽሐፉ በለስ ያለው ቤተእስራኤልን ነው ብሎ ተርጉሞታል።

ለ. ሕግና ሥርዓት

ለምሳሌ ፍትሀ ነገሥት

ሐ. በመጽሐፍ ቅዱስ የሌለውን ያሚላሉ፣

መ. ምስጋናና ፀሎት

ለምሳሌ፡ ድጓ ጾመ ድጓ፣ አሥራአራቱ ቅዳሴ፣ መጽሐፈ ሰዓታት፣ መጽሐፈ ወዘተርፈ::

አዋልድ መጻሕፍትን ማን ጻፉቸው?

አዋልድ መጽሐፍትን የጻፉአቸው ጻድቃን፣ ሰማዕታት፣ ሊቃውንት፣ ወይም መመህራን ናቸው:: የተጻፉበት ዘመን ቤተክርስቲያን መስፋፋት ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ ነው:: የጻፉአቸውም በሚከተሉት መንገዶች ነው:: ከብሉይና ከሀዲስ ኪዳን ጥቅስ በታላቅ ጥንቃቄና መንፈሳዊ ምርምር በጾም በፀሎት በሱባኤ ጌታ ለቤተክርስቲያን በሰጠው ስልጣንና ነጻነት ነው:: ሉቃ.10:29-37

ምዕራፍ ሁለት

ዓለም በዚህ በተመሰቃቀለ ማኅበራዊ ኑሮ ሲኖሩ ከቶ ደስ ብሎት በኑሮው አምኖበት የሚኖር አልነበረም:: ብዙ ነቢያት ስለመሲህ መምጣት አስፋፍተው ተናግረው ነበር:: ይህ ትንቢት የተጠበቀው በእስራኤል ብቻ በመሆኑ የእስራኤል ተስፋ አሁንም መሲሁ መጥቶ ካለባቸው ችግር እንዲያድናቸው ከሮማውያን የባርነት ግዛት ነጻ እንዲያወጣቸው ይጠብቁ ነበር::

አረማውያን ደግሞ የሰውን ጨካኝነት፣ የክፋቱን ብዛት ከቀን ወደ ቀን እየባሰ መሄዱን አይተው ከአምላክ አንድ ምህረት ካልተሳከ በቀር በሰው ኃይል ድህነት ሲደረግ የማይችል እንደሆነ ያውቁ ነበር::

የእስራኤል ተስፋ ሙሉ ቢሆንም መሲህ እንደሚመጣ ተስፋ ቢያደርጉም የመሲህን መምጣት ይጠባበቁት የነበረ አንድ መሲህ ተነስቶ አገሯን ከባዕድ አገዛዝ ነጻ አውጥቶ የዳዊትን፣ የሰሎሞንን መንግሥት መልሶ በሰላም የሚያስተዳድር አድርገው ይጠባበቁት ነበር እንጂ አምላክ ተወልዶ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ዓለምን እንደሚያድን አያምኑም ነበር::

የሰው ወገን የሆነ ሁሉ ደክሞት፣ መኖር ሰልችቶት ሁሉም በየበኩሉ ይቆዝም ነበር:: ሀብታሙ በሃብቱ ደስታን ለመሸመት አልሆንለት ብሎ መበለታትን ወዬት ወደቃችሁ የሚላቸው አልነበረም:: በሽተኞችና፣ ረሃብተኞች ጥሪኝ ጥሬ፣ ኩባያ ውሃ የሚላቸው አጥተው በረሃብ ይተላለቁ ነበር::

ዓለም በዚህ መልክ በሚገኝበት በጭንቁ ጊዜ የዓለም መድሃኒት የሆነው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ በሥጋ ተገለጠ ማለት ሰው ሆኖ ተወለደ::

የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የሕይወት ታሪክ፣

«ብስራት»

እግዚአብሔር መንፈሱን የሚያሳርፍበት የበቃ ሰው ባልነበረበት ጊዜ በነፍስና በሥጋ ንጽህት የሆነች የእግዚአብሔርን ቃል በማኅፀኗ ለመሸከም የበቃች በናዝሬት ከተማ የምትኖር አንዲት ድንግል ነበረች:: የዚህችም ድንግል ስሟ ማርያም ነበር:: ሉቃ. 1:27

እግዚአብሔር የዓለም ድህነት ፍቃዱ ስለሆነ ለዚህ ዓለም ድህነት ምክንያት ይህችን ድንግል መረጠ:: ስለዚህም በፊቱ የሚቆመውን ባለሟሉን መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ይናገር ዘንድ ወደእርሷ ላከ:: መልአኩም ወደዚች ድንግል በደረሰ ጊዜ «ፀጋን ያገኘሽ /የተመላሽ/ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው:: አንቺም ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ» አላት:: ሉቃ. 1:28 ቅድስት ድንግል ማርያም በነገሩ ተገረመች ወንድ ሳይኖራት በድንገት ይህን የመሰለ የምስራች ስለነገራት ቅድስት ድንግል ማርያምም እውነተኛ ስለነበረች በከንቱ ውዳሴ አልተጠለፈችም፣ ስለዚህ ወዲያውኑ አልተቀበለችውም ነበርና ወንድ የማላውቅ ሲሆን ይህ እንደምን ይሆናል? ብላ ጠየቀችው፣ መልአኩም የተላከበት ነገር ነውና በብዙ አስረጅ አስረዳትና ማስረያውን ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም ሉቃ. 1:37 አላት ቅድስት ድንግል ማርያምም በእርግጥ ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለምና እነሆ የእግዚአብሔር ገረዱ አለሁኝ፣ እንደቃልህ ይሁንልኝ አለችው:: በዚህን ጊዜ አካላዊ ቃል በማኅፀኗ ተቀረፀ::

የኤልሳቤጥ ምስክርነት

ቅድስት ድንግል ማርያም የመልአኩን ብስራት የምስራች እንደሰማች ወዲያውኑ አክስቷ ኤልሳቤጥ የምስራች እንደሰማች ወዲያውኑ አክስቷ እልሳቤጥ ሉቃ. 1:39 ከአልሳቤጥም ወደምትገኝበት ወደ ይሁዳ ሄደች::

ዘንድ ደርሳ ሰላምታ እንደተሰጣጡ በኤልሳቤጥ ላይ መንፈስ ቅዱስ ሞላባትና የቅዱስ ገብርኤልን ቃል በመድገም አንቺ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ የማህፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው ብላ ብጽዕናዋን፣ ቅድስናዋን፣ የጌታ እናት መሆኗን ተናገረች:: ሉቃ. 1:41-45:: ቅድስት ድንግል ማርያምም ከሰማያውያን ከመላእክት የቅዱስ ገብርኤልን: ከምድርያውያን ከኤልሳቤጥ ከሁለት ወገን ምስክር ስላገኘች ለባለውለታው አምላክ ምስጋናን አቀረበች:: ሉቃ. 1:46-55

የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት

በሮማ አውግስጦስ ቄሳር በነገሰ በሶርያ ቄሬኔምስ ገገር በነበረበት ጊዜ በኢየሩሳሌምና በአውራጃዋም ሔሮድስ በነገሰ ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ እንዲቆጠር ቄሳር በሰጠው አዋጅ መሠረት የቅድስት ድንግል ማርያምና የቅዱስ ዮሴፍ ሃገር ይሁዳ /ቤተልሔም/ ነበርና በአዋጁ መሠረት ሊቆጠሩ እንደመጡ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቤተልሔም ተወለደ:: ሉቃ. 2:1 ለቆጠራው የመጣው ሰው በዝቶ ቦታውን ይዞት ስለነበር እመቤታችንና ዮሴፍ ማረፊያ አጥተው በአንድ በረት እንደሰፈሩ የጌታችን ልደት በዚያም በበረት ሆነ:: ሆኖም አምላክ ነውና እንደ አምላክነቱ ከእንስሳት ወገን ላምና አህያ እስትንፋሳቸውን ገበሩለት:: ሉቃ.2:1-7

የሰማይ ሠራዊት ደግሞ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰው በጎ ፈቃድ እያሉ በምስጋና ተቀበሉት:: ተቋርጦ የነበረው ስራቸው ተጀምሯል በምስጋና ተቀበሉት:: ተቋርጦ የነበረው ስራቸው ተጀምሯል

እንዲሁም የጥበብ ሰዎች ከምስራቅ ረጅም ጉዞ ተጉዘው መጥተው ሰገዱለት፣ ወርቅ ለመንግስቱ፣ እጣን ለክህነቱ፣ ከርቤም ለሞቱ፣ ምሳሌነት አድርገው ገበሩለት:: ማቴ. 2:1 መጨረሻው

ቅድስት ድንግል ማርያም ግን የሆነውን ሁሉ ታስተውል በልቧም ትጠብቀው ነበር:: ታላላቅ ተዓምራት ሲደረጉ አይታለችና ይኸውም በኀቱም ድንግልና ፀንሳ በኀቱም ድንግልና መውለድ የሰማይ ሠራዊት መጥተው ምስጋና ማቅረብ ይህ ሁሉ ተጠቃሎ ማየት ታላቅነቱን የሚገልጽ ነውና:: ሉቃ. 2:19

የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ከሕግ በታች መኖሩና እድገቱ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በ8ኛው ቀን ተገረዘ ሉቃ. 2:21 በአርባ ቀኑም ወደ ቤተመቅደስ ተወሰደ እዚያም ስምዖን አቀፈው ሃናም አየችው:: ሉቃ. 2:22-23

የእመቤታችንና የጌታችን ስደት ወደግብፅ

የምስራቅ ሰዎች ሲመጡ የአይሁድ ንጉሥ የት ነው የተወለደው? እያሉ የክርስቶስን ንጉሥነት እየመሰከሩ ስለመጡ ማቴ.21-4 ሔሮድስ ንጉሥ ከሆነማ ንጉሥ ሳይገል አይነግሥም በኔ ላይ የሚሰለጥንብኝ እንዴት ያለ ንጉሥ ተወለደብኝ በማለት ጌታን ይገድል ዘንድ አሰበ::

ስለዚህም ወደ ግብፅ እንዲሰደዱ ምክሩን የሚለግስ መልአክ ከእግዚአብሔር ታዘዘ እርሱም በሌሊት በራእይ ለዮሴፍ አሳየው ተናገረም እንዲህ ሲል «ተነሳና እናቱንና ሕጻኑን ይዘህ በሌሊት ወደ ግብጽ ሽሽ ሔሮድስ ሕጻኑን ይገድለው ዘንድ አለውና» አለው:: ዮሴፍ ቅድስት ድንግል ማርያምንና ሕጻኑን ይዞ በሌሊት ወደ ግብፅ ተሰደደ:: ማቴ.2:13-15 ሆሴ.ዕ.11:1 ከዚያም ከቦታ ወደቦታ በመዘዋወር ሶስት ዓመት ከመንፈቅ ቆየ፣ ሔሮድስም እንደሞተ ያው መልአክ ለዮሴፍ ከግብፅ እንዲመለስ አመለከተውና ሲመለስ ወደ ይሁዳ በመሄድ ፈንታ በናዝሬት እንዲቆዩ ሆነና ጌታ በዚያው አደገ:: ማቴ. 2:19-23

የኢየሱስ ክርስቶስ የሕጻንነቱ ጊዜ

ከግብፅ ስደት ከተመለሱ በኋላ ጌታችንም ቤተሰቦቹም መኖሪያቸው ናዝሬት ነበር:: ሜቴ. 2:23 ናዝሬትም የሌላ አውራጃ ከተማ ነበረች ግን እንደሌሎች አውራጃ ከተሞች ዝነኛ አልነበረችም ስለዚህ የእለት ምግቡን ያገኝ የነበረው እንጨት እየጠረበ ለቤት አገልግሎት የሚውሉ እቃዎችን እየሰራ በመሸጥ ነበር:: ጌታችንም ከዮሴፍ ጋር በመኖር ይህን ስራ እንደሰራ ይገመታል:: ሆኖም በዚህ በናዝሬት እያደገ ጥበቡን እየተሞላ በመንፈስ እየጠነከረ ይሄድ ነበር:: ምክንያቱም ጌታችን ግዕዛ ሕጻናትን አላፋለሰም እንደማንኛ ውም ሕጻን ቀስ በቀስ እያለ ነው ያደገው::

በ12 ዓመቱ ከዘመዶቹ ጋር ለበዓል እንደማንኛውም ሰው ሂዶ እንደነበር እናገኛለን:: ሉቃ. 2:41-51 ምክንያቱም እመቤታችንም ዮሴፍም በየዓመቱ እንደ አይሁድ ሥርዓት /ልማድ/ በበዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ነበርና:: ዘፀ.23:14-17 ኦሪት በዓመት ሦስት ጊዜ በአንተ ዘንድ ያለ ወንድ ሁሉ በጌታ በእግዚአብሔር ፊት ይታይ ትል ስለነበር ነው::

በዚያም በኢየሩሳሌም በሊቃውንቱ መካከል ሆኖ ሲጠይቃቸው ሲሰማቸውም ተገኝቷል:: ሉቃ.2:46-48 ይኸውም ማለት የእብራውያንን ስርዓት በመከተል የእብራውያንን ትምህርት እየተማረ እንደአደገ ያስረዳል:: አባ ህርያቆስ እንደአስረዳው «የእብራውያንን ሕግ ተማረ» ይላል:: ጌታችንም በዚህ ስለዚህ የእብራውያን ሕግ የጸና ሆነ:: በናዝሬት እየኖረ በጥበብም በቁመትም አደገ በእግዚአብሔርና ያገለግል በሰው ፊትም ሞገስን አገኘ:: ዘመዶቹንም ይታዘዝ፣ ነበር:: ሉቃ. 2:52 ከሠላሳ ዓመት እድሜው በኋላ በመምህርነት እስከ ተገለጠበት ጊዜ ድረስ ተራ ሰው መስሎ በዚያው በናዝሬት ኖረ:: በዚህም ዘመን ሁሉ ሰው የሚሰራውን ከኃጢያት በቀር ሠራ አባ ህርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ከኃጢያት ብቻ በቀር የሰውን ሕግ ሁሉ ፈፀመ እንዳለ!

የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት

ክርስቶስ እንደተጠመቀ ወዲያውኑ ከዲያቢሎስ ይፈተን ዘንድ ወደ ምድረበዳ ሄደ በዚያም አርባ መዓልት አርባ ሌሊት ጾመ ከዚህ በኋላ ተራበ ፈታኙ ሰይጣንም እንደተራበ ባየ ጊዜ አዳምን በመብል እንደአሳትኩ ክርስቶስንም በምግብ አስታለሁ ብሎ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንክ እነዚህን ድንጋዮች እዘዝ ሕብስት እንዲሆኑ አለው ክርስቶስ ግን ለፈቃዱ አልታዘዘለትም እንዲያውም «ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ከእግዚአብሔር በሚወጣው ቃልም ነው እንጂ» ሲል መለሰለት:: ማቴ. 4:4፣ ዘፀ. 8:3

ሁለተኛው ፈተና «ወደ ቤተመቅደስ ወስዶ ከጫፉ ላይ አውጥቶ ከዚህም ዘለህ ውረድ ስለአንተ መልእክቱን ያዛቸዋል በገዳናው ሁሉ እንዲጠብቁህ እግርህም በእንቅፋት እንዳትሰናከል የሚል ጽሑፍ አለና አለው::»

ጌታችንም መልሶ «ፈጣሪህን እግዚአብሔርን አትፈታተነው» የሚለውን መለሰለት ማንኛውንም የማይገባውን እየሰራ እግዚአብሔር ይህን ያደርግብኛል የሚለው ሁሉ የማይረባ መሆኑን ጠቅሶ አስረዳው:: ማቴ. 4:5-7፣ መዝ. 90:11-12::

ለሦስተኛ ጊዜ እንደገና ከረጅም ተራራ አወጣውና የዓለምን መንግሥታት ክብራቸውን አሳይቶ ለኔ ብትታዘዝ፣ ብትሰግድልኝም፣ ብታመለከኝም ይህን ሁሉ ለአንተ አሰጥሀለሁ ብሎ በሚያስጎመጅ አገላለጥ ገለጠለት:: ጌታችን ግን ከክብሩ ዙፋን የወረደው፣ ወደዚህ ዓለም የመጣው፣ ለሰው ደህንነት እንጂ ለራሱ ክብር አይደለምና:: ሰይጣን ባለጋራዬ ወግድ ከኋላዬ ሲል ለአምላክ የአምልኮት ስግደት መስገድ አምላክን በቻ ማምለክ እንደሚገባ አስረድቶ ድል ነስቶታል:: ማቴ 4:8-11 በዚህን ጊዜ ግን እንደ ድል አድራጊነቱ ምስጋና ለማቅረብ፣ ለማገልገል መላእክቱ መጡለት:: ማቴ 4-11

የሐዋርያት መጠራት

ክርስቶስ ጾሙን ከፈጸመ በኋላ ደቀመዛሙርቱን መሰብሰብ ጀመረ:: ገሚሱን ከዓሣ አጥማጅነት ማቴ.4:18-22፣ ማር.1:20፣ ሉቃ.5:2-11 እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ፣ ቅዱስ እንድርያስ፣ ቅዱስ ያዕቆብ: ወልደዘብድዮስና ወንድሙ ቅዱስ ዮሐንስ ሌላውም እንዲሁ ከመቅረጫው ቅዱስ ማቴዎስን ማቴ 9:9፣ ማር.2:14፣ ሉቃ.5:27 ቅዱስ ያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ እንዲሁ በመንገድ እንዳለ የክርስቶስ ጥሪ ደረሰውና ለመከተል ፈቃደኛ ሆኖ ዓለምን እየተሰናበት ተከተለው:: ዮሐ. 1:34-52 ይህ ሁሉ የተፈፀመው ከጾሙ በኋላ ባሉት ቀናት ባደረገው ትምህርት ነው:: ማር. 3:13-19፣ ሉቃ. 6:14-16

የመጀመሪያው ተዓምር

በሦስተኛው ቀን በገሊላ ቃና ሠርግ ተደረገና ጌታችን በዚያ የመጀመሪያውን ተዓምር አደረገ:: በሠርጉ ላይ እናቱ እመቤታችን፣ 12ቱም ሐዋርያት ተገኝተዋል:: በግብዣውም የወይን ጠጅ ባለቀባቸውም ጊዜ በእመቤታችን አማላጅነት፣ አማካኝነት ዘመዷ «ዶኪማስን» ልጅዋን ለምና ከውርደት፣ ከሸሙጥ አድናቸዋለች:: ዮሐ. 2:1-12

ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ትምህርት

፩ አንቀጸ ብፁዓን

የተራራው ስብከት በመባል የሚታወቀውን እንደ ቤተክርስቲያናችን ስያሜ ግን አንቀጸ ብፁአን እየተባለ የሚጠራውን እንደ መጀመሪያው አዋጅ አድርጐ «ብፁዓን ብፁዓን» እያለ እውነተኛውን የክርስቲያን ትምህርት በዚህ መልክ አስተማረ:: ማቴ.5:1-12 ይህ ትምህርት ፍጹም ልዩ የሆነ የፍጹምነት ትምህርት ነው የክርስትናውም እምነት ፍጹም ነውና አንድ የመንግሥ... ሠሪ መንግሥት እንደያዘ የሚያውጀው የመንግሥቱን ዓላማ ነው:: ክርስቶስም

በመጀመሪያ የክርስትናውን አላማ ይህንና ይህን ሠርቶ የፈፀመ ብፁዕ ነው በማለት እውነተኛውን ክርስቲያናዊ ትምህርት አስተማረ:: ምንም በተለያዩ ቦታዎች ብፁዓን ቢጠሩም በዚህ በተራራው ትምህርት ጊዜ ተብለው የተገለጡት እንደቅዱስ ማቴዎስ አገላለጥ 9 /ዘጠኝ/ ናቸው::

፪ ትምህርት በምሳሌ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር እንዲሁ ቢገባው ይግባው ካልገባውም ይቅር በማለት አልነበረም ነገር ግን ሁሉም በሚገባው በምሳሌ ያስተምር ነበር:: ለምሳሌ ለገበሬዎች በእርሻና በዘር እየመሰለ አስተምሯል:: ማቴ. 13:3-50፣ ማር. 13:33:: ለነጋዴዎች በመክሊትና በልዩ ልዩ ሚዛን እየመሰለ አስተምሯል:: ማቴ. 25:14-30 ለመምህራን፣ ለካህናት በልዩ ልዩ ምሳሌ እየመሰለ አስተምሯል:: መንግሥተ ሰማያትን በልዩ ልዩ ምሳሌዎች እየመሰለ አስተምሯል:: እንዲያውም ያለ ምሳሌ አላስተማረም፣ አልተናገረም ማቴ. 13:35 እንግዲህ ወደዚህ ዓለም የመጣበት ዓላማ ለማስተማር ስለሆነ ሁሉንም በሚገባው መልክ አስተምሯል::

የጌታችንና የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተዓምራት

ድውያነ ነፍስን በትምህርት እየፈወሰ ድውያነ ሥጋን በተዓምራት ይፈውስ ነበር:: ከተዓምራቱም በጥቂቱ ሕብስት አበርክቶ ማብላትን ማቴ.15:32-38፣ የ38 ዓመት መጻጉዕን መፈወስ ዮሐ.5:5-10፣ እውራንን መፈወስ ዮሐ. 9፣ ሙት ማንሳት ዮሐ. 11:1-34 በአጠቃላይ ብዙ ገቢረ ተዓምራትን ፈጽሟል:: ግን ድውይ በመፈወሱ ተዓምራትን ሁሉ በማድረጉ ሰንበትን ሻረ ተብሎ ተከሷል ሰይጣንን በሰይጣን አለቃ ያወጣል ተብሎ ተከሷል::

የጌታችንና መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማኅበራዊ ኑሮ

መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው የሆነው ሰውን መስሎ ሰው በሄደበት ሄዶ ለማስተማር ነው:: በሰዎች ማኅበራዊ ኑሮም እየገባ የደስታቸውም፣ የኃዘናቸውም ተከፋይ ሆኗል:: በመጀመሪያ ጊዜ በገሊላ ቃና ተዓምራቱን ያደረገው በሠርግ ቤት መገኘቱ የሰዎችም የደስታ ተከፋይ ከመሆኑ የተነሳ ነው:: ዮሐ. 2:1-12::

ከቅዱስ ማቴዎስ ቤት ጀምሮ በነዓልአዛር፣ በእነሰምዖን ዘለምፅ ቤት ግብዣ እየተጋበዘ ገብቷል:: በእነዚህም ቤቶች ቋሚ የሆኑ ትምህርቶችን ሰጥቷል:: ማቴ. 9:11፣ ሉቃ. 10:38-42

በቤተመቅድስ ተገኝቶ የፀሎቱ ተካፋይ ለመሆን ከ12 ዓመት እድሜው ጀምሮ ፈጽሟል:: ሲቃ. 2:42-50 እኔ አምላክ ነኝና እኔ ያለሁበት ነው ቤተመቅድስ አላለም:: ይህም ሰው እምነቱን፣ ሥርዓቱን አክብሮ በማኅበር ፀሎት በተወሰነ ቦታ መገኘት ግዴታ መሆኑን ያስረዳል::

በኃዘን ቤት ተገኝቶ ተንሰቅስቆ አልቅሷል፣ ይኸውም በአልዓዛር ቤት ነው:: በዚያም ከመገኘቱ የተነሳ አልዓዛርን ከሞት አስነስቷል:: ዮሐ.11:11-34 በዚህም መልክ እንደማንኛውም ሰው ሆኖ ከኃጢአት በቀር የሰውን ችግር እየተካፈለ እግረ መንገዱን ግን እያስተማረ ኖረ ሲያስተምርም ውሎ የሚያድርበት ቤት፣ የሚያርፍበት ክፍል ከቶ አልነበረውም ቀን በምኩራብ በአዳራሹ ሁሉ ሲያስተምር ይውላል፣ ሌሊት ግን ወደ ደብረ ዘይት እየመጣ ያድር ነበር:: ሉቃ. 21:37 ምግብ የሚያዘጋጅለት አልነበረም፣ ደከመህ እረፍ የሚለው ዘመድ አልነበረውም፣ ሲያስተምር ውሎ ልጆች የሚበላ አለን? እያለ ይጠይቅ ነበር:: ማቴ. 15:32-38

የሐሙስ እራት

ጌታችን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፍስሀን /የፋሲካን/ በዓል በማክበር ሲበላ ሕብስቱን አንስቶ ባረከ ፈተተና ለደቀመዛሙርቱም እንኩ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው ነገ በመልእልተ መስቀል የሚቆረሰው ብሎ ሰጣቸው፣ ጽዋውንም አንስቶ እንዲሁ ባረከ እንኩ ሁላችሁ ጠጡ ይህ ነው የሐዲስ ኪዳን ደሜ ለዓለም ኃጢአት ማስተሰሪያ ሆኖ ነገ የሚፈሰው ሲል ሰጣቸው:: ማቴ. 26:26-29፣ ማር. 14:22-24

በዚህ ጊዜ ሥርዓተ ቁርባንን አሳያቸው ምሥጢረ ቁርባንን መሰረተላቸው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በክርስቶስ የሚያምን ሁሉ ከርሱ ጋር ግንኙነት ሳያቋርጥ 1ቆሮ.11:26 ይኖር ዘንድ ሥጋውን መብላት ደሙን መጠጣት አስፈላጊ መሆኑን አስረዳ ከዚህ በኋላ ደቀመዘሙርቱን ይዞ ለፀሎት ወደ ጌቴ ሴማኒ ሔደ:: ማቴ. 26:36-46

የጌታችን መያዝ

ጌታችን በጌቴ ሴማኒ ሆኖ ሲፀልይ ከደቀመዛሙርቱ አንዱ የነበረ ይሁዳ ወደካህናቱ አለቃ ሄዶ ነገር ሠራ ያሲዘውም ዘንድ 30 ብር ተቀብሎ የጭፍሮቹ መሪ ሆኖ ድንገት ደረሰ:: ጥፍሮቹ ክርስቶስን አይተው አያውቁትም ጊዜውም ጨለማ ነበርና እኔ ሄጄ የምስመው እርሱ ክርስቶስ ነው ተባብራችሁ ያዙት ብሎ ምልክት ሰጥቷቸው ነበርና ይሁዳ ሂዶ መመህር ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን ሲል እጅ ነሳው:: በዚህ ጊዜ ተረባርበው ያዙት:: ክርስቶስ ግን ይሁዳ በመሳም ልታሲዘኝ መጣህን? ሲል የሰላም ቃል ተናግሮ እጁን ሰጠ እንጂ አልያዝም ብሎ አልታገለም:: ወዲያውም ጭፍሮቹ እያዳፉ፣ እያጋፉ ወደ ሊቀካህናቱ ወደ ቀያፋ ወሰዱት:: ማቴ. 26:47-57 ደቀመዛሙርቱ ግን ለራሳቸው ፈርተው ተበተኑ ቅዱስ ጴጥሮስና ቅዱስ ዮሐንስ ብቻ የሚሆነውን ሁኔታ ሁሉ ለማየት በኋላ በኋላ እየተከተሉ እስከ ሊቀካህናቱ ግቢ አብረውት ሄዱ ቅዱስ ዮሐንስ ግን

እስከመጨረሻውም ቢሆን አልተለየውም:: ስለዚህ በመስቀሉም ጊዜ በአንጻሩም ሆኖ ሲያለቅስ ውሎአል:: ማቴ. 26:58፣ ዮሐ. 19:26

ሊቀካህናቱም አጣድፎ የበኩሉን ምርመራ ፈፀመ በክርስቶስ ላይ ለሞት የሚያበቃ ውሣኔ በበኩሉ አስወስኖና ወደ ጲላጦስ ወሰደው ጲላጦስ ግን ነገሩን መላልሶ በማጥናት ምንም በደል ያልተገኘበት መሆኑን ተረድቶ ሊለቀው ፈልጐ ነበር:: ነገር ግን የካህናቱ አለቃ ጸሐፍቱም የሕዝብ ሽማግሌዎችም በአንድ ድምጽ ሆነው ስቀለው አስወግደው እያሉ ጮሁ በመቀጠልም ይህን ሰው ካዳንከው ግን የቄሳር ታማኙ አይደለህም እራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ነውና ይህ ሰው የቄሳር ጠላት ነው ለቄሳርም ሰዎች ግብር እንዳይከፍሉ ከልክሎአል ሲሉ ከቄሳር ጋር እንደሚያጣሉት አስፈራሩት በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ሕጋችንም ሞት ይገባዋል ብለው የእነርሱን ሕግ ስለጠቀሱት እንደሕጋችሁ ወስዳችሁ ስቀሉት ብሎ ክርስቶስን አሳልፎ ሰጣቸው:: ጲላጦስ ግን ከነገሩ ንፁሕ እንደሆነ ለማጠየቅ ደሙ በእነርሱ ላይ ይሁን ሲል እጁን በአደባባይ ታጠበ:: ይህም የክርስቶስ እወነተኛነት በእጁም በቃሉም ያልበደለ መሆኑን ያመለክታል:: ማቴ. 27:15-26፣ ሉቃ. 23:1-25 ዮሐ.18:28

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደክፉ አድራጊ በመስቀል ተሰቀለ በመስቀል ተሰቅሎ የሞተ ሁሉ እርጉም ይባል ነበርና እርግማንን ውርደትን ከሰው ለማራቅ ሲል በእንጨት ተሰቀለ ወንጀሉንም ከፍተኛ ለማድረግ በነፍስ ገዳይና በልዩ ልዩ ወንጀል ከተፈረደባቸው ሁለት ወንበዴዎች ጋር ተሰቀለ::

ክርስቶስ በሰው ዘንድ እንደክፉ አድራጊ ቢቆጠርም ሌላው ግዑዝ ፍጥረት ሁሉ ለአምላክ ለመመስከር ወደኃላ አላሉም ስለዚህም ፀሐይ ጨለመ፣ ጨረቃ ደም ሆነ፣ ከዋክብት ረገፉ፣ ድንጋዮች ተሰነጣጠቁ፣ መቃብራት ተከፈቱ፣ ሙታን ተነሱ፣ የቤተመቅድስ መጋረጃ ከላይ እስከታች ተቀደደ:: ማቴ. 15:23፣ ሉቃ.23:44-45

ካህናቱም ፍላጐታቸው የክርስቶስን ሕይወት ለማጥፋት ነበር ይኸው ፈቃዳቸው ተፈፀመ የክርስቶስ ፈቃድ ደግሞ ስለሰው ሕይወት ተላልፎ መሞት ነበር እርሱም ተፈፀመ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሳለ «ሁሉ ተፈፀመ» ሲል የመጨረሻውን ቃል ተናግሮ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በስልጣኑ ለየ:: ዮሐ. 19:30

የአንድ ሰው ሞት ለወገኑ ኃዘን ቢሆን ለሌላው ደስታ ነው:: የክርስቶስ ሞት በእናቱ በእመቤታችን በቅድስተ ቅዱሳንና በደቀ መዛሙርቱ በኩል መራራ ኃዘን ሲሆን በጸሐፍቱና በሊቀ ካህናቱ በኩል ደግሞ ታላቅ ደስታ ሆነ::

የጌታችን የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር

«ንጉሥ የሰቀለው አንበሳ የሰበረው» ይፈራልና በመስቀል ተሰቅሎ የሞተውን ኢየሱስን ለመቅበር የትሩፋት አበጋዞች ዮሴፍና ኒቆዲሞስ የተባሉ ሽማግሌዎች ጥያቄ አቀረቡ:: ጲላጦስም እንደሞተ በሰማ ጊዜ ተደነቀ በመስቀል ላይ የተደረገውን ተአምራት ሰምቶ ስለነበር በእውነት ይህ ሰው ታላቅ ነው ብሎ በመስቀሉ ተጸጽቶ ነበርና ዮሴፍና ኒቆዲሞስም በጠየቁት መሠረት እንዲቀበር ተፈቀደላቸውና በአዲስ በፍታህ ገንዘው ማንም ወደአልተቀበረበት ቦታ ወስደው ዮሴፍ ለራሱ ባዘጋጀው መቃብር ውስጥ ቀበሩት:: ማቲ.27:56-61፣ ማር.15:42፣ ሉቃ.83:5-56፣ ዮሐ.19:38-42

በዚህም ጊዜ መለኮት በአካለ ነፍስ ወደሲኦል ሄዶ ለነፍሳት ነጻነትን ሰበከ 1ጴጥ. 3:18 ከቅዱስ ሥጋው ጋርም ወደ መቃብር ወረደ እንዲሁም ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በእሪና አልተለየም አለምን ይገዛ፣ ያስተዳድር ነበር:: ማቴ. 27:62-66 መቃብር ጠባቂዎችም ተመደቡ:: ለመቃብሩም ቁልፍ ተደረገለት በማሕተምም ታተመ ግን ክርስቶስ መቃብሩን ከፍቱልኝ፣ መግነዝን ፍቱልኝ ሳይል በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ:: ማቴ. 28:77፣ ማር.16:16፣ ሉቃ.24:5: ዮሐ. 20:16

የጌታችንና የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ

ክርስቶስ በተቀበረ በሦስተኛው ዕለት በመንፈቀ ሌሊት ሲነሳ ጠባቂዎች ደነገጡ። እንደበድንም ሆኑ ክርስቶስን ከልደቱ እስከመስቀል ሞቱ ድረስ በደካማነት መልክ እንደሰውነቱ ብቻ ይመለከቱት ነበር። ነገር ግን ትንሣኤው ፍፁም አምላክነቱን፣ አሸናፊነቱን አሳመነ ሞት በእርሱ ላይ ስልጣን የለውም፣ ይዞም ሊያስቀረው አልቻለም። ማቴ.28:4

በክርስቶስ ሞት ያዘኑት ሐዋርያት ቅዱሳት አንስትም ፀጥታ ሳያገኙ ሰንብተው ነበር። በዚህ ቀን ግን በየበኩላቸው ወደ መቃብር እየሄዱ ከመቃብር አካሉን ሰላጡ በበለጠ አዘኑ። ሴቶች ደግሞ ከመመለሳቸው የተነሳ መልአኩ እንዴት ሕያውን ከሙታን ጋር ትፈልጉታላችሁ እርሱ ተነስቷል ከዚህም የለም የሚል የሚያስደስትም፣ የሚያሳዝንም ቃል ሰምተው ተመለሱ እያዘኑም ሲሄዱ ክርስቶስን ከመንገድ አገኙት እጅም ነሱት /ሰገዱለት/። ማቴ.28:5-10 እርሱ ግን ሂዱና ለደቀመዛሙርቶቼ እንደተነሳሁ ንገሯቸው አላቸው እነርሱም ሲነግሩ ሲሄዱ ሐዋርያት ከመንገድ ከክርስቶስ ጋር ተገናኙ በክርስቶስ መነሳት በደቀመዛሙርቱ በኩል ፍፁም ደስታ ሲሆን በሊቀካህናቱና በጸሐፍቱ በኩል ደግሞ፣ ኃዘን፣ ፍርሃት ሆነ ስለዚህም ትንሣኤው ለሕዝብ እንዳይነገር እኛ ተኝተን ሳለን ደቀመዛሙርቱ መጥተው ወሰዱት ተብሎ እንዲነገር አስደረጉ። ማቴ. 28:11-15 ክርስቶስ ግን ለደቀመዘሙርቱ «ሰላም ለእናንተ ይሁን ሞት ጠፋላችሁ» ብሎ በኃዘን ተወግቶ የነበረውን ልባቸውን አጽናናላቸው ማቴ.28:9

እንዲሁም ከእነሱ ጋር እየወጣና እየወረደ እንደቀድሞው እየበላና እየጠጣ አርባ እለት /ቀን/ አብሯቸው ቆየ። የሐዋ. 1:1-4

የጌታችንና የመድሐኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ እርገት

መድሐኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ተልእኮ ደከመኝ ልረፍ ሳይል በመውጣት፣ በመውረድ ፈፀመ ማጠቃለያውም ሞቱን አደረገ። በመልእልተ መስቀል ተሰቅሎ ደሙን አፍስሶ ሥጋውን ቆርሶ ለሰው ልጅ ክሶ ከሙታን ተለይቶ ከተነሳ በኋላ የሚፈጽመው ሌላ ተልእኮ ስለሌለው የቆየው 40 ቀን ብቻ ነበር። ከዚህ በኋላ ወደላከው ወደ አብ አረገ የሐዋ.1:1-4 ደቀመዛሙርቱ ተሰብስበው ባሉበት የማጽናኛ ቃል «እናንተ ግን ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ቆዩ» ብሎ ነግሮአቸው አረገ። ሉቃ.24:48-52

ደቀመዛሙርቱም እጅ ነስተው ወደኢየሩሳሌም ተመለሱ ሉቃ. 24:50-52 120 ቤተሰቦች የሚያህሉ ሳይለያዩ የተሰፋውን ቃል ይጠባበቁ ነበር። የሐዋ.1:15 120 ቤተሰብ የሚባሉትም 12ቱ ሐዋርያት፣ 72ቱ አርድዕት /ተማሪዎች/፣ 36ቱ ቅዱሳት አንስት ነበሩ ቅድስት ድንግል ማርያምም ከእነዚህ ሁሉ አልተለየችም ነበር።

እንግዲህ ከመምጣቱ እስከ እርገቱ ያለውን ታሪክ ያቀፈውን ምሥጢረ ተዋህዶ በማጤን የአምላክ ውለታው እንዳይረሳን ሲያሳስበን ከዚሁም ጋር ፍጡር ነው፣ አማላጅ ነው ተብሎ የማይጠራ፣ የማይባል መሆኑን በመገንዘብ በትጋትና በንቃት ፍቅሩን ተላብሰን ፍጹም በአምላክነቱ አምነን በሕይወታችን ለዘለዓለም ልንጠቀም ይገባል።

ምዕራፍ ሦስት

ሙሴ ጸሊም ማን ነው?

የስሙን ትርጉም ስንመለከተው ጸሊም ጨለማ ጥቁር ማለት ሲሆን ሙሴ ጸሊም መልኩ እጅግ ጥቁር የሆነ ጨለማን የሚመስል ፊት ያለው በትወልዱም ኢትዮጵያዊ ነው ይባላል። በግብሩም /በስራውም/ አምላኩን የማያውቅ እጅግ ጨካኝ አረመኔ ከክፉ ሥራ ውስጥ ይህ ቀረው የማይባል ዘራፊ፣ ወንበዴ /ቀማኛ/ ሰው ገዳይ የነበረ ዝናው የታወቀና ስሙ ሲነገርና ሲጠራ ሰው ሁሉ የሚሸሸውና የሚፈራው በጉልበቱ የሚመካ ኃይለኛ አንድ በግ /ጠቦት/ ብቻውን እንደ ሸንኩርት ልጦ የሚያቀላጥፍ ወይም የሚበላ፣ አንድ እንስራ ወይን የሚጠጣ፣ አንበሳ አንቆ የሚገድል፣ ሰው ገድሎ በጦር ሰክቶ ሥጋውን ለሰማይ አሞራ የሚሠጥ፣ ወንዝ ውኃ ቢሞላበት ደረት ለደረት ተጋፊቶ ዋኝቶ የሚሻገር ሰው ነበር።

የሚኖረውም ፀሐይን ለሚያመልኩ ሰዎች አገልጋይ ሆኖ ስለነበር ጌቱቹም ሲሞቱ ለልጆቻቸው በመገዛት ሥራውን ቀጠለ በዚህ በስራውም ወቅት እሱን የሚመስሉ ጓደኞች ስለነበሩት ከሱ ጋር አብረውት ወደ ዘረፋና ቅሚያ ይወጡ ነበር የጌቶቹ ልጆችም ልክ እንደቤተሰቦቻቸው በፀሐይ በጨረቃ የሚያመልኩ ስለነበረ አገልጋዮቻቸውንም ልክ እንደ ወላጆቻቸው ያስተዳድሯቸው፣ ይገዟቸው፣ ያሠሯቸው ነበር። ታዲያ በዚህ ወቅት ነበር ሙሴ በዘረፋም ሥራ ሲጓዝ ወደ በረሃ ውስጥ የገባው። የፀሐዩ ዋዕይም /ሙቀት/ እጅግ ከፍተኛ ስለነበር ከአንዲት የዛፍ ጥላ ሥር በማረፍ ቀና ብሎ ወደ ሰማይ በማየት ስለ አምላክ መመራመር በልቡ ማሰብ ጀመረ። ከዚህ በፊት እንደዚሁ የሰውን አፈጣጠር ለመመርመር ብሎ ወላጅ የሆኑ እናቶች ማኅፀንን ቀዶ ይመለከት ነበርና አሁንም ይህች ፀሐይ ምን አምላክ ናት ፀሐይ ሆይ አምላክ ከሆንክ ንገረኝ እያለ በልቡም ሁልጊዜ የማላውቅህ፣ የማላይህ አምላክ «አጠይቀኒ ርእስከ» /ራስህን አስረዳኝ፣ ግለጥልኝ/ ይል ነበር። ከፀሐይም ምንም መልስ ሲያጣ አምላክስ የኛ ጌቶች ናቸው በልተው ጠጥተው

ከጥላ አርፈው የሚውሉ ፀሐይ ግን ሲመሽ ትጠፉለች ለጨለማ ቦታዋን ለቃ ሌሊት አትታይም ጠዋትም ትወጣለች ስትሄድ ትውላለች በማለት ለጓደኞቹ ነገራቸው እነሱም በዚህ በግብፅ በረሃ ውስጥ ገዳመ አስቄጥስ ነበርና ምን አምላክ አምላክ ትላለህ አምላክስ ከፈለግህ ያውልህ እዘያ ማዶ ገዳም ግባ ቢሉት ወዲያው ወደ አባ ኤስድሮስ ገዳመ አስቄጥስ ተነስቶ ሄደ መነኮሳቱም ፈጣራያቸውን ሰ ያጠድሱ /ሲያመሰግኑ/ ሰማ።

መነኮሳቱም ዝናውን ያውቁ ስለነበር ባዩት ጊዜ ተሸበሩ ሊዘርፍ፣ ሊቀማ መጣ ሲሉ አበምኔቱ አባ ኤስድሮስ ግን እግዚአብሔር ስለ ሙሴ ጸሊም በጎ አሳብ ስለገለጠላቸው መምጣቱን አውቀው ጸጋ እግዚአብሔር ጦርታ አምጥተዋለችና ያለመጠራጠር ተቀበሉት ካሉ እና ከተቀበሉት በኋላ ጥያቄ አቀረቡለት ለምን መጣህ? ቢሉት አምላክን አገኝ ብዬ፣ ታስተምሩኝ ታሳውቁኝ ዘንድ ሲል መልስ ሲሰጥ አባ ኤስድሮስ ሙሴን ይዞ ወደ አባ መቃርስ ዘንድ ወሰደው በዚያው አስተምረው በንስሃ ቀጥተው፣ መክረው፣ አጥምቀው፣ በክርስትና የእግዚአብሔር ልጅ ይሆን ዘንድ አስተካክለው ደግ ሰው እንዲሆን አደረጉት /አበቁት/።

ሰው የሚሠራት ትሩፋት /ደግ ሥሣብ/ ሁሉ በእግዚአብሔር አጋዥነትና ፍቃድ ትፈጽማለች እና እንዲህ ብሎ ጌታ እንደተናገረ «ፀጋ እግዚአብሔር ወደ ትሩፋት ታመጣለች /ሰውን ትስበዋለች/» የምትስበውም በሦስት ነገር ነው። ከእነዚህ በአንዱ ለመመረጥ ታብቃዋለች እነሱም:-

1. በማሰብ
2. በመማርና
3. ቅዱሳት መጽሐፍትን በማንበብ ናቸው።

ሙሴ ጸሊም ሕሊናው ወደ በጎ ነገር ስትሳብ እና ስትመራመር ፀጋ እግዚአብሔር አገኘችው፣ አዋቂም አደረገችው። በዚህ ግብሩም ከብሉይ ዘመን አምላኩን

ተመራምሮ እንዳገኘ እንደአብርሃም ከሐዲስ ኪዳን ዘመን ደግሞ ሙሴ ጸሊም ነው ተብሎ ይነገራል::

የአባታችን የሙሴ ጸሊም ገዳማዊ ሕይወቱ

ይህ አባት ገዳማዊ ሕይወቱን ክርስትናን ተቀብሎ ስልጣነ ክህነትን ለመቀበልም በቃ ታዲያ ከእለታት በአንዲት ቀን ከጓደኛው ዮሐንስ አጺር /ዮሐንስ አጭሩ/ ጋር ሳለ የቤተክርስቲያኑ የገዳሙ አባቶች ሙሴ ጸሊምን አንተ ጥቁር፣ አንተ አስቀያሚ፣ አንተ መልከጥፉ መሳይ ቅዳሴ ግባና አገልግል አሉት እሱም በአባባላቸው ቅር በመሰኘቱ አልገባም እነሱም ምነው ተቀየምከን ቢሉት መልስ ስላልሰጣቸው ጓደኛውን ዮሐንስ አጭሩንም አንተ ድንክ፣ የምድር ጉድ፣ አጭር እስቲ ግባና ቀድስ ቢሉት እሺ በጄ ብሎ ተቀበሎ በደስታና በውዴታ በፍቅር ሊቀድስ ገባ ምንም ቅር ሳይለው ነበርና «ምንም አልዋሻችሁም የሌለብኝን አልተናገራችሁኝም ያለብኝን ጉድ የሚያሰኝ አጭርነቴን ነው» ሲል መልስ ቢሰጥ በል አንተ በቅተሃል ግባ ብለውት ቀድሶአል:: ሙሴን ግን ገና ይቀርሃል በተጋድሎህ በርታ ብለውት ከዚያም በኋላ እሱም በምንኩስናው፣ በፀሎት በመጋደል ለብቃት ሊደርስ እና ለመቀደስ /ለማገልገል/ በቅቷል::

በዚህ በተጋድሎው ወቅት የክርስቲያኖች ሁሉ ጠላት ዲያቢሎስ /ሰይጣን/ መሆኑንም ባወቀና በተረዳ ጊዜ መቼ አግኝቼው አንበሳውን አንቄ እንደምገድለው ያን ሁሉ የውጋ ጉርፍ በሃይል ዋኝቼ ገፍቼው እንደምሻገር እሱንም ድል ባደረኩት ከእንግዲ ማንንም አያስቸግርም የሚል ሃሣብ እንደነበረው ክርስቲያኖችም ዲያቢሎስን በጉልበት በኃይል የሚያሸንፉ ይመስለው ስለነበር፣ ነገር ግን ሰይጣንም ይህን ሃሣቡን ስላየ /ስላወቀ/ ፈተና፣ መከራ አበዛበት በዚህ ጊዜ ለአባ ኤስድሮስ አማከራቸው እሳቸውም የበቁ አባት ስለነበሩ ጸጋ እግዚአብሔር የተገለጣላቸው ናቸው:: ወደ ተራራ፣ ወደ ሠገነት ላይ አውጥተው ቅዱሳን መላእክትን በምሥራቅ ርኩሳን መላእክትን /አጋንንትን/ በስተምዕራብ አሰልፈው የሚዋጉ አስመስለው አሳዩት ምንድን ናቸው ቢላቸው

በኃይሌ በጉልበቴ ብለህ በራስህ ከተመካህ እነዚህ አጋንንት ይዋጉሃል::

ነገር ግን በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በሱ ፈቃድ፣ ኃይል ይሁን ያልክ እንደሆነ በምስራቅ በኩል ያየሃቸው ቅዱሳን መላእክት ይረዱሃል፣ ይጠብቁሃል ቢሉት እሱም ወዲያው መልሶ በእግዚአብሔር ፈቃድ ቸርነት ነው እንጂ በማለት የፍቅር ምክራቸውን በተግባር ላይ በማዋል በጾምና በፀሎት ተጋድሎውን፣ በስግደት ሥጋውን በቁመት በማድከም፣ በመብል፣ በመጠጥ፣ በዝሙት፣ በመግደል የሚፈታተነውን ጠላት ድል ለመንሳት ይጥር ነበር:: አባ ኤስድሮስም ይመክረውና ያጽናናው ነበር::

ከተጋድሎውም ብዛት የተነሳ ብዙ አረጋውያን በሚተኙበት ጊዜ በየቤታቸው እየዞረ ውኃ ከበረሃ ሂዶ እየቀዳ በተዓምራትም በየእንስራቸው ይሞላላቸው ነበር:: ብዙ ዓመትም በዚህ ሥራው ቀጠለ፣ ዲያቢሎስ ግን በዚህ ሥራው ቀናበትና ደበደበው እግረ ሽባ ሆኖም ታሞ ከመተኛት ደረሰ:: ይሁን እንጂ ባለጋራው ሰይጣን እንደታመመ ባወቀ ጊዜ ፈተናውን ጨመረበት ሥጋው በእሳት ውስጥ እንደተቃጠለ እንጨት እስኪመስል ድረስ ተጋደለ:: እግዚአብሔርም ትዕግስቱን ባየ ጊዜ መከራውን ሁሉ አስወገደለት ሰይጣንን ድል እንዲነሳው አበቃው መንፈስ ቅዱስ ወረደለት /ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ተሰጠው/:: ቅምስት መቶ የገዳሙ አባቶች ተሰብስበው አበምኔት እንዲሆንላቸው መርጠው ቅስና ሾሙት ሊቀጳጳሱ ግን ይህን ጥቁር ሰው ለምን አመጣችሁት ሲሉ ሙሴም «አዎ እኔ መልኬ ቢከፋ ሥራዬ ቢከረፋ አይተው እውነት ተናገሩ ሲል መለስ ሊቀጳጳሱ በመገረም መለሱና ሙሴ ጸሊም ሆይ እነሆ ሁለመናህ ጸአዳ ብሩህ ነው ይገባኻል አሉት::»

ከእለታት በአንዲት ቀን ብዙ አረጋውያን ወደሱ መጥተው ሳለ ውኃ አጥቶ ሲወጣ ሲገባ አይተው ምን ሆነሃል አሉት ውኃ ካላገኘሁ ምን አጣጣችኋለሁ ብዬ ነው አለ ወዲያው ጌታ በቸርነቱ /በቤቱ/ ዙሪያ ውኃውን

አዘነበለት እንግዶቹንም አጠጣ ብዙ ተዓምራትንም ለማድረግ ወደ ብቃት ደረሠ::

ከብቃቱም /ከእምነቱ እና ከታማኝነቱ፣ ከታዛዥነቱ ከተጋደሎው/ በጌታ ቸርነት ጸጋውን ስላበዛለት ከነፅሮተ ሥሉስ ቅዱስ ሥላሴን በመንበራቸው፣ እንዳሉ ከፅረሐ-ዓርያም እስከ ታችኛው እንጦሮጦስ /በርባሮስ/ ድረስ እስከማየት በቃ:: በመንፈሳዊ አባትነቱ ዝናው ተሰማ እግዚአብሔርም ቸር፣ ደግ አምላክ መሆኑ ምንም ቢበድሉ በቅን ልብ ቢመለሱ ከፍፁምነት /ከብቃት/ ደረጃ እንደሚያደርስ ታወቀ:: /1/

ባላጋራችን ዲያቢሎስ እንኳን እኔ አባታችሁ ሙሴ ጸሊም ነኝ መጣሁላችሁ ብሎ በገዳሙ የነበሩትን ሁሉ በሙሴ ጸሊም መንፈሳዊ ሕይወት ይመኩ፣ ይደሰቱ እና አምላከ ሙሴ ጸሊም እያሉ ይፀልዩ ስለነበር መነኮሣቱን ለማሳሳት «እኔ ሙሴ ጸሊም መጣሁላችሁ» ብሎ ተመስሎ ወደ አልሆነ ቦታ ሲያስወጣቸው ተጠራጠሩትና በሥላሴ ስም ቢያማትቡበት ካጠገባቸው እንደጢስ በኖ እንደጉም ተኖ ተሰወራቸውና በፍፁም እምነት ወደ ፀሎታቸው ተመለሱ:: በዚህ ሁኔታ ገዳማዊ ሕይወቱን ካየን አሁን ደግሞ ወደዜና እረፍቱ በሚቀጥለው ላይ እንመልከት::

የአባታችን የሙሴ ጸሊም ዜና እረፍት

ሙሴ ጸሊም ሰውን የሚገድል መሆኑን ከላይ በርእሳችን ላይ እንደጠቀስነው አሁን ደግሞ ንስሃ ገብቶ፣ በገዳም ተወስኖ፣ በጾም፣ በጸሎት፣ በተጋድሎ ጸንቶ በጽድቅ ደረጃ /ከብቃት/ ቢደርስም እንዲህ ይል ነበር:: «እኔ ብዙ ሰው በግፍ ስገድል ነበርና ያንን ሞት ካገኘሁት እኔም መቀበል አለብኝ» ሰውን የገደለ፣ የሰው ደም ያፈሰሰ ደሙ ይፈሳል የሚለውን በማሰብ ይመኘው ስለነበር በሰው እጅም እንደሚሞት ታውቆት በመረዳቱ እነሆ ከእለታት፣ ከዘመናት በኋላ የነበረበት ገዳም በአረማውያን ተከበበ መነኮሳቱም ተሸበሩ ደነገጡ ብዙዎቹም ሸሹ አባ ሙሴ ጸሊም ግን ከተወሰኑት መነኮሳት ጋር በመሆን እያበረታታቸው ለተቀደሰ

ሰማዕትነት እንደሚበቁ ከፍ ያለ ዋጋ እንደሚያገኙ እየመከራቸው አብረውት ጸንተው እስከ መጨረሻው ሳይሸሹ በሰማዕትነት ሊያርፉ ችለዋል:: ስለዚህ ሙሴ ጸሊም በነዚሁ አረማውያን በጭካኔ ታርዶ ሰማእትነትን ተቀብሏል:: የእረፍቱ ቀንም ሰኔ 24 ነው:: በዚሁ እለት በቅድስት ቤተክርስቲያናችን የእርፍቱ መተሰበያ እንደሆነ ታውቆ ይታሰባል /ይዘከራል/:: /2/

ማጠቃለያ

- ንስሃ ኃጥኡን እንዳጻድቅ፣ ዘማዊውን እንደ ድንግል፣ ርኩሱን እንደ ንጹሕ የምታደርግ ደገኛይቱ ስጦታ ናት:: እኛም ከማንኛውም ክፉ ምግባራችን ተመልሰን ወደ እግዚአብሔር አባታችን ብንቀርብ ይቅር ብሎ ጸጋውን ሊሰጠን ፈቃዱ ነው:: /3/

- ሙሴ ጸሊም አንድ ጊዜ ኃጢአቱን ሁሉ እርግፍ አድርጐ ለመተው ቆርጦ በማሰብና በመነሣሣት እንደ አብርሃም አባታችን ጣኦቱን ሰብሮ በብዙ ፍጥረታት አምልኮ በኋላም «አምላከ ፀሐይ ተናበበኒ» የፀሐይ አምላክ ተናገረኝ፣ አነጋግረኝ፣ ልወቅህ እያለ በበጐ ህሊና ቢመራመርና ቢመለስ እግዘአብሔር አምላካችን አብርሃም ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአበትህም ቤት ቍለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፣ እባርክሃለው::/4/ ብሎ በመጥራት ለታላቅ ክበር አብቅቶታል:: ይህ አባትም በዘመነ ሐዲስ አምላኩን ተመራምሮ ያገኘ ሙሴ ጸሊም ተብሎ ይነገርለታል:: ከኃጢአት ግብሩ ፍጹም ትቶ ፈጣሪውን አግኝቶት በገዳም በጾም በጸሎት ከተወሰነ በኋላ ወደ ኋላ ዞር ብሎ ያሳለፈውን የኃጢአት በደል /የመርገም ጨርቅ/ አወልቆ ጥሎ እስከመጨረሻው በመጽናት እንደሰማዕቱ ሊቀዲያቆን ቅዱስ እስጢፋኖስ ሥላሴን ከማየት ሰማዕት ከመሆን ደረሰ::/5/ እኛስ ምን እየሰራን ይሆን? ንስሃ ገብተን በጽድቅ ሥራችን እስከመጨረሻው ጸንተናል?/6/ ወይስ ለጥቅምና ለወዳሴ ከንቱ በመሻት ወደ ኋላ

ተመልሰናል? ነው ወይም የሎጥ ሚስትን በግብራችን መስለናታል? ውሻ ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ ነን? ወይንስ እንደ እርያ /እሣማ/ ታጥቦ ጭቃ እነሆን? /7/

- የእኛስ እምነትና ክርስትና የአብርሃምን፣ የሙሴ ጸሊምን የሎጥን፣ የቅዱስ እስጢፋኖስን ፈለግ የሐዋርያትን ት/ት መከተል የጌታችንን ትዕዛዙን መጠበቅ አለብን::/8/ ያለበለዚያ ግን እንደ ሎጥ ሚስት የሰዶምና ገሞራን ኃጢአት ቅጣት ዞር ብለሽ አትይ ወደኋላ እንዳታይ ከባልሽና ከልጆችሽ ጋር ወደፊት መቅሰፍት በሌለበት በመልካሙ መንገድሽ ሂጂ ቢላት ቃሉን መጠበቅ ተስኗት ለአንድ አፍታ ወደኋላዋ ዞር ብላ ብታይ ትእዛዙን ብትጥስ ከዚያው ዞር ብላ ቀረችዋ:: የጨው ሐወልት ሆነች:: ሰው ከመሆን ተቀይራ ወደ ሐወልትንት/9/ ማሰብ ማወቅ የተሰነው የማይንቀሳቀስ ሐወልት! እኛም ዛሬ ንስሃ ገብተን በጽድቅ ሥራ ላይ እያለን ወደ ቤተክርስቲያን እየሮጥን ሰንበት ት/ት እየተከታተልን እየተማርን ወደኋላ ተመልሰን ከዚህ ግብራችን ብንወጣ ዓለም ብታሸንፈን ታጥቦ ጭቃ ወይም በቁሙ የሞተ ሰው እንዳንሆን እንጠንቀቅ የቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ፣ የሚሮጥም እስከ መጨረሻው በሐይማኖቱ፣ በእምነት ፀንቶ ይሩጥ:: /10/

እንግዲህ ከወዴት እንደወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ አለዚያ እመጣብሃለው/11/ ንስሃም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ::

- እስከ ሞት ድረስ የታመንክ ሁን የሕይወትንም አክሊል እስጥሃለው:: /12/

- እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ... /13/

- እንግዲህ ቅና ንስሃም ግባ .../14/ ድል የነሣው በሁለተኛ ው ሞት አይጐዳም /15/

አምላከ አብርሃም፣ ይስሐቅ ወያዕቆብ፣ ወሙሴ ጸሊም ንስሐ ገብተን ሃይማኖት ከምግባር ሰርተን ቅዱስ ሥጋውን ወክቡር ደሙን በልተን ጠጥተን ያዘጋጀልንን ገነት፣ መንግስተ ሰማያትን ለመውረስ ያብቃን አሜን::

መጽሐፍ ቅዱስ፣

1. ሮሜ. 5:19፣ ያዕ. 4:6 2ጴጥ. 3:9-10
2. ማቴ. 10:41-42
3. ምሳ. 28:13፣ሐዋ. 2:38
4. ዘፍ. 12:1-2
5. ሐዋ. 7:55-56
6. ዕብ. 3:14-15
7. ምሳ. 26:11፣ 2ጴጥ. 2:22
8. ማቴ. 19:15-19
9. ዘፍ. 19:26
10. 1ቆሮ. 10:12
11. ራእይ 2:5-6
12. ራእይ 2:10-11
13. ራእይ 3:20-21
14. ራእይ 3:19
15. ራእይ 2:11

ምዕራፍ አራት

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ያን ግን እወቁ ባለቤት ከሌሊቱ ሌባ በየትኛው ክፍት ቦታ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ በነቃ ቤቱም ሊቆፈር ባለተውም ነበር ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሰዓት ይመጣልና:: ማቴ.24:43-44

እርሱም እናንተ የማታስተውሉ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድ እና ወደክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ በመጻሕፍት የተጻፈውን ሁሉ ተረጐመላቸው:: ሉቃ. 24:25-27

ስለዚህ ከሙታን ከተነሳ በኋላ ደቀመዛሙርቱ ይህን እንደተናገረ አሰቡና መጽሐፍንም ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ:: ዮሐ. 2:22

በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ ይህም ለእነርሱ የጥፋት ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው:: ይህም ከእግዚአብሔር ነው:: ስለክርስቶስ ተስጥቶአችኋልና ስለእርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም በኔ ያያችሁት አሁንም በኔ እንዳለ የምትሰሙት ያው መጋደል ደርሶባችኋልና:: ፊልጵስዩስ 1:28-30

ዘመኑን እየዋጃችሁ በውጪ ባሉት ዘንድ በጥበብ ተመላለሱ ለእያንዳንድ እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁል ጊዜ በጨው እንደተቀመመ በጸጋ ይሁን:: ቆላስይስ 4:5-7

የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሉ የሚለውጠን እንጂ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃሉን የምንለውጥ አንሁን::

አሕዛብ፤ ትንቢት ያልተነገረላቸው ሱባኤ ያለተቆጠረላቸው በተለያዩ አማልክት ሲያመልኩ የኖሩ ግዝረትና የመመሪያ ሥርዓት የሌላቸው የተበታተኑ ተስፋ የሌላቸው ሕዝቦች ማለት ነው::

አምላክ፤ ቃሉ ገዥ፣ ፈጣሪ፣ ክብርና ኃይል ሥልጣንም ያለው ነው ብዙን ጊዜ እግዚያብሔርን ያመለክታል:: በተለያዩ ጊዜያት በብሉይ ዘመን፣ በሐዲስ ዘመን ተገልጿል::

በተለያዩ ቦታዎች በኮሬብ /በእግዚአብሔር ተራራ፣ እንደገና በሲና ተራራ ዘፀአት 3:1-4፣ ዘዳ.19:10፣ በሐዲስ ኪዳን በደብረታቦር፣ በዮርዳኖስ በተለያዩ ሁኔታዎች ዘፍ. 3:8-10 /በድምጽ/ ዘዳ. 3:1-6 /በእሳት/፣ዘዳ. 19:18 ዘዳ. 14:24 /በእሳትና በደመና/፣ ዘዳ. 5:22-27 /በደመና/፣ዘዳ. 19:9-12 /በደመና/፣ ዘዳ. 24:15-18፣ ዘዳ. 33:8-11፣ ዘዳ. 34:5

መጽሐፍ ቅዱስ ለምን ቅዱስ ተባለ? ቅዱስ የሚለው ቅጽል ለምን ተቀጸለለት?

መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች በዓለም ላይ ካሉት ወይም ከሚገኙት መጻሕፍት ተለይቶ ቅዱስ የተባለበት ምክንያት:-

፩ ከእግዚአብሔር አፍ የተገኘ ስለሆነ፣
፪ ስለ ቅዱስ እግዚአብሔር የሚናገር ስለሆነ፣
፫ ምዕመናንን ወደቅድስና የሚጠራ፣ የሚጋብዝ ስለሆነ፣
ዘሌዋ. 11:44፣ ዘሌዋ. 19:2-3፣ 1ኛጴጥ. 1:15-16

መጽሐፍ ቅዱስን ማን ጻፈው?

እግዚአብሔር ቅዱስ ቃሉን ያስተላለፈው በሰዎች አማካኝነት ለሰዎች በመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስን 40 የተለያዩ ሰዎች ጽፈውታል::

መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ተጻፈ?

መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር ገላጭነት በእግዚአብሔር መሪነት ተጻፈ:: መጽሐፍ ቅዱስን የተለያዩ ሰዎች ተግባር ወይም ሥራ በማስነሳት ቅዱስ ቃሉን እግዚአብሔር አጽፎአቸዋል:: ለምሳሌ:- ሰሎሞን ንጉሥ ነበር:: ምሳ. 1:1 አሞጽ. እረኛ ነበር:: አሞ. 7:14፣ ሕዝቅኤል ካህን ነበር:: ሕዝ. 1:3: ጴጥሮስና እንድርያስ ዓሣ አጥማጆች ነበሩ:: ማቴ. 4:8፣ ያዕቆብና ዮሐንስም እንዲሁ ዓሣ አጥማጆች ነበሩ:: ማቴ. 4:12: ማቴዎስ ቀራጭ ነበር:: ማቴ. 9:9፣ ሉቃስ ሐኪም ነበር:: ቆላ. 4 ከ1 ጀመሮ

በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው እግዚአብሔር አምላክ በመረጣቸውና በቀደሳቸው ሰዎች ነው:: ኤር. 1:4-10፣ 2ጴጥ. 1:20-21

የአማልእክት ስም

በአል 1ነገ. 16:31፣ 2ዜና መዋዕል 17:3
የጣኦት ስም 1ነገ. 11:33፣ 1ነገ. 18:21-40፣ 1ዮሐ. 5:21

<u>ሕዝብ:-</u> የሚለው ቃል ሲተረጎም ትንቢት የተነገረላቸው ሱባኤ የተቆጠረላቸው ፍጥረታትን ሁሉ በፈጠረ በአንድ አምላክ በማምለክ የታወቁ ግዝረትና የመመሪያ ሥርዓት ያላቸው ባለተስፋ ሕዝቦች ማለት ነው::

<u>አረማዊ:-</u> ማለት እስራኤላዊ ያልሆነ ሥርዓትና ሕግ የሌለው መደዴና ያልሰለጠነ ሕዝብ ማለት ነው::

<u>መናፍቃን</u>:- ማለት የቤተክርስቲያን ሰዎች ሳይሆኑ የቤተክርስቲያን መስለው ወይንም

ከቤተክርስቲያን እምነትና ትምህርት ግማሹን ያልያዙ /በእምነት ሙሉ ያልሆኑ ጎደሎ/ ሰዎች ማለት ነው::

በአንድ ሃይማኖት ውስጥ የተለያዩ ሃሳቦችን የሚከተሉ፣ የሆነውን ለማመን የሚያመነቱና የሚጠራጠሩ ሰዎች መናፍቃን ይባላሉ:: ገላ. 5:19-21፣ 1ዮሐ. 2:19-20

መጽሐፍት በሁለት ታላላቅ ክፍሎች ይከፈላሉ እነርሱም:-

፩ መጽሐፍ አምላካዊ /መጽሐፍ መንፈሳዊ/
፪ መጽሐፍ አለማዊ በመባል ይታወቃል::

እግዚአብሔር በተለያዩ ጊዜ በተለያዩ ቦታዎች በተለያዩ ሁኔታዎች በአርአያውና በምሳሌው ለፈጠረው ከፍጥረታትም ሁሉ በላይ ላከበረው ሰው ራሱን ገልጿል:: እግዚአብሔር አምላክ ለሰው ልጆች እራሱን ከገለጸባቸው ነገሮች አንዱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ቅዱስ ማለት የተለየ፣ ልዩ ማለት ነው:: ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ የተለየ፣ መጽሐፍ፣ ልዩ መጽሐፍ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ የሚያደረገው:-

፩ በዘመን ፍጻሜ የማይለወጥ ስለሆነ፣
፪ ተቀባይነቱም የማይሻር በመሆኑ ነው:
፫ ሲነበብ ቢውል ቢያድር የማይሰለች ስለሆነ፣
፬ ትርጉም አዘል ምስጢር ያለው በመሆኑ: ከሌሎች መጽሕፍት ይለያል::

ከላይ የጠቀስናቸው ሰዎች ከተለያዩ የሥራ መስክ ለዚህ ለተቀደሰና ክቡር ለሆነ ሥራ መመረጥ የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ዘንድ ሰው ሁሉ እኩል

መሆኑንና እግዚአብሔርም እምነትና ትሁት ስብእና ያለውን እንደሚመረጥ ያስተምረናል።

መጽሐፍ ቅዱስ መቼ ተጻፈ?

- መጽሐፍ ቅዱስ ከ1400 ዓመተ ዓለም እስከ 400 ዓመተ ምህረት ባለው ዘመን ውስጥ ተጻፈ።

መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በምን ቋንቋ ተጻፈ?

መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በእብራይስጥ ቋንቋ ተጻፈ ምንም እንኳን የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ /ብሉይ ኪዳን/ በእብራይስጥ ቋንቋ ቢጻፍም እስከ አምስተኛው መቶ ክ/ዘመን ድረስ በአምስት ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ተተርጉሟል።

፩ በሶሪያ
፪ በጥንቱ ላቲን /ቮልጌት/
፫ በቅብጦ /ኮፕት/
፬ በኢትዮጵያ /ግዕዝ/
፭ በአርመን

በእነዚህ ከላይ በጠቀስናቸው ቋንቋዎች የተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ከዋናው እብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ ተቀድቷልና /ተገልብጧልና/ 2ቆሮ. 5:16-21

በ1525 ዓ.ም ቴንዳየል የተባለ እንግሊዛዊ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ እንግሊዘኛ ተረጉመው። በ1534 ዓ.ም ሉተር ወደጀርመንኛ ተረጐመው በዚህ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ በየቋንቋው እየተቀዳ በአሁኑ ወቅት ከ1500 በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ለመጻፍ በቅቷል።

መጽሐፍ ቅዱስ ለምን በአንድ ጥራዝ እንዲዘጋጅ አስፈለገ?

ወደ መጨረሻው ዓመተ ዓለም አካባቢ ፍልስፍና በዓለም ላይ በተለይም በእስክንድርያ፣ በሶርያ፣ በሮም፣ በግሪክና በቁስጥንጥንያ አካባቢ እጅግ በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍቶና ገኖ ወደ ክርስትናው ዘመንም ተሻገረ። በሐዲስ ዘመን የተከሰተው የክርስትና እምነት የፈላስፎችን ከንቱ መራቀቅ ውድቅ ስላደረገው በአራት መቶኛው ዓ.ም መግቢያው ላይ የነበሩ የዓለም ፈላስፋዎች የክርስትና እምነትን ለማቋቋም በቅዱሳት መጽሐፍት ስም ፍልስፍናቸውን እየጻፉ በየቦታው ይበትኑ ጀመር። የዚህ ዓይነቱ የቅዱሳት መጽሐፍት ሕልውናን /እውነተኛነትን/ የሚፈታተን ሁኔታ ቅዱሳን አባቶቻችን ስላሳሰባቸው በ325 ዓ.ም አርዮስን ስህተቱን ቢያምን ከግዝቱ ሊፈቱት ባያምን ግን ከቤተክርስቲያን አንድነት ሊለዩት የተሰበሰቡት 318ቱ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት ከአርዮስ ጉዳይ በተጨማሪ በፍልስፍና፣ በኑፋቄ፣ በክህደት ያልተበረዙትን ቅዱሳት መጽሐፍት በመለየት በአንድ ጥራዝ እንዲካተቱ በጉባዔው ተስማሙ ይሁን እንጂ ይህን ስምምነታቸውን በ368 ዓ.ም በካርቴጂያ ጉባዔ አጸደቁት። ነገር ግን በ14 ክ/ዘመን /በ14 መቶ ዓ.ም/ በእንግሊዝ አገር በምዕራፍ ሲከፋፈል በቁጥር ግን በ1545 ዓ.ም በፈረንሳይ አገር ተከፋፈለ።

መጽሐፍ ቅዱስ በስንት ይከፈላል?

መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ተብሎ በሁለት ይከፈላል።

ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን ተብሎ በ2 ቢከፈልም 32ቱ ሰዎች ብለይ ኪዳንን፣ 8ቱ ሰዎች ደግሞ ሐዲስ ኪዳንን ጽፈውታል።

ከዚሁ ጋር ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያናችን ከመሰል አብያተ ቤተክርስቲያናት /እህት

አብያተ ቤተክርስቲያናት/ ጋር የምትጠቀምባቸው የቅዱሳት መጽሐፍት ብዛት 81 /ሰማንያ አሀዱ/ ነው:: መሰል እህት አብያተ ቤተክርስቲያናት /የምስራቅ አብያተ ክርስቲያናት፣ ኦሬንታል ቸርች/ የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው::

፩ ግብፅ /እስክንድርያ/
፪ ሶርያ
፫ ህንድ
፬ አርመን
፭ ኢትዮጵያ

ሰማንያ አሀዱን ሳይቀበሉ 66ቱን ብቻ የሚቀበሉ አሉ ከነዚህም ጋር 66ቱን አብራ ትቀበላለች:: ይህም ሲባል የነሱን የተዛባ ሀሳብና ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆነውን ሥጋዊ አተረጓጐማቸውን ግን አትቀበልም 66ቱ የሚባሉት 39ኙን የብሉይ ኪዳንና 27ቱን የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት ሲሆኑ 80 አሀዱ የሚባሉት 46ቱ የብለይ ኪዳንና 35ቱ የሐዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍትን ይቀበሏቸዋል:: 24 እና ከ24 የከፈሉአቸውን እንደገና 14 ብለው ለብቻቸው ይቀበሏቸዋል:: ከላይ በሁለት የከፈሉአቸው ቅዱሳት መጻሕፍት ናቸው:: እነዚህም ቅዱሳት መጻሕፍት በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሲሆኑ እነዚህም ቅዱሳት መጻሕፍት ቤተክርስቲያናችን ከምትቀበላቸው ከ46ቱ ብሉያት መጻሕፍት ውስጥ የሚካተቱና የሚገኙ ናቸው:: ሳምራዊያን ደግሞ 5ቱ የሙሴ መጻሕፍት የሚባሉትን ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ኦሪት ዘዳግም ያሉትን ብቻ ይቀበላሉ::

በ451 ዓ.ም ከኦርቶዶክስስ ተዋህዶ እምነት ተገንጥለው የወጡ ካቶሊኮች ደግሞ የቅዱሳት መጻሕፍትን ከ81 ወደ 76 ዝቅ በማድረግ ይቀበላሉ:: በ16 መቶ ክ/ዘመን የተነሳው ደግሞ 66ቱን ብቻ ይቀበላሉ::

ቅዱሳት መጻሕፍት ከትውልድ ወደትወልድ እንዴት ባለ ሁኔታ ተጠብቀው እስከ አሁን ዘመን /ትወልድ/ ሊደርሱ፣ ሊተላለፉ ቻለ?

፩ በብለይ ኪዳን ዘመን /በጥንት ዘመን/ ቅዱሳት መጻሕፍት በቤተመቅደስ ይቀመጡ ወይም ይጠበቁ ስለነበር ነው:: 2ኛ ነገ.22:8፣ 2ዜና.34:14-15
፪ በዚያ ስልጣኔ ባላደገበትና ባልተስፋፋበት ዘመን ጸሐፊዎች በቅርፊት /ፓፒሩስ/ በጡብና በብራና እየጻፉ በጥንቃቄ ከማስቀመጣቸውም ባሻገር በስደት ዘመንም በመደበቅ ከጥፋት ለማዳን ቆፍረው በመቀበር የራሳቸውን ሕይወት አሳልፎ በመስጠት ለትውልድ ለማስተላለፍ በቅተዋል:: ለምሳሌ በሲና የተጻፈው በ3000 ዓ.ዓ በሲና በረሃ ሲገኝ እንደዚሁ በ400 ዓ.ዓ በእስክርንድርያ የተጻፈው በእስክንድርያ ተገኝቷል::

በ1947 ዓ.ም በሙት ባሕር አካባቢ በእረኛ አማካኝነት ምልክት በመገኘቱ ምርምሮች ከተካሄዱ በኋላ የተገኙት የብራና ጽሑፍ ግኝቶች ከላይ ለጠቀስነው ምስክሮቻችን ሲሆኑ ከእነዚህ ግኝቶች መካከል መጀመሪያ የተገኘው ጥቅል ትንቢተ ኢሳይያስ ሲሆን ከዚሁ ጋር አብሮ ከ1500 በላይ ሙሉ ጽሁፎች ከ5000 በላይ ያልታተሙ ጥቅሎች ተገኝተዋል::

በጥንቱ በብሉይ ዘመን እንጢያቆስ ኤጲፋንዮስ የተባለ መጽሐፍትን ሲያቃጥልና አምልኮ እግዚአብሔርን ሊሽር አዋጅ ባስነገረበት ወቅት /ዘመን/ የመቃቢስ ዘቢንያም ልጆች ባደረጉት ከፍተኛ ተጋደሎ አትርፈውታል በሐዲስ ኪዳን ዘመን ግን 276 ዓ.ም ዱዮቅልጥያኖስና መክስምያኖስ የተባሉ ነገሥታት ተነስተው ክርስቲያኖችን ሲያሳድዱ አብዛኞቹን መጽሐፍት በወቅቱ የነበሩ ክርስቲያኖች በየዋሻው ደብቀው ሲያተርፉአቸው ከመቃጠልም የመትረፍ ዕድል ያላጋጠመውም መጽሐፍ ነበር እርሱም ራእየ ዮሐንስ ነው::

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በተወለደበት ዘመንም ከቤተመቅደስ ከነበሩት መጻሕፍት እየተገለጠ በምኩራብ ይነበብ ነበር:: ሉቃ. 4:16-17

የጥንት ክርስ ኖች እና አባቶች እነዚህን የጥንት ጽሑፎች በእጅ ጽሒፈት አባዝተው አረማዊ ጠላት ሲመጣባቸው ከንዋየ ቅድሳት ጋር በመደበቅ በጉድጓድ ውስጥ በማስቀመጥ በከፍተኛ ጥረት ከትውልድ ወደትውልድ ለማስተላለፍ በቅተዋል:: ይህም ጥረታቸውና ትጋታቸው ያባቶቻችንን ጽኑ እምነትን አርቆ አሳቢነትን ያስተምረናል::

መጽሐፍ ቅዱስ በኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን

በብሉይ ኪዳን

ከክርስቶስ ልደት 1000 ዓመት በፊት የኢትዮጵያ ንግሥት የነበረችው ንግሥት ሳባ በዚያን ጊዜ የእስራኤልም ንጉሥ የነበረውን የንጉሥ ዳዊትን ልጅ የሰሎሞንን ጥበብና ዝና ሰምታ ለመጐብኘት ሄዳ ደርሳ ስትመለስ ከንጉሡ ሰሎሞን ቀዳማዊ ሚኒሊክን ፀንሣ ተመለሰች ልጁም ካደገ በኋላ አባቱን ለመጠየቅ በ20 ዓመቱ ሄዶ ለ3 ዓመትም ቆይቶ ሕገ ኦሪትን ከተማረ በኋላ «በ982 ዓ.ዓ» አካባቢ የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ሕገ ኦሪትን የብሉይ ኪዳን ካህናትንና ታቦተ ጽዮንን ይዞ ወደኢትዮጵያ ገባ:: ኢትዮጵያ ብሉይ ኪዳንን ለመቀበሏ መረጃ የሚሆኑን ጥቅሶች::

1. የሐዋርያት ሥራ 8:26 ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ትንቢተ ኢሳይያስን ማንበቡ፤
2. ግዝረት፤
3. የተከለከለ መባልእት /ምግቦች/፤
4. ሶፎንያስ 3:10 «ከኢትዮጵያ ወንዞች ማዶ የሚማልዱኝ የተበተኑት ሴቶች ልጆቼ ቁርባኔን ያመጡልኛል» የሚሉት ያስረዱናል::

ሐዲስ ኪዳን

የሐዲስ ኪዳንን መጻሕፍት አገባብ ከማየታችን በፊት ክርስትና ወደኢትዮጵያ እንዴት ገባ የሚለውን እንመለከታለን ኢትዮጵያ ክርስትናን የተቀበለችው ፊልጶስ ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ካጠመቀው በኋላ ሲሆን፣ ይህም የሆነው በ34 ዓ.ም ነው የሐዋርያት ሥራ 8:26-40 ጃንደረባውም ወደ ሀገሩ መጥቶ ክርስትናን አስተማረ ይሁን እንጂ እንደቁርባን፣ ክህነት የመሳሰሉት የክርስትና እምነትና ሥርዓት አልገባም ነበር::

በዚህ ሁኔታ እስከ 300 ክ/ዘመን ከቆየ በኋላ በዚሁ ዘመን መግቢያ /መጀመሪያ/ ሜሮጵዮስ የተባለ ነጋዴ /ፈላስፋ/ ከሁለቱ ወጣቶች ጋር በጀልባ ሲሄዱ አደጋ ጣዮች ድንገተኛ አደጋ አደረሱባቸውና ሁለቱ ፍሬምናጦስና ኤጌሲዎስ /ሲድራኮስ/ ቀሩ በዛፍ ስር ሲፀልዩ ወታደሮቹ ኢዛና ወደተበለው በዘመኑ ወደነበረው ንጉሥ ወስዷቸው በኢዛናና በቤተመንግሥቱ ተወዳጅነት ስላገኙ በጅሮንድና ጋሻጃግሬ ሆነው ተሾሙ ከዚያም ንጉሡ ሲሞት ሲል ሁለቱን አስናብቶ የማስተዳድሩን ጉዳይ ለእቴጌይቱ አደራ ብሎ አረፈ::

ንግሥቲቱም ሁለቱን ወጣቶች ለምና ካስቀረች በኋላ የንግሥቲቱ ልጆች እስኪያድጉ ሲረዷት ቆዩ አብርሃና አጽብሃ /ልጆቿ/ አድገው በትረ መንግሥቱን ሲቀበሉ ሲድራኮስ ሀገሩ ሄዶ ካህን ሲሆን ፍሬምናጦስ ግን ወደግብፅ ከእስክንድርያ የክርስትናን ሥርዓት ለማምጣት ሄደ በዚህ ጊዜ የእስክንድርያ ቤተክርስቲያን አባቶች ወደኒቅያ ጉባኤ ሄደው ስለነበር አንድ ዓመት ቆይተው ሲመለሱ ጉዳዩን አቀረበ:: ጉዳዩ ሲታይም ሁለት ዓመት ቆይቶ እንደገና ለቅዱስ አትናቴዎስ አቀረበ አትናቴዎስም እጅግ ተደስቶ የኢትዮጵያውያንን ባህልና ሃይማኖት የሚያውቅ ስለተገኘ ፍሬምናጦስን ኤጲስ ቆጶስ አድርጎ ሾሞ ላከው ከዚያም ወደኢትዮጵያ መጥቶ ካህናትንና ዲያቆናትን ሾመ ወደግራ የነበረውን አጻጻፍ አስተካክሎ ክርስትናን በሰፊው አስተማረ

ቅዱሳት መጻሕፍትንም ከፅር /ግሪክ/ ወደ ግዕዝ ቋንቋ መልሷል ተርጉመዋል።

ከፍሬምናጢስም በኋላ 9ኙን ቅዱሳን ወደኢትዮጵያ ሲገቡ 70 ሊቃውንት የተረጎሟቸውን መጽሐፍት ይዘው ገቡ 480 ዓ.ም በዚህ ጊዜም ክርስትና በበለጠ በኢትዮጵያ የተስፋፋ ሲሆን እነዚሁም ቅዱሳን የግዕዝ ቋንቋ ተምረው መጻሕፍትን ከሱርሱትና፣ ከእብራይስጥ፣ ወደግዕዝ መልሰዋል።

በ14ኛው መቶ ክ/ዘመን በአጼ ዘርአያዕቆብ ዘመን መንግሥት የብሉያትና የሐዲሳት ትርጓሜና የሊቃውንት መጻሕፍት ገብተዋል።

ምሳሌ:- ሃይማኖተ አበው፣ ድርሳናት፣ ፍትሃ ነገሥት ወዘተ ከዚያም በ1514 ዓ.ም በጀርመናዊው ዮሐንስ ፓስተር አማካኝነት መዝሙራት ዳዊትን ወደግዕዝ በደንብ ታትሟል።

ከላይ ያየናቸው ገባ ብለው የሚታዩት ሲሆን በየጊዜው የተነሱ የቤተክርስቲያን ሊቃውንት መጽሐፍትን በየዘመኑ ከእብራይስጥ ከፅርዕ /ግሪክ/ ወደ ግዕዝ ተተርጉመውልናል። እንዲሁም ሊቃውንትና፣ መጽሐፈ መነኮሳት፣ ዜና አበው፣ ገድለሰማዕታትና፣ ስንክሳር፣ የመሳሰሉትም የፀሎትና የሥርዓት መጻሕፍት እንዲሁም ዜና ሐዋርያትንም መጽሐፍ ከግሪክ /ከፅርዕ/፣ ከግብፅ፣ ከአረብ፣ በየጊዜው ተተርጉመዋል።

በዚህ መልኩ ቅዱሳን መጻሕፍት ቢተረጉሙም ንባባቸውና ትርጉማቸው ብዙ ስለነበርና እንደዛሬው ወረቀት የጽሕፈት መሣሪያ ሳይሆን ቆዳ ፍቀው ብራና አለዝበው፣ ቀለም በጥብጠውና፣ አዘጋጅተው በእጃቸው ስለሚጽፉት እንደልብ አልተዳረሰም ነበር። በዚህ ሁኔታ ከቆየ በኋላ 1914 ዓ.ም የጽሕፈት መኪና መጥቶ መታተም ተጀመረ።

በመካከሉም የጣልያን ኢትዮጵያን መውረር አቋረጠው። ያንጊዜ በመታተምና በጥራዝ ላይ የነበረው በየቦታው በዘረፋው ምክንያት ቢወድቁና ቢበታተኑም የተረፉት እስከአሁን አገልግሎታቸውን ይሰጣሉ። ከወረራው በፊት ከታተሙት መጻሕፍትም 4ቱ ወንጌል፣ 14ቱ ቅዳሴ፣ ማርይስሐቅ፣ አረጋዊ መንፈሳዊና ፊሊጵስዩስ መጽሐፈ ሲራክና አምስቱ የሰሎሞን መጻሕፍት ሕዝቅኤልና ወዳሴ ማርያም ሲሆኑ እንዲሁም በነጠላ ትርጓሜ የታተሙት 4ቱ ወንጌላውያን፣ የሐዋርያት ሥራ፣ 14ቱ ቅዳሴ ናቸው።

በ1947 ዓ.ም ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ /ብሉይና ሐዲስ/ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በአማርኛ፣ 1980ዎቹ በአናሲሞስ ናሲብ ወደ ኦሮምኛ፣ በ1948 ዓ.ም በአባ ተወልደ መድኅን ገብሩ ወደ ትግሪኛ ተተርጉሟል። በዚህ መልኩ እየታተሙ በአሁኑ ወቅትም ከ20 በላይ በሚሆኑ የአገራችን ቋንቋዎች ተባዝተውና መጽሐፍ ቅዱስ ተተርጉመው ይገኛሉ። ይሁን እንጂ የድርጅትንም ሆነ የግል እምነት ለመግለጽ ሲባል በስም ሆነ በወርቁ ትርጉም የማይገናኝ ፍቺ እየተሰጠ ቀለል ባለ ቋንቋ ወይም አዲስ እትም በመባል የሚወጡት ሁሉ ቅዱሳት መጽሐፍትን መመገብ ሳይሆን ትንቢቶች እየተፈፀሙ መሆናቸውን በዚህ አጋጣሚ ልንረዳውና ልናስተውለው ይገባል። 2ኛ ሄጴጥ. 3:16-18

ትርጓሜ

ሁለት ዓይነት ትርጓሜ ሲኖር ይኸውም:-

1. ነጠላ
2. አንድምታ ትርጓሜ ናቸው።

ነጠላ ትርጓሜ:- ሙሉ ምንባብና ያለምንም ህተታ ከአንድ ቋንቋ ወደሌላ መተርጎም ወይም መመለስ ሲሆን፣

አንድምታ ትርጓሜ:- አንድ ጊዜ ከተተረጐመ በኋላ ይህን የመሰለ ትርጉም አለው እያለ እስከ 10 እና 15 ገጽ በማማረጥ ወይም 1ኛ 2ኛ ብሎ በመተንተን አንድም እያለ የሚያስረዳ ነው:: ሉቃ. 13:18

መጽሐፍ ቅዱስ የሚባለውን የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና፣ ለተግሳፅ፣ ልብንም ለማቅናት፣ የጽድቅንም ሥራ ለመስራት፣ ምክር ያለባቸው መጻሐፍ ሁሉ ነው:: 2ጢሞ.3:15-17 ከእነዚህም ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጽሐፍት በአንድ ላይ ሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ብለን የምንጠራውን እንመለከታለን:: መጽሐፍ ቅዱስ ብሉይና ሐዲስ ኪዳን ተብሎ በ2 የሚከፈል ሲሆን በውስጡ ያሉትንም ቅዱሳት መጽሐፍትንም ቤተክርስቲያናችን ከመሰል እህተ አቢያተክርስቲያን ጋር በሕብረት የምንጠቀምበትና የምትቀበለው 80 አህዱ መጽሐፍ ሲሆን ከሌሎቹ ጋር በእነዚህም ውስጥ የሆኑትን 66ቱን ትቀበላለች ይህም ሲባል የሚቀበሉትን አተረጓጐምና ሀሣብ ትቀበላለች ማለት አይደለም:: 66ት የሚባሉትም 39 የብሉይ ኪዳንና፣ 27 ከሐዲስ ኪዳን ናቸው:: 81ዱ የሚባሉትም 46 ብሉይ ኪዳንና፣ 35 ከሐዲስ ኪዳን ናቸው::

ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን ከምትቀበላቸው ውስጥ አጉድለው አንቀበልም የሚሉት የሚያቀርቧቸው ምክንያቶችና ጥያቄዎች ከነመልሶቻቸው ቀጥለን እንመልከት:-

ጥያቄዎቹ:-

ሀ. አይሁድ ለእነዚህ መጻሕፍት ትኩረት አልሰጧቸውምና፣
ለ. ሐዋርያት ወንጌልንና መልእክታትን ሲጽፉ ከሌሎች የብሉይ መጻሕፍት ሲጠቅሱ ከእነዚህ አልጠቀሱም፣

ሐ. በመጀመሪያዎቹ 3 መቶኛውም አካባቢ የነበሩ የቤተክርስቲያን አባቶች /318ቱ፡ ሰቃውንት/ አልተቀበሏቸውም አልጠቀሱም፣
መ. በራእይ ዮሐንስ 22:18 ላይ ማንም በዚህ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጻሕፍት የተጻፉትን መቅሰፎቶች ይጨምርበታል ማንም በዚህ ትንቢት መጻሕፍት ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጉድል፣ ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር እድሉን ያጐድልበታል:: ስለሚል በማለት ከእውነት የራቀና ማስረጃ የለሽ ሃሣብና ጥያቄ ያቀርባሉ:: ይህን ጥቅስ በጥቂቱ ብናይ እንማራለን::

ጦቢት 4:9 → ከማር. 6:19-20
ዮዲት 8:12 → ከማቴ. 4:12
ጠቢቡ ሰሎሞን 16:26 → ከማቴ. 4:4
ጦቢት 4:16 → ከማቴ. 7:12
ጠቢቡ ሰሎሞን 2:1-9 → ከ1ኛቆሮ. 15:32
ሲራክ 11:18-19 → ከሉቃ. 12:19
ሲራክ 28:2 → ከማር. 11:25፣ ሉቃ. 6:37

ስለዚህም የአባቶቻችንን የሐዋርያት ፈለግ ተከትለንና ምክራቸውንም ተቀብለን እነዚህን መጻሕፍት እንጠቀምባቸው ዘንድ ቅድስት ቤተክርስቲያን ታስተምረናለች:: እንዲሁም «ሐዋርያት ካልጠቀሱባቸው አትጠቀምባቸው» የሚል ሕግ በመሠረቱ የለም ነገር ግን የግድ መጠቀስ አለበት ካልን የመጽሐፈ አስቴር አልተጠቀሰምና ይህንንም ላንቀበለው ነው ማለት ነው?

ይህም ጥያቄ «ሐ» «... ካልዋሉበት» እንዲሉ አይነት ነው:: ምክንያቱም በዚያን ጊዜ የነበሩ የቤተክርስቲያን አባቶች በ81ዱ ቁጥር ካለው መጽሐፍት ይጠቅሱ ነበር:: ለምሳሌ ያህል /የግብፅ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ትምህርተ መለኮት 1ኛ መጽሐፍ በሚለው የቄስ ሚካኤል ሚና መጽሐፍ ገጽ 16/ ካቀረቡት ...ኣኣል፣

መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ሲራክን ቅዱስ አትናቴዎስ ቅዱስ ባስልዮስ እና ቅዱስ ኤፍሬም መጽሐፈ ጥበብን ካቀረቡትም ባስሊዎስና ኤጲፋንዮስ መጽሐፈ ጦቢትን ካቀረቡት ደግሞ የእስክንድርያው ቀለሚንጦስ፣ ባስልዮስ፣ መጽሐፈ ባሮክንም እንዲሁም ቅዱስ አትናቴዎስ፣ ቅዱስ ባስሊዎስና ዮሐንስ አፈወርቅም ይገኙበታል:: ከላይ በተገለጸው መጽሐፍ መነሻነትም ተጠቅመውበታል:: እንግዲህ ለመረጃ ያህል በትንሹ ካየን አባቶች በእነዚህ መጻሕፍት ይጠቀሙባቸውና ይቀበሏቸው እንጂ ከቁጥር አላወጧቸውም::

የመጨረሻውን ጥያቄ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አለማስተዋል ነው እንጂ ግልጽ ነበር:: ይህን ያልንበት በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ብሎ የሚናገረው ለራእይ ዮሐንስ ብቻ ነው:: ምክንያቱም ከላይ እንዳየነው መጽሐፍት በአንድ ላይ የተጠረዙት ከ325ት ዓ.ም ጉባኤ በኋላ ነው:: ይህ ቃል የተጻፈበት ዋናው ምክንያትም መጽሐፍቱ ተሰብስበው ሲጠረዙ ራእይ ዮሐንስ ከ276 ዓ.ም ጀምረው የሮምን ግዛት ለሁለት ሲመሩ በነበሩት ነገሥታት፣ በዲዮቅልጢያኖስና በመክስምያኖስ፣ አማካኝነት ክርስቲያኖች ሲገደሉና መጽሐፍት ሲቃጠሉ ራእይ ዮሐንስም በዚሁ ጊዜ ጠፍቶ /በመቃጠሉ/ ስላልተገኘ ዮሐንስ አፈወርቅ የተባለው የቤተክርስቲያን አባት ለወንጌላዊው ዮሐንስ የተገለጸለት፣ ዳንኤል የናቡከደንፆር ሕልም እንዲገለጽለት ሱባኤ እንደያዘ ዳን. 2:16-19 ሱባኤ ገብቶ ራእይ ዮሐንስ ለወንጌላዊ እንደተገለፀለት እንዲሁ ለዮሐንስ አፈወርቅ ተገለፀለት:: ተገልጾለትም ጻፈ በዚህን ጊዜ ዮሐንስ አፈወርቅ ወንጌላዊ ዮሐንስ ካየው «ይህ ይጐድላል ይህ ተጨምሯል» ብለው እንዳይጨምሩና እንዳይቀንሱ ይህን መልዕክት አስተላለፈ እንጂ የቅዱሳት መጽሐፍትን ቁጥር አልወሰነም ወይም ሌሎችን መጽሐፍት አትቀበሉ አላሉም::

የመጽሐፍ ቅዱስ አመዳደብ

ከላይ እንደተመለከትነው ብሉይና ሐዲስ ተብሎ መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት አበይት ክፍሎች ይመደባል::

፩ ብሉይ ኪዳን ማለት የጥንት፣ የቆየ፣ የመጀመሪያ ውል ስምምነት ማለት ሲሆን የሚያስረዳውም የሰው ልጅ በገነት በደስታ ለመኖር ተፈቅዶለት ሳለ በሕግ ተላላፊነቱ የሞት ፍርድ ተፈርዶበት ለብዙ ዘመናት በመርገም እንደኖረ፣ እግዚአብሔር ከተለያዩ ቅዱሳን ጋር የገባውን ቃል ኪዳን፣ ሕዝብ እስራኤል ከእግዚአበሔር ጋር ስለነበራቸው ግንኙነት ስለሰራላቸው ሕግ ስለገባው ቃል ኪዳን ያስረዳል:: ስለዚህም እነዚህን መጻሕፍት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ስለተጻፉት ቅዱሳት መጻሕፍት ሲባሉ ከቀድሞው አባቶች ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ስለያዙ ደግሞ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ይባላሉ::

፪ ሐዲስ ኪዳን አዲስ ውል፣ አዲስ ስምምነት ማለት ሲሆን በኤርምያስ 31:31 «እነሆ ከእስራኤል ቤትና ከአይሁድ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ጊዜ ይመጣል::» ተብሎ በትንቢት እንደተነገረው ስለአምላክ በተዋህዶ ከድንግል መወለድ፣ ስለአደረገው የሰው ልጆችን የማዳን ጉዞውና በትንቢቱ መሠረት የሐዲስ ኪዳን የሚሆን ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙን በመስጠት አለምን ያዳነበትና የእስራኤል ዘነፍስ /ክርስቲያኖች/ መመሪያ ነው:: ማቴ. 26:26-29፣ ሉቃ. 19:20 ስለዚህም የጥንት ውል በአዲስ ውል ፀና፣ ፍጹምነትን አገኘ፣ ማለት ነው:: «ብሉይን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽመው እንጂ ለመሻር አልመጣሁም» ማቴ. 5:17 ብሎ በሕያው ቃሉ ተናግሯልና::

የሁለቱ ኪዳናት ግንኙነት /አንድነት/

፩ አስገኚው አንዱ እግዚአብሔር በመሆኑ አላማቸውም አንድ ነው ይህ አንድነታቸው ስለዓለም ድህነት በክርስቶስ መምጣት መሆኑን ነብያት በትንቢትና፣ ምሳሌ የገለጹትን ሐዋርያት በትንቢትና በስብከት

መልክ ጽፈውታል። ለዚህ ዓረፍተ ነገር ምሳሌ የምናደርገው ቅዱስ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ 10:1-11 በተናገረው ቃል መሠረት ነው።

፪ ብሉይ መነሻ፣ ሐዲስ መድረሻ ነው። የብሉይ ትንቢቶች ምሳሌዎች በሐዲስ ኪዳን ይተረጐማሉ፣ ለሐዲስ ኪዳንም ብሉይ ይጠቀሳል። አስረጂም ይሆናል። ስለዚህም ሁለቱን በአንድ ላይ አጣምራ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ትጠቀምበታለች።

እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት አድርጋ በመንፈስ እግዚአብሔር የተጻፉ፣ የትውፊት ቅዱሳት መጻሕፍትን ትገለገልባቸዋለች። በእነዚሁ መጽሕፍትም መጽሐፍ ቅዱስን ታስረዳለች፣ ትተረጉማለች።

ተፈፀመ

ምዕራፍ አምስት
ምሥጢረ ተክሊል

ተክሊል ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ. ተክሊል ማለት በቅድስት ቤተክርስቲያን የጋብቻ ሥርዓት የሚፈጽሙበት ካህናት መሽራውንና ሙሽራይቱን በቃል ኪዳ ን አንድ የሚያደርጉበት ትዕዛዘ እግዚአብሔርን የሚያጸኑበት ሕግ ማለት ነው።

ለ. ተክሊል ማለት ክብር ማለት ነው። ምክንያቱም በዚህ ሕግ ሴት የባሏ ክብሩ ናት የተባለች እረዳቱን በቃል ኪዳን የሚቀበልበት ምሥጢር ነው። 1ኛቆሮ. 11:7 ይኸውም ክለለ፣ አከበረ ካለው ግሥ የወጣ ዘር ነው።

- ሥርዓተ ተክሊል መቼ ተጀመረ?

  - ምንም እንኳ ጋብቻ ከአዳምና ከሔዋን ቢጀመርም ሥርዓተ ተክሊል ግን በዘመነ ሐዲስ ከጌታ ልደት ወዲህ ነው።

- በቤተክርስቲያናችን ሕግና ደንብ መሠረት ስንት ዓይነት ሥርዓት ተክሊል አለ?

  - በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት ሁለት ዓይነት ሥርዓተ ተክሊል ይፈፀማል።

    ፩ኛ ለሕጋዊያን /በንጽህና ወይንም በድንግልና ላሉ/
    ፪ኛ ለመዐስባን ከሕግ ለወጡ /ንጽህናቸውን ወይም ድንግልናቸውን ላጐደፉ /ላጐደሉ/ የሚደረግ ሥርዓት ነው።

- ሥርዓተ ተክሊል ያለ ሥጋወደሙ ሊፈፀም ይችላል?

- ሥርዓተ ተክሊል በሥጋ ወደሙ ለተወሰኑት ወይንም ለሚወሰኑ ሰዎች ብቻ እንጂ ለማንኛውም ሰው ሊፈፀም አይችልም

  «ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» ማቴ. 19:5 ባለው ቃል መሠረት ያለሥጋወደሙ የተክሊል ጋብቻ አይፈቀድም አንድ የሚያደርጋቸው እርሱ ነውና:: ፍትሀነገሥት አንቀጽ 24 ቁጥር 899

• ጋብቻ ፈጻሚዎች ንጽህናቸውን አጉድፈው በንስሀ ሲመለሱ ሥርዓተ ተክሊል ይደርስላቸዋልን?

- ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ልጆች በንስሀ ታጥበው ከመጡላት አልቀበልም አትልም:: ሉቃ. 15:11 ባዝኖ የነበረው ልጅ ጥፋቱን አውቆ ወደ አባቱ በተመለሰ ጊዜ አባቱም አልፈልግህም አላለውም ይልቁንስ በመምጣቱ እጅግ ደስ ብሎት ተድላ ደስታ አደረገ እንጂ:: ስለዚህም የአደፈውን ሰውነት በንስሀ ሳሙና ታጥቦ ካጸዱ በኋላ ከመጡ ከላይ በተገለጸው መሠረት በሁለተኛው ደረጃ ማለትም ለመዐስባን የተገለፀው ሥርዓተ ተክሊል ይደርስላቸዋል:: «ንስሀ ዘማዊውን ድንግል ታደርጋለችና»::

• ሥርዓተ ተክሊል አይደገምም እንዲህ ከሆነ አንድ ሰው በሥርዓተ ተክሊል አግብቶ አንደኛው በሞትም ሆነ በሕግ ፍቺ ቢለያዩ እንደገና ለማግባት አይችልም? ከአገባስ በሥጋ ወደሙ ነው? ወይንስ በተክሊል?

- ጋብቻው በመሞትም ሆነ በሕግ ፍቺ ቢለያዩ ሕጉን ጠብቆ ማግባት ይቻላል:: እንዲህም ሲባል:-

፩ኛ በተክሊል ያገባው ሰው በሥጋ ወደሙ አንድ የሆነች ሚስቱ በሞት ብትለየው ሕጉን

ሳያፈርስ በንጽህናቸው እንደገና ማግባት ይችላል::

፪ኛ በሥርዓተ ተክሊል ተጋብተው በሥጋወደሙ አንድ ከሆኑ በኋላ ከሁለት አንዳቸው ከሕግ ወጥተው ቢገኙ ወይም ቢያመነዝሩ አጥፊው ወገን ይመለስ ዘንድ በመጀመሪያ ይመከራል ቀጥሎም ለቤተክርስቲያን አባቶች ተነግሮ እንደገና አልሰማ ቢል ሕጉን ጠብቆ ያለው ከሕግ እንዳይወጣ የቤተክርስቲያን /ካህናት/ ፍቺውን እዲያፀድቁ ይደረጋል ከዚያም ያሰው ማለትም የበደለው ወገን ማጥፋቱን አወቆ በንስሀ ከተመለሰ አንድ ይሆናሉ ካልተመለሰና በጥፋቱ ላይ ጥፋት የሚጨምር ከሆነ ግን እንደሞተ /እንደሞተች/ ተቆጥሮ በሕግ ያለው ሰው እንደገና ማግባት ይችላል:: ሮሜ. 7:2-3

፫ኛ ሥርዓተ ተክሊል የማይደገም ስለሆነ ጋብቻው በቅዱስ ቁርባን ወይም በሥጋወደሙ ይፈፀማል::

• ንጽህና የጐደለው ሰው ንጽህናውን ካላፈረሰው ሰው ጋር ተማምነው ጋብቻውን ቢፈቃቀዱ ተክሊሉ ይፈፀምላቸዋል? ከተፈፀመስ በእንዴት አይነት ሁኔታ ይፈፀማል?

- ሥርዓተ ተክሊሉ ይፈፀምላቸዋል አፈጻፀሙም እንደሚከተለው ይሆናል:: መጐናጸፊያውን በአንድ ላይ ይለብሱታል:: ከዚህ በኃላ የሥርዓተ ተክሊሉ ፀሎት ይፈፀማል ከተክሊሉ የበለጠ ሁለቱንም ሙሽሮች አንድ አካል የሚያደርጋቸው ቅዱስ ቁርባን ነውና ሥጋ ወደሙን መቀበል ይኖርባቸዋል::

- ሁለት ዓይነት ሥርዓተ ተክሊል አለ ከተባለ በሁለቱም ጊዜ የሚደረገው ወይም ሙሽሮቹ በራሳቸው ላይ የሚደፉት አክሊል ይለያያልን?

- በሁለቱም ሥርዓተ ተክሊል ጊዜ ሙሽሮቹ የሚደፉት አክሊል የተለየ አይደለም ነገር ግን በሁለቱም ጊዜ የሚደረገው የተክሊል ፀሎት ይለያያል ስለዚህም የሚለያቸው ተክሊል ሳይሆን የሚደርሰው ሥርዓተ ፀሎት ነው::

- ያለሥጋወደሙ ተክሊል አይጸድቅም ካልን አንዳንድ አብያተ ቤተክርስቲያናት ተክሊልን ያለቁርባን ሲያደርሱ ይታይል ይህም ሕግን መጣስ ስለሆነ የሚያስጠይቀው ካህኑን ነው? ወይስ ሙሽሮቹን ነው?

- በሁለቱም ወገን ጥያቄ አለባቸው

<u>ካህኑ</u>:-

ሀ. ተክሊል ያለሥጋወደሙ እንደማይከብር ሲያውቅ፣
ለ. በይበልጥም ከተክሊሉ ይልቅ አንድ አካል የሚያደርጋቸው ሥጋ ወደሙ መሆኑን ሲረዳ ይህንን ሳይፈፅም በመቅረቱ፣ ይጠየቃል::

<u>ሙሽሮቹ</u>:-

ሀ. አስቀድመው ሲመጡ ተለያይተው እንጂ አንድ አካል ሆነው አልመጡም ማለትም ሁለቱ አካል የሆኑት ሙሽሮች አንድ አካል የሚሆኑት በሥጋ ወደሙ ሲሆን ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ካልመጡ አንድ አካል አልሆኑምና፣

ሲሆን ሥጋ ወደሙን ለመቀበል ካልመጡ አንድ አካል አልሆኑምና፣

ለ. መሀላውን ስላልፈፀሙ ማለት አንድ አካል ነን ብለው የሚምሉትን መሀላ ደፍረው በመቀበላቸው ጥያቄ ይኖርባቸዋል::

- በሥርዓተ ተክሊል ከተጋቡ ሙሽሮች መካከል አንደኛው በሞት ቢለይ ሕጉን ጠብቆ እንደገና በሥጋ ወደሙ መጋባት ይችላል? እንዲህ ከሆነ ሁለተኛ ጊዜ እንዲህ ቢያጋጥመው ለሦስተኛ ጊዜ ማግባት ይችላል? ይህስ ከሆነ እስከ ስንት ጊዜ ማግባት ይችላል?

- እንዲህ ዓይነቱ የሞት አጋጣሚ ቢያገኘው በዝሙት ጾር የሚመጣውን ፈተና ከቻለ ለሁለት ጊዜ ያደረገው ይበቃዋል:: ይህን ፈተና ካልቻለ ግን ለሦስተኛ ጊዜ ይፈቀድለታል ከዚህ በላይ ግን እራሱን አሳልፎ ለዝሙት ሰጥቶ ከእግዚአብሔር ሕይወት መውጣት ይመጣልና አይፈቀድለትም::

- ማንኛወም ወንድ ወይም ሴት ራሳቸውን ሳይችሉ በተክሊል ጋብቻ የሚሆናቸውን ባል ወይም ሚስት መምረጥ ይችላሉን?

- በወላጅ ፈቃድ ከሆነ ወይንም የወላጁ ችግር ካለ ለምሳሌ የወንዱ ወይም የሴቷ ወላጆች በሞት የተለያዩ ከሆነ ለመረዳዳት ይቻል ዘንድ ራሳቸውን እስኪችሉ በቤተሰብ እቅፍ ስር ሆነው ይድራቸዋል ያለበለዚያ ግን እንዲህ ዓይነቱ ከባድ ችግር ከሌለ በስተቀር እራስን ሳይችሉ መመራረጥ አይቻልም::

- በቤተክርስቲያናችን ሥርዓትና ደንብ መሠረት የወንድና የሴት በር መግቢያ ለብቻ መሆን አለበት ተብሎ ተወስኗል ይህ ሆኖ ሳለ አብዛኛውን ጊዜ ተክሊል

- ሴቷ ሙሽራ በወንድ መግቢያ መግባት የለባትም ወንዱም ሙሽራ እንዲሁ ይህን ከጣሱ ሥርዓትን ያፋልሳሉና በወንድ በር መግቢያ መግባት የለባቸውም ወንዱ ሙሽራ ከእነአጃቢያቸው በወንድ በር መግቢያ በኩል ሴቷም ሙሽራ ከእነአጃቢዎቿ በሴት በር መግቢያ በኩል ትገባና የቤተክርስቲያን በር ወይንም ሥርዓተ ተክሊሉን የሚያደርሱት አባቶች በአዘጋጁት ወንበር በአወደምህረቱ ላይ ካህናት አለበቸው:: ሲወጡ ግን በአንድ ላይ መገናኘት በሥጋ ወደሙ አንድ ሆነዋልና:: ሆነው ነው

- ሥርዓተ ተክሊል ለመፈፀም /ለማድረስ/ የተጋቢዎቹ ዕድሜ ከስንት በላይ መሆን አለበት?

  - ተክሊሉን ለመፈፀም ወንድ ከ18ዓመት በላይ ሴት ደግሞ ከ15 ዓመት በላይ መሆን አለባቸው:: ይኸውም ተጋቢዎቹ ትዳራቸውን በትክክል የመምራት ኃላፊነት የአዕምሮ ብስለት ሁኔታ ሲኖራቸው ነው::

- አበው ሲያስተምሩ ለትዳር፣ ለክህነትም፣ ሆነ ለምልኩስና ሕይወትን ለወደፊቱ ውሣኔ ለመስጠት የአንድ ሰው ዕድሜ 30 ዓመት መሆን አለበት ይላሉ ይህ ከሆነ ለወንድ 18 ዓመት መሆን አለበት ካለ ይህ አይፈርስምን?

  - በጥንት ጊዜ የሰው ልጆች ዕድሜ በጣም እረዥምም ነበር እስከ 400 ዓመትና ከዚያም በላይ ይኖሩ ነበር ስለዚህም 30 ዓመት ተባለ:: ዛሬ ግን የሰው ዕድሜ እጅግ ቢበዛ 120 አሊያም 70 እና 80 ስለሆነ 18 ዓመት ተባለ::

- ሰዎች በሥርዓተ ተክሊል ከመወሰናቸው በፊት ምን ማድረግ አለባቸው?

- ሰዎች በሥርዓተ ተክሊል ከመወሰናቸው በፊት ምን ማድረግ አለባቸው?

  - ማንኛውም ሰው በሥርዓተ ተክሊል ከመወሰኑ በፊት

    ሀ. የሃይማኖት ትምህርት በደንብ ጠንቅቆ ማወቅ
    ለ. ሥርዓተ ቤተክርስቲያን መማር
    ሐ. ለጋብቻ እስኪደርሱ ድረስ እራሳቸውን በራሳቸው መምራት
    መ. አብረው ሲሆኑ ልዩ የሆነ ጨዋታ ማለትም ግላዊ ግንኙነትን ሳይፈጥሩ ሁሉንም ነገር በሕዝብ ፊት ወይም በሰው ፊት ማከናወን አለባቸው::

- ከሕግ እንዳይወጡ የሚያደርጉት ጥንቃቄ እንዴት ነው?

  - ይህ የጋብቻ /የሥርዓተ ተክሊል/ ጉዳይ ለሕይወታቸው ወሳኝ ነውና የፀሎት ልምድ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል ጠዋት ሲነሱ ማታ ሲተኙ በፀሎት ማመልከት አለባቸው::

«ወደፈተና እንዳትገቡ ትጉና ፀልዩ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው» ማቴ. 26:41

ከሠርጉ ቀን አስቀድሞ ከቤተክህነት የተሰጣቸውን ማስረጃ በአቅራቢያቸው ላለው የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ አቅርበው ቃል ኪዳናቸውን በቤተክርስቲያን መፈፀም ይገባቸዋል:: በዚሁ ቀን ሙሽራውና ሙሽራይቱ ከነዘመዶቻቸው በቤተክርስቲያን ተገኝተው በቃል ኪዳን ሕግ መሠረት የቀለበቱን ሥነ-ሥርዓት ይፈፅማሉ:: በመተጫጨት የሰጡትንም የፈቃድ ቃል በመሀላ ያፀናሉ በሥነ-ሥርዓቱ ቀንም ከሌሊት በዘጠኝ /9/ ሰዓት ሙሽራው ከዘመዶቹ በደቡባዊ መዓዘን /መግቢያ/ ሥፍራ ሥፍራቸውን ይዘው ይገባሉ ከዚያ በኋላ በምዕራብ በኩል ከመካከለኛው ክፍል ማለት ከቅድስቱ በቤተመቅደሱ ፊት ለፊት ካለው

አውደምህረት ላይ ሊቀ ዲያቆናት ሙሽራውና ሙሽራይቱን ሥርዓተ ተክሊል የሚፈጽሙበትን ምንጣፍ አንጥፎ ለሁለት የሚሆን አንድ አግዳሚ ወንበር እንዲሁም አንድ ጠረጴዛ ሙሽሮቹ ቃል ኪዳናቸውን የሚፈጽሙበትንና ሥጋወደሙን አንድ ሆነው የሚቀበሉበትን መጐናጸፊያ፣ የሚቀቡትን ዘይት፣ የሚያቀዳጃቸውን አክሊላት ያዘጋጃሉ ከዚህ በኋላ ሙሽራውና ሙሽራይቱ ስፍራቸውን ይዘው ይቆማሉ ካህናቱ ሥርዓተ ተክሊሉን ይፈጽማሉ በመጨረሻም አስቀድሰው ሥጋ ወደሙን ተቀብለው ቃልኪዳናቸውን በሥጋ ወደሙ ያፀናሉ ይፈጽማሉ:: ያለቁርባን ግን ተክሊል እንደተክሊል ሆኖ ሊቆጠር አይችልም::

የቃል ኪዳናቸው ሥርዓት በሚፈፀምበት ቀን ሙሽራውና ሙሽራይቱ ከዘመዶቻቸውና ከወዳጆቻቸው ጋር ወደቤተክርስቲያን መጥተው ሙሽራው በቄሱ ቀኝ ሙሽራይቱ በቄሱ ግራ ይቆማሉ ከዚህ በኋላ ቄሱ መጽሐፈ ተክሊሉን በመያዝ ሥርዓቱን ያደርጋል::

በመጀመሪያ ከፀሎቱ አስቀድሞ ሁለቱን አንድ አካል የሚያደርጋቸውን እግዚአብሔርን ያመሰግናል በመቀጠልም ሙሽራው የሙሽራይቱን ቀኝ እጅ በቀኝ እጁ ይዞ ቃል ኪዳን እንዲገባ ያደርጋል:: ሙሽራይቱም እንዲሁ ታደርጋለች ዘፍ. 2:23 ይህ እንደበቃ ካህኑ በቀለበቶቹ ላይ የሚፀለየውን ፀሎት ይፀልያል ይህን ሲያደርስ ከዲያቆናት ጋር በመሆን ነው ይህን ፀሎት እንደፈጸመ ቀለበቶቹን በመስቀል ይባርካል እንዲህ እያለ በዚህ ቀን ተሰብስበው በፀሎት ከኛ ጋር በክብር ያሉትን አባቶቻችንና ወንድሞቻችንን፣ እናቶቻችንንና እህቶቻችንን ባርካቸው፣ አምላክን በወለደች በእመቤታችን በድንግል ማርያም አማላጅነት ወንዶችንም ሴቶችንም ባርኮችህን የምዕመናን አንድነት አጽና ካለ በኋላ ቄሱ ቀለበቱን አንስቶ ለሙሽራው ይሰጠዋል ሙሽራውም ለሙሽራይቱ በግራ እጅ በአራተኛይቱ ጣቷ ያድርግላት ሙሽራይቱም እንዲሁ ታድርግለት በዚሁ ጊዜ ቃል ኪዳኑን ይቀበላሉ ምስክራቸውን እግዚአብሔርን በማድረግ ዘፍጥ. 24:22

ዘይት ይቀባቸዋል ይህ ተፈጽሞ ካለቀ በኋላ በአክሊሎቹ ላይ እንዲሁ የአክሊል ፀሎት ይፈፀማል አክሊሎቹንም በመስቀል ይባርካል ከባረከውም በኋላ ካህኑ አክሊሉን ያደርግላቸዋል:: ይህ እንደተፈፀመ ሙሽራውና ሙሽራይቱ በመሰዊያው ፊት ለፊት ይቆማሉ ቄሱም የምልጃ ፀሎት ይፈፅምላቸዋል የምልጃ ፀሎት እንዳበቃ ሙሽራውንና ሙሽራይቱን እጅ ለእጅ በመስቀል እያማተበ ይባርካቸዋል ከቡራኬው በኋላ ፀሎተ ቅዳሴውን ተካፍለው ሥጋውን ደሙን ይቀበላሉ ሥርዓተ ቅዳሴው እንዳበቃ ካህኑ ለሁለቱም የምክር ቃል ይሰጧቸዋል::

ምሳሌ:-

<u>ቀለበቱ:-</u> የወርቅ መሆኑ ንጽህናቸውን፣ ቅድስናቸውን፣ ሃይማኖታቸውን ሲገልጽ፤

<u>ክብነቱ:-</u> ባል በሚስቱ ሚስትም በባሏ መታሰራቸውን ያስረዳል::

<u>መጐናፀፊያው:-</u> አንድ ክብር የሚወርሱ መሆናቸውን፣ ሁለትነት ቀርቶ አንድ አካል ለመሆናቸው ሲያመስጥር ነው::

<u>ተክሊል:-</u> አንድ ክብር የሚወርሱ መሆናቸውን ሲገልጽ ነው::

<u>ዘይቱ:-</u> ጸጋን እንደሚያገኙ፣ የተባረከ ዘር እንዲያገኙ፣ በረከት እንዲያስጣቸው፣ አጋንንት እንዲርቁ የሚያደርግ ምሳሌ ነው::

<u>ማጠቃለያ</u>

፩ኛ ጋብቻ ለመረዳዳት፣ ለመተጋገዝ ከልዑል እግዚአብሔር ለሰው የተሰጠ ሕግ ነው:: ዘፍ.2:20

ማጠቃለያ

፩ኛ ጋብቻ ለመረዳዳት፣ ለመተጋገዝ ከልዑል እግዚአብሔር ለሰው የተሰጠ ሕግ ነው:: ዘፍ.2:20

፪ኛ ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንድ አካል ናቸው ሁለት አይደሉም በዚህ ምክንያት ወንድ አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር ይዋኃዳል፣ ይተባበራል፣ አንድ ይሆናል:: ዘፍ. 2:24. ማቴ. 19:5

፫ኛ ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ መፋታት ክልክል ነው እግዚአብሔር አንድ የደረጋቸው ስለሆነ ሰው ሊለያያቸው አይችልም ሚልኪያስ 2:14-16፣ ማርቆስ 10:2-9

፬ኛ ጋብቻ አንድ በአንድ ይፀናል እንጂ ሁለተኛ ቁጥሩን አይነካም ማለት ለአንድ ወንድ አንድ ሴት ለአንዲት ሴት አንድ ወንድ ነው እንጂ ከዚያ በላይ አልተፈቀደም ባል ከሚስቱ ሚስትም ከባሏ መተላለፍ የለባቸውም ባል ከሚስቱ ብቻ ሚስትም በባሏ ተወስነው ይኖራሉ:: 1ኛቆሮ.7:2

፭ኛ ወንድ ለሚስቱ የሚገባትን ሁሉ መጠበቅ፣ ማድረግ ይገባዋል ሴትም ለባሏ የሚገባውን መጠበቅ ማድረግ ይገባታል:: 1ኛቆሮ. 7:3

፮ኛ ሴት ባሏ ያዘዛትን ልትፈጽም እንጂ በባሏ ላይ የሌላ ትዕዛዝ ፈጻሚ ልትሆን የወደደችውን ልታደርግ በራሷ ላይ ስልጣን የላትም በሷ ላይ የማዘዝ ስልጣን ያለው ወንዱ ነው እንዲሁም ወንድ በሚስቱ ላይ የሌላይቱ ታዛዥ ሊሆን ከሌላይቱ ፈቃድ ሊፈጽም በራሱ የማዘዝ ሥልጣን የለውም በራሱ ላይ ሥልጣን ያላት የምታዝበት ሚስቱ ናት:: 1ኛቆሮ. 7:4

፯ኛ ለጸምና ለፀሎት ከተወሰነ ቦታና ጊዜ በቀር ባልና ሚስት መለያየት የለባቸውም ሰይጣን ድል እንዳይነሳቸው ተጠባብቀው መኖር ይገባቸዋል:: 1ኛ ቆሮ. 7:1 ጀምሮ

፰ኛ ቤተክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትታዘዝ ሚስትም አሳዳሪዋ ስለሆነ ለባሏ መታዘዝ ይገባታል:: እንዲሁም ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት እራሱንም አሳልፎ ለሞት እንደሰጠላት ሥጋውን ደሙን እንደመገባት እንደዚሁ ውድ አካሉ ናትና ሚስቱን መውደድ መርዳት ይገባዋል:: ኤፌሶን 5:22-23

፱ኛ ለሴት በሥጋዊ ጌጥ ከማጌጥ ይልቅ ለባሏ በመታዘዝ ባሏን በመፍራት በመውደድ ጌታዬ እያለች ሳትፈራ ሳታፍር መልካም ሥራ በመሥራት ንጹህ ልቦናዋን ገልጾ እያሳየች በትህትናና በመንፈሳዊ ኃይል በመሆን ብታጌጥ ይበልጣል:: ወንድም በምድር ክብር ብቻ ሳይሆን የሰማይ ሕይወትና ክብር ተሳታፊው ስለሆነች ሚስቱን ሳይንቅ እንደዓይን ብሌን ይጠብቅ:: ባልና ሚስት አንድ ልብ አንድ አፍ ሆነው በመተማመን መኖር ይገባቸዋል እንጂ በሀሣብ መለያየት አለመተማመን የለባቸውም:: 1ኛቆሮ. 3:1-9

፲ኛ ባልና ሚስት በሞት ካልሆነ በስተቀር መለያየት የለባቸውም በሞት መለያየት ቢደርስባቸው ግን ወደኋላ የቀረው ንጽህናውን ጠብቆ መኖር የማይቻለው ከሆነ ሁለተኛ ማግባት ይቻላል:: ሮሜ. 7:2-3

፲፩ኛ ባልና ሚስት በድንገት ግጭት በእለት ቁጣ ቢለያዩ ይታረቁ አንታረቅም ቢሉ ግን በእየራሳቸው ንጽህናቸውን ጠብቀው መኖር አለባቸው እንጂ በየራሳቸው ሌላ ማግባት የለባቸወም:: 1ኛቆሮ. 7:16

፲፫ኛ ሥጋዊ ተዛምዶ መንፈሳዊ ተዛምዶ እስከ ሰባት /7/ ትውልድ ማግባት ክልክል ነው::

ሀ. ወደላይ የአባቱንና የአያቱን የቅድመአያቱን ሚስት ልጅዋን፣ እህቷን፣ እናቷን አያገባም::

ለ. ወደታች ልጅዋን፣የልጅ ልጅዋን ወይም የልጅዋን የልጅ ልጅ፣ የሚስት ልጅዋን፣ እህቷን: እናቷንና አያቷንም አያገባም::

ሐ. የወንድም፣ የእህት፣ የአክስትና የአማትና የምራት: የዋርሣና አይት/የወንድም የአጐት፣ ሚስት/ የጋብቻ ክልክልነት እንደዚህ ነው:: ዘሌ. 6:21

የሚስጢረ ተክሊል የሥርዓቱ አፈጻጸም ከብዙ በጥቂቱ በዚህ ተፈፀመ::

ምዕራፍ ስድስት

በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

የዓለም አባት የዓለም መድኃኒት ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእናቱ ጋር ይክበር ይመስገንና በፈቃዱና በቸርነቱ በዚህ ዓመት ማለትም በ1992 ዓ.ም ከላሊበላ ከተማ 5:00 ሰዓት ያህል ራቅ የሚለውን የቅዱስ ይምርሐነክርስቶስን ታሪክ እግዚአብሔር በመረጣቸውና በቀደሳቸው ቅዱሳን አባቶቻችን ነገሥታት ላይ አድሮ የሠራቸውን እፁብ ድንቅ አብያተ ክርስቲያናት /ቤተ መቅደሶች/ በቦታው ተገኝተው ላላዩትና እድሉ ገጥሞአቸው አይተው የታሪኩን ፍንጭ ያልተረዱ ካሉና ቦታውንም ያላዩ ካሉ እንዲያዩ በዚህ አጋጣሚ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከአባቶች ያገኘነውን የቅዱሳን ቦታ እውነተኛ አመሠራረት በእግዚአብሔር ቸርነትና አጋዥነት ከብዙ በትንሹ ለማቅረብ እንሞክራለን::

ለጊዜው እግዚአብሔር አምላክ በቅዱስ ላሊበላ ላይ አድሮ ስላነጻቸው አሥር ቤተ መቅደሶች የአምላክ ፈቃድ በሆነ ጊዜ እስክምናዘጋጅ ዛሬ በዚህች አጭር ጽሑፍ ለማስተዋወቅ የምንሞክረው ከቅዱስ ላሊበላ ቤተ መቅድስ በስተስሜን ምዕራብ በሚገኘው ጉንደር በአቅራቢያነት ስለሚያዋስነው ስለ ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ቤተ መቅደስ ይሆናል:: ይህንን የቅዱስ ይምርሐነን ታሪክ እና የቦታውን አመሠራረት የነገሩንና በስፋት ያስረዱን በአሁኑ ሰዓት በቦታው ላይ የሚገኙት በጉጃም በማስተማርና የምንኩስና ሥርዓትን ለሚፈጽሙ ምዕመናን ግልጋሎትን በመስጠት እና ቤተክርስቲያንን በማገልገል ላይ የሚገኙትን ቀደምት አባት አባ ወልደአረጋዊ ይባላሉ:: ትክክል ዕድሜአቸውን ባናውቅም በንግሥት ዘውዲቱ ጊዜ ጀምሮ የነበሩ መሆናቸውን የገለጹልን አባት በዚህች ቦታ ተወልደው እንዳደጉ ይናገራሉ:: እንደሳቸው አባበልም በቤተክርስቲያናችን ሥርዓት በቆሞሳት ማዕረግ ያሉ መሆኑንም ገልጸውልናል::

አባ ወልደአረጋዊ በአሁኑ ሰዓት በአይናቸው ችግር ያለ ረዳት ለመንቀሳቀስ ስለተሳናቸው በመሪ የሚንቀሳቀሱ ሲሆን በዕድሜአቸው መግፋት የመጣ ይመስላል ቀና ብለው ለመሄድ የተሳናቸው ቢሆኑም እግዚአብሔር በለገሳቸው የዕድሜ ጸጋ ለአካባቢው ምዕመን ወንጌልን በማስተማርና የሚያውቁአቸውን ገድል ቅዱሳን እና ቦታዎች አመሠራረት ባገኙ ጊዜ ሁሉ ታሪኩን በማስተላለፍ የቅዱሳን ገድል ከማስማትና ከማሳወቅ ወደኋላ የማይሉ ትልቅ የሃይማኖት አባት ናቸው:: እኛም በቦታው በተገኘን ጊዜ ከልጅነት ጀምሮ ስላገለገሉት እና ስለሚወዷት ገዳም ስለ ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ የነገሩንን ቃል በቃል በማስታወሻ ይዘን ታሪኩን ለሚያውቁት እንድናዳርስ የቅዱስ ይምርሐነክርስቶስን ገድል ሁሉም እንዲያውቀው ካለን ከልብ የመነጨ ፍቅር በእግዚአብሔር ስም ቃል ስላስገቡን እኛም እንደሰማነው የሃይማኖት ፍቅር ያለው ሁሉ እንዲሰማውና እኛም በአቅማችን የገባነውን ቃል በመጠኑ ፈጻሚ እንድንሆን በመድኃኒዓለም ቸርነት በእመቤታችን አጋዥነት በዚህ መልኩ አቅርበነዋል::

ከዚህ በተጨማሪ ልንገልጽ የምንፈልገው ይህንን የቅዱስ ይምርሐነክርስቶስን ገድል ከብዙ በጣም በጥቂቱ ለአቀራረብ እንዲያመች ስናቀርብ ዋናው ዓላማው ቦታውን እግዚአብሔር በፈቀደ ሰዓት እስክንረግጠው ይህን ገድሉን አንብበን በቦታው ለመገኘት በሃሳባችን የምንጓጓ እንኳን እንደተገኘን ይቆጠርልናል:: ለዚህ የጽሁፍ ጥራዝ መግዣ የምናወጣው ብር ተሰብስቦ ዕጣን፣ ጧፍ፣ ሻማ፣ ዘይት /መብራት/ ወ.ዘ.ተ. ተገዝተው ስለሚላኩበት መብዓውን ላቀረበ ለሚለው ቃልኪዳኑ በቦታው ተገኝተን እንዳቀረብን ይሆንልናል:: የምናደርገውን ሁሉ በፍጹም ዕምነትና ሃይማኖታዊ ፍቅር እንደሁም ለቅዱሳን ባለን ጥልቅ አክብሮት ይሁን:: ይህ ጽሑፍ በእጃችሁ ገብቶ የምታነቡ ምዕምናን ሁሉ በተቻላችሁ መጠን ለመንፈሳዊ ወንድሞቻችሁ፣ እህቶቻችሁ፣ የቅዱሳንን አባት ገድል እንዲያውቁ እንድታደርጉ በልዑል እግዚአብሔር ስም እንለምናችኋለን:: እናንተም የቅዱሳን አባት በረከት

ያድርባችኋልና ለሃይማኖታችንም ጥንታዊነት በዓይነ ሥጋ የሚታይ መረጃ ነውና::

ለዚህ ጽሁፍ ማዘጋጃ የሚያስፈልገው ቁሳቁስ ሁሉ በእግዚአብሔር ቸርነት ተሟልቶ ለዚህ ስለበቃ ለመድኃኒዓለምና ለእመቤታችን ምስጋናና ክብር ይሁን አሜን::

የቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ገዳም ከላሊበላ ከተማ ለበረታ ተጓዥ የ5:00 ሰዓት መንገድ ሲሆን እንደየአቅሙ አዛውንቱም፣ ወጣቱም፣ ወፍራሙም፣ ቀጭኑም፣ በሽተኛ ውም ሁሉንም በቸርነቱ ያደርሰዋል:: ዋናው የልብ መሻት ነውና:: የደከመውም እያረፈ በዝግታ ተጉዞ፣ ሙሉ ቀንም ቢወስድበት ከደጅ ሳይደርስ አያድርም እንደውም ከቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ገድል እንደተረዳነው ጌታችን ለቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ በሰጠው ቃል ኪዳን አንተን ብሎ የሚመጣውን መንገደኛ ከመንገድ አላስድርብህም ብሎታልና ሲመጣም ሆነ ደርሶ ሲሄዱ ከመንገድ ካልፈቀደበት አያሳድርም ይባላል:: ከዚህ አባባል የተነሳ ይመስላል ብዙ ሰዎች ካለማጤን ከቦታው ላይ አላሳድርብህም ነው ያለውና ማደር አይፈቀድም እያሉ ተሳልመው ወዲያው ይወጣሉ፣ አያድሩም:: ነገር ግን በቦታው ያደረ ትልቅ በረከት እንዳለውና እንዲያውም እንዲያድር እንጂ እንዳያድር ግዝት የለውም ተብለናል:: መጥተው ቦታውን ረግጠው ሳያድሩ በሚወጡት እንደሚያዝኑም በቦታው ያሉ አባቶች ተናግረዋል::

ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ማነው?

ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ከ3ቱ የጥንታዊ የኢትዮጵያ ነገሥታት /ወንድማማቾች/

1. ግርማ ሥዩም
2. ዛን ሥዩም
3. ጠንጠውድም

ከሚባሉ የግርማ ሥዩም ልጅ ነው። ቅዱስ ላሊበላ ከዛንሥዩም የሚወለድ ሲሆን ለቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ የአጐት ልጅ ነው። ከቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ የነገሠውም አርባ ዓመት ነው። ዘመኑም ከገድሉ እንደተረዳነው የነገሰበት /1036-1076/ ነው።

ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ከናቱ ማህፀን ሳለ በጌታ የተመረጠ ነበርና እናቱ ወልዳው ሳለ ከመልኩ ማማር የተነሳ ግማሹ ንጉሥ ይሆናል፣ ግማሹ ካህን ይሆናል ወ.ዘ.ተ እያሉ ያዩት ሁሉ ቢያስጨንቋት እናት ናትና ደነገጠች።

አይን ይወጋብኛል ብላ ተጨነቀች። የዚህን ሕፃን ምሥጢር የሚፈታ የተማረ፣ መጽሐፍ የሚያውቅ፣ የሃይማኖት ዕውቀት የሚተረጉም /በወቅቱ አዋቂ የተባለውን/ አምጡልኝ እያለች ብትማፀን ጳጳስ አመጡላት። ጳጳሱም በመልኩ ማማር እየተደነቀ ወደ ሕፃኑ ሲባርከው ቢጠጋ ካህኑ ላይ ያለው መንፈሳዊ ኃይል ተገልጾለት እኔ ኃጢያት የወረሰኝ ደካማ ነኝና እሱ እኔን ይባርከኝ እንጂ እኔስ ልባርከው አይገባኝም አለ ሕፃኑም በእግዚአብሔር ፈቃድ ጳጳሱን ባረከው።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ዝና ታወቀ። እናቱም 40 ቀን ሲሞላው ጳጳሱን እንዲያጠምቁለት ብትለምናቸውም የሰው ሳይሆን የእግዚአብሔር ትዕዛዝ እንደደረሳቸው ተናግረው ለሕዝቡም የሕፃኑን መመረጥ እየነገሩ የእግዚአብሔርን ጥበብ እያደነቁ አጥምቀው ሜሮን ቀብተው ሥጋ ወደሙን አቀብለው ለእናቲቱም እንድታጠባው ቢሰጧት እምቢ አለ። እናቲቱም አይን ወግቶት ነው ብላ ተጨነቀች። እሱ ግን ዕጣ ፈንታው ከምድራዊ እህል ውኃ አልነበረምና የይሥሐቅ፣ የያዕቆብ፣ የእስራኤል አምላክ ይመስገን ብሎ በዘጠኝ ሰዓት ለእናቱ ሲል በእግዚአብሔር ፈቃድ ጡት ጠባ።

ቅዱስ ይመርሐነክርስቶስ ገና ሳይወለድ በጊዜው ንጉሥ የነበረው አጐቱ ጠንጠውድም ነበርና ትንቢት ተናጋሪዎችን እየሰበሰበ መንግሥቱን የሚወርሰው ማን

እንደሆነ ሲያስጠይቅ ይምርሐነክርስቶስ ይባላል ቢሉት ኢንዲህ ያለ ስም በኛ ግዛት ውስጥ የለም። ልጄነውን? አላቸው አይደለም የወንድምህ ልጅ ነው ገና በእናቱ ማኅፀን ነው ያለው አልተወለደም አሉት። ንጉሥም ልጆቼ እያሉ እንዴት መንግሥቴን ይወርሳል ብሎ ቅናትና ትዕቢት አደረበት።

መወለዱንም በሰማ ጊዜ ጌታችን ከአመቤታችን ስለመወለዱ ትንቢት እንደተነገረለት ሄሮድስም ትንቢቱን ፈርቶ መንግሥቴን ይወርሳል ብሎ እንዳሳደደው ንጉሥ ጠንጠወድም ሕጻኑን ልየው መንግሥቴን የሚወርሰውን ድንቀኛውን ሕጻን ልየው ብሎ አስመጣው ሕፃኑም አፍንጫው የገነት ተክል የመሰለ፣ ከአፉ የሚወጣው መዓዛ የሚጣፍጥ፣ ዓይኖቹ ያማሩ፣ ውብ ልጅ ነበርና የሕፃኑን መልክ አይቶ ማማሩ ቡያጓጓውም መንግሥትህን ይወርሳል ተብሏልና መጥፎ ሀሣብ በልቦናው አደረበት ሊገድለውም አሰበ። ከመወለዱ በፊት ትንቢቱን የተናገሩትን ሰብስቦ አትግደለው በእግዚአብሔር ዘንድ በነፍሱ ትጠየቃለህ ነገር ግን መንግሥትህን አንዳያገኝ እዚያው ገጠር ከእናቱ ዘንደ መልሰው። «ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተውም» እንዲሉ ጥቂት ቀናቶች ከሰነበተ በኋላ ሰይጣንናዊ ሀሣቡን ዲያቢሎስ ቀሰቀሰበት ሊገድለውም ቆረጠ አንዳንድ አማካሪዎቹም ላይ ሰይጣን አድሮ ሕጻኑ ተማረም አልተማረም ትንቢቱ የእግዚአብሔር ነውና መፈጸሙ አይቀርም ይህን ሕፃን ከምድረገጽ አስወግደው አሉት። ንጉሥ ጠንጠውድም የወንድሜን ልጅ ናፍቆኛልና ሂዱና ከእናቱ ጋር አምጡልኝ ብሎ ወታደሮችን ላከ።

ወታደሮቹ መላካቸውንና ንጉሥም ለበጐ ነገር እንዳልፈለገው የቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ እናት በመንፈስ ስለተገለጸላት ሕጻኑን ደበቀችው። ወታደሮቹም በመጡ ጊዜ አብልታ፣ አጠጥታ ስታስተናግዳቸው በመጠጥ ኃይል ነበሩና ልጁን ንጉሡ እንደናፈቁት ይዘው ለመሄድ እንደመጡ ቢነግሯትም ሞተ ብለው እንዳረዷት ያዙኝ ልቀቁኝ እያለች አለቀሰች። አለ ብላ ደህንነቱን ሲነግሯት የመጡ የመሰላት መሆኑን ገልጻ ብትናገር ወታደሮቹ በልተዋል ጠጥተዋልና

አፍረው እርስ በርሳቸው ተመካክረው ንጉሡ ደህንነት እኗቲቱ እንዳታስብ ተልከው የመጡ የሕጻኑን ገልጸው እናቲቱን አረጋግተው ወደ ንጉሡ መሆናቸውን ንጉሡም ይዘው ይመጣሉ ብሎ ይጠብቅ ነበርና ተመለሱ:: ቢላቸው ልጁ እንደሌለ ሁኔታውን ቢያስረዱት ምነው ሞቷል ብሎ ተደስቶ ዝም አለ:: የቀኝ ጠባቂው በመሃል ገብርኤልም፣ የግራ ጠባቂው ቅዱስ ሩፋኤል ቅዱስ ይምርሐነክርንስቶስ የእግዚአብሔር መልአክ ቅዱስ የሆነው ወደ ይምርሐነክርስቶስ እናት ተልኮ በይ ልጅሽን ገብርኤል ከማያገኘው ቦታ አንቺም ከማትስጊበት ቦታ አስቀምጠዋለሁና ምንም ለልጅሽ እንዳታስቢ ብሎ ቅዱስ ገብርኤል ኢየሩሳሌም ወስዶ በስውር አስቀመጠው::

የቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ የኢየሩሳሌም ቆይታ

ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ በኢየሩሳሌም ተምሮ ጽድቅን ተቀብሎ በግብፅና በእሥራኤል እየዞረ እያስተማረ ዕውራንን እያበራ፣ ድውያንን እየፈወሰ ብዙ ታአምራቶችን እያደረገ ቆሞ ጌታ ሙሴን በቃል ያነጋግረው እንደነበር ይምርሐነክርስቶስ እንደ ሙሴ አምላክን ቃል በቃል ሳይሆን በአካለ-ሥጋ እየተገለጸለት ያነጋግረው ነበርና ሚስት እንዲያገባ ጌታ ቢያዘው ጌታ ሆይ ሚስትስ አላገባም እኔ በድንግልና ሕይወት ተወስኜ አንተን እያገለገልኩ መኖር ነውና የምፈልገው እባክህ ፈጣሪዬ ሚስት አላገባም ብሎ ከጌታ ጋር ክርክር ቢገጥም የምታገባት ሴት እንዳንተው ቅድስት ናት ድንግል ናትም የምታገባት ለሥጋዊ ፈቃድ ሳይሆን በሀሣብ እንድትረዳህ ነው ቢለው ይምርሐነክርስቶስ ሴት ከእኔ ጋር ሆና እንዴት በድንግልና እኖራለሁ ቢለው ጌታም በሥጋዊ ፈቃድ እንዳይፈልጋት ቃል ገብቶለት ከካህን ወገን የተወለደችውን ቅድስት ሕዝባ ከተባለችው የነገደ ሌዊ ልጅ አጋባት አግብቶም ቀሰሰ::

አንድ ቀን ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ በቤተክርስቲያን ኪዳን ሲያደርስ ሳለ «... እግዚአብሔር አብ ወሀቤ ብርሃን» ሲል /ብርሃን የሚሰጥ አምላክ ጌታ አቤት አለው:: ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ «ምነው በሰው አገር ረሳኸኝ ፈቃድህ

ቢሆን ወደ ሀገሬ መልሰኝ» አለው:: ጌታም «እናት ሙሽራ ልጅዋን ትረሳለች? እንዴት እረሳለሁ አንተ ለእኔ ሙሽራዬ አይደለህምን? ሲል አሁን ወደ ሀገርህ ሂድ እኔም ከአንተ ጋር ነኝ:: ጠባቂ መልአክ ሩፋኤል ይከተልሃል» ያሳድድህ የነበረውን ንጉሥም ሞቶልሃል:: አለው በዚህ ጊዜ በቤተክርስቲያን ተሰብስቦ ኪዳን ያዳምጥ የነበረውን ሕዝብ ኪዳኑን አቋርጠህ ወግ የምታወጋው ደክሞህ ነውን? አሉት ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስም የሆነውን ሚስጥር ሳይገልጽ እንቅልፍ ጥሎኝ ነው ያቋረጥኩት ብሎ ኪዳኑን ፈጽሞ ወደ ቤቱ ሄደ::

ለቅዱስ ሕዝባ /ለሚስቱ/ የሆነውን ሁሉ ነገራት ፈቃደኛ ከሆንሽ ወደ ሀገሬ አብረን እንሂድ አላት እሷም እሺ ብላው አብረው መጡ:: በመንገድም በሽተኞችን እየፈወሰ ወደ ምድረ ኢትዮጵያ ገባ::

ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ በምድረ ኢትዮጵያ

ቅዱስ ይምርሐክርስቶስ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ በውሎ ክ/ሀገር በላስታ አውራጃ በምትገኝ በአንዲት ቦታ ባረፈ ጊዜ በግዕዝ ዝየሠመርኩ /ይህችን ቦታ ወደድኳት/ ብሎ ድንኳን ተክሎ ተቀመጠ:: በዚህም 15 ዓመት በድንኳን መና ከሰማይ እየወረደለት ቀደሰ:: ይህች ቦታ በግዕዙ ዝየሠመርኩ አባባል ተከትለው ነዋሪዎቹ ሲያዚያ ይሏት ነበርና ዛሬም ድረስ በዚያው ስም ትጠራለች:: አንድ ቀን ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ በዚህች ቦታ ሕዝቡን ግብር አብልቶ ነበርና አዋቂ ነን ባዮች ከቤቱ ገብተው ንጉሥ ሆይ ዛሬ አንድ ምክር ልንመክርህ መጥተናል እንድትሰማን አሉት:: አንተ ከቅዱስ ዳዊት ልበ አምላክ ከተባለው ትበልጣለህን? ብዙ ቁባቶችና ሚስቶች ከነበሩት፣ ከአብርሃም ደጉ ሰው ትበልጣለህን? 3 ሴቶች አግብቶ ከነበረው ከያቆብስ ትበልጣለህን? ብለው ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስን ሌላ ሚስት እንዲያገባ ቢመክሩት ስህተት ነው እናንተ አጋንንቶች አመንዝር ብላችሁ የምትመክሩኝ ብሎ አባረራቸው አፍረው ሄዱ:: ሌሊት ግን ለምን ይህንን ዓይነት ምክር እንደመከሩት በሀሳቡ ሲያሰላስል አደረ:: ምን ፈልገው ይሆን እያለ በቁጣ

ስላበረራቸው መንፈሱ ተጨነቀበት:: በበነጋው ቅዳሴ ሲገባ የተለመደው ሰማያዊ መና ሳይወርድ ቀረ:: ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ዕንባውን እያፈሰሰ ወደ ፈጣሪው አለቀሰ:: ዕንባው አልቆ ደም ደሙ አልቆ ዕዥ እስኪያነባ ድረስ አለቀሰ:: የቆመበት ቦታ በዕንባው ጨቀየ:: ያን ጊዜ ጌታ አእላፍ መላእክትን ይዞ ወረደ:: ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ እያለቀሰ ከፊቱ ቆመ በእናትህ ማህጸን የመረጥኩህ ወዳጄ፣ ልጄ ይምርሐነክርስቶስ ይህን ሁሉ ዕንባ ምድሪቱ እስክትጨቀይ የምታለቅሰው ምን በድየህ ነው ቢለው ጌታዬ ሆይ ምነዋ ማልቀስ ይብዛብኝ ያስለመድከኝን ስታስቀርብኝ ከዚህ ሌላ ምን የምሆነው በደል አለና እንዴት አላለቅስ ከእንግዲህስ ወዲህ ምን መኖርን እመርጣለሁ ሕይወቴስ አንተን አስቀይማ ልትጠቅመኝ ነው? መኖር ለእኔ ከእንግዲህ ትርጉም አለውን? ቢለው ጌታም ያሰብከውን አንተው ታውቃለህና ያስለመድኩህ የቀረብህ ከክፉ ሀሳብህ ነው ቢለው ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ደንግጦ ጌታም ባሰብኩ ምን ቀረህ ቢለው ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስም ታዲያ አሁን ነጥቀኸኝ ይቀራል ወይስ ትሰጠኛለህ? አለው ጌታም በዚህስ ቦታ ክፉ አስበህብታልና በዚህች ቦታ አይሰጥህም ነገር ግን ሥጋህ ከሚቀበርበት እኔ ከፈቀድኩት ቦታ ሣር የማትፈልግ፣ በድንጋይ የተከደነች እስከ ዕለት ምጽአት የማትፈርስ ቤተ መቅደስ በዚያች ቦታ ትሰራለህ:: ትውልድ ሁሉ የአንተን መቅደስ ይሰበሰቡበት ዘንድ፣ የእኔንም ረቂቅነትና ጥበብ ያወቁበት ዘንድ ትሰራለህ አለው:: በዚህም ጊዜ ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ጌታ ሆይ ይህችን ቦታ እወዳታለሁ እና አትናቅብኝ በዚሁ ልቀመጥ ብሎ አምላኩን ተማጸነ:: አንተ የወደድከውን ንቁብህ አይደለም:: ነገር ግን የሚነግሠው አረመኔ ንጉሥ ስላለ ይህችን ቦታ ያቃጥልብሃል እኔ በፈቀድኩት ቦታ ግን የምትሠራት ቤተ መቅደስ እስከ ዕለተ ምጽዓት ምንም አይነካትም አለው:: በዚህም ጊዜ ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ጌታዬ ሆይ ከአንተ ከአባቴ ፈቃድስ እንዳልወጣ ታውቃለህና ማን ይመራኛል? ቢለው ቅዱስ ሩፋኤል መልአኩን አዝዞለት ቅድስት ሕዝባን ይዞ እግዚአብሔር አምላክ ወደ አመለከተው ቦታ ተጓዘ:: በጉዞውም ላይ ድውያንን እየፈወሰ፣ ለምጻምን እያነጻ ለሕዝባን አረጋገጠላት መሬት ሁሉ እየፀለየ በአካባቢው

በደረሰ ጊዜ የሚሄዱበትን አቅጣጫ የተመለከቱት ሰዎች ወደዚያ አልፎ እንዳይሄድ አስጠነቀቁት:: በምትሄዱበት ቦታ አጋንንት ያደረባቸው ይጥላቻዋል አሉት:: ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ እግዚአብሔርን ኃይል አድርጎ ተጓዘ:: እንደተባለውም ውሾቹ በአስፈሪ ሁኔታ እየጮሁ መጡበት ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስም ደነገጠ፣ ፈራ ያን ጊዜ መልአኩ ሩፋኤል በአካል ተገልጾ አትፍራ አትደንግጥ ብሎ አጽናናው ውሾቹም ፊታቸውን አዙረው ከፊት ከፊት እየመሩአቸው ከቤት አስገቡአቸው የባለውቃቢው ሚስት የአየር ጋኔን የያዛት ነበረችና እነሱን ስታይ እያስጓራ ጣላት:: ቦታው ለአጋንንት የሚገበርበት አጋንንት የሠፈሩበት ቦታ ነበርና በቤት ውስጥ የነበሩትንና የጠንቋይ አገልጋዮች ውሾቹ ሳይተናኮሉአቸው ከቤት በመግባታቸው ተገርመው ዛሬ ከጌታችን የበለጠ ጠንቋይ መጥቷል እያሉ እርስ በእርስ ይነጋገሩ ነበር:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ጠንቋዩ ከቤት ሲገባ አስደናቂ ነገር ጠበቀው:: እነዚያ ሰው የማያስቀርቡ ውሾች በቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ፣ ቅድስት ሕዝባና ቅዱስ ሩፋኤል ሆነው ሦስቱ ተቀምጠው እነርሱ እግር ሥር ውሾቹ ተኝተው አገኙአቸው ሚስቱም ከፊት ለፊታቸው በቁመቷ ተዘርግታ ሲያይ ጦር አንስቶ ወደ እነሱ በመወርወር እሱ እራሱ የወረወረው ጦር ተመልሶ ወግቶት ሞተ:: ይህንን የሰሙ የአካባቢው ሰዎች ሊተናኮሉአቸው ፈለጉ ግማሾቹም ለአጋንንት ለጠንቋይ ያደሩ ነበሩና ያንን ያያበት ዐይኑ /አንድ ዐይኑ ማየት የተሳነው/ በመሆኑ ያንኑ እለት በራ እሱም እነዚህ ሰዎች ቄስ ናቸው እያለ ሕዝቡ እንዳይተናኮሉአቸው ማስተባበር ጀመረ:: ቅዱስ ሩፋኤል ከአምላኩ በተሰጠው ስልጣንና ትዕዛዝ አጋንንትን በእሳት ሠንሠለት እስሮ ከቅጽበት እየሩጠ ሳለ ልጁ ከቂርቆስ ጋር ጉጃም ውስጥ ምድረ አቦላ ከምትባል ቦታ ወስደው ቢወረውሯቸው ምድር ተከፍታ ዋጠቻቸው በዚያም አትመው ቀበሩአቸው አጋንንትንም ከቦታው አጠፉ::

የቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ የአሁኑ ቅዱስ ቦታ አሠራር እጳሜ

በአምላክ ፈቃድ ሩፋኤል አጋንንቱን ከአጣራ በኋላ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአካል መጥቶ የቤተ መቅደሱን አሠራር ለቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ገለጸለት ለድልደላ የሚሆኑትን እንጨቶችና ለመሥሪያ የሚያገለግሉትን ቁሳቁሶች ከኢየሩሳሌም በሰረገላ እየመጣህ ሥራ አሠራሩም በባህሩ ላይ /ባሕሩ አጋንንት የሰፈረበት የነበረው/ እንጨቱን ረብርቦ እንጨት ላይ እብነበረድና ድንጋይ፣ ከድንጋይ ላይ ሣር፣ ከሣሩ ላይ ጭቃ፣ ከጭቃው ላይ መሬት ደልድልበት፣ ከአበቃህ በኋላ ፎቁን በድልድይ እንጨት ረብርበህ ሥራ የድንጋይም ጥርብ ከውስጥ የተሠራው ቤተመቅደስ እንዲሸፍን ከጣራ በላይ ዙሪያውን ከልሉት:: ከዚያም ሠርቶ ሲያበቃ ሕዝቡንም አስፍርበት በኋላም ቤተ መቅደሱን ሠራ:: /ኢየሩሳሌም በቀን አምስት ጊዜ እየተመላለሰ በደመና በሰረገላ የሚሰራበትን ቁሳቁስ ያመጣ ነበር::/

የቤተመቅደሱ ወለሉና ጣሪያው በተለያዩ ቀለማት በአላቸው ልሙጥ ሙጫ መሰል ጌጦች በመስቀል ቅርጽ ያሸበረቁ ሲሆን፣ የመስቀሎቹ ቅርጽ የተለያዩና በጣም ውብ የሆኑ ናቸው:: የግድግዳው ዙሪያ አሠራርና የድንጋዩ አጠራረብ በአሁኑ በዘመናችን ለምናያቸው የጥበብ ሥራዎች መሠረት ለመሆናቸው ምስክር ናቸው:: ቤተመቅደሱ በአጠቃላይ ውስጡ በአሁኑ ሰዓት ዘመናዊው ጥበብ ተከትለው የሚሠሩትን አሠራሮች ይመስላሉ:: ግማሽ በግማሽ የውስጡና የውጩ ግድግዳ ውብ በሆኑ የእምነበረድ ድንጋዮች ያሸበረቁ ናቸው ይህም ብቻ ሳይሆን ከምድር ከላይ ፎቅም ታክሎ የተሠራበት ነው ምንም እንኳን የፎቁ አሠራር በጅምር የቀረ ቢሆንም ለአሠራር የተጠቀመበት ጥበብ እጅግ ድንቅ ነው:: እንግዲህ ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ይህን የመሰለውን ቅዱስ ቦታ መስከረም 13 ቀን ጀምሮ ሰኔ 21 ቀን ማለትም በዘጠኝ ወር ከስምንት ቀን በእግዚአብሔር ቸርነት እንደፈጸመው ይነገራል:: በፈጸመበትም ዕለት ሰኔ 21 ቀን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ዕለት ጌታችን

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በአካል ወርዶ ከቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ ጋር እንደረሰእና ቤተመቅደሱን እንደባረከው አባቶች አስረድተውናል:: ምናልባት ሰኔ 21 ቀን ጌታ ራሱ የእናቱን ቤተመቅደስ በአንድ ቀን ሰርቶ አንጾ እንደቀደሰባት ምሳሌ ትሆን ዘንድ ይህንን በዓላቷ እንዲፈጽም የአደረገላት መሆኑን ማን ያውቃል?

ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ በሚቀድስበት ጊዜ ተጨማሪ ቄስም ሆነ ዲያቆን የለውም እንደ ዛሬ እንደምናየው የቤተክርስቲያን ሥርዓት ሳይሆን እንደቀሳውስትም፣ እንደዲያቆናትም ብቻውን ነበር ሥርዓተ ቅዳሴውን የሚያከናውነው ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስም 40 ዓመት በመሉ የቀደሰው ሰማያዊ ሕብስተ መና ከሰማይ እየወረደለት ነው::

በዚያን ጊዜ እዚያው ባሕር ውስጥ ገብቶ የሚጸልይ አንድ መነኩሴ ነበር ቅዱስ ሩፋኤል ሰማያዊውን ህብስተ መና ከሰማይ ይዞ ሲወርድ ተመልክቶ ሊቀበል ከሚጸልይበት ባሕር ውስጥ ወጥቶ ወደ ቅዱስ ሩፋኤል ቢቀርብ ቅዱስ ሩፋኤልም እኔ ለንጉሥ እንጂ ለመነኩሴ እንድሰጥ አልተላኩም ቢለው እንዴት ያለ ንጉሥ ነው ጠጅ እየጠጣ ጮማ እያማረጠ ሰማያዊ መና የሚወርድለት ይህ አምላክ ማን እንደሚያገለግለው አያውቅ ብሎ ወደ ባሕሩ ሊወረወር ሲል የእግዚአብሔር መልአክ ገሰጸው ይህም ንጉሥ ሥጋ ይበላ ጠጅ ይጠጣ እንደሆነ አይተሀልን? ስለ እርሱ ሥራ የምታውቀውስ አለህን? በል ከዛሬ ጀምሮ አስተምር// በኢትዮጵያ ማስተማር ነውና የሚበልጠው ስለባርያዬና ስለወዳጄ ይምርሐነክርስቶስ ያየኸውን መስክርለት በምድረ ግብፅና እስራኤል ለሚገኙ ሕዝቦች ቅድስናውን ንገራቸው፣ አስተምራቸው አንተም በምድር ሳይሆን በሰማያዊት ቦታ ከሱ ጋር ትገናኛለህ በክብርም ከሱ ጋር ትቀመጣለህ አለው መነኩሴውም እንደታዘዘው በግብፅ በእስራኤል ምድር እየዞረ ስለቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ በአምላክ መመረጥ ሰማያዊ መና ከሰማይ እንደሚወርድለት እንደሚመገብ በሚቀድስበት ጊዜ በሰማያዊ መና እንደሚያቆርብ በአስተማረ ጊዜ ሕዝቡ ወዳለበት ቦታ ለመምጣት ይጸልይ ነበር:: ቁጥራቸው 5774

የሆኑ ከምዕመናን፣ ከዲያቆናት፣ ከካህናት፣ ከኤጲስ ቆጶሳት ማዕረግ ያላቸው በኢየሩሳሌም ዝናህን ሰምተን በአንተ ልንባረክ፣ በአንተ ልንቀደስ፣ መጥተናል አሉት:: ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስም እኔ ኃጢአተኛ ነኝ ምዕመናኑን፣ ቀሳውስትና ዲያቆናትን ይህን ሁሉ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳትን ግን እንዴት ብዬ አቆርባለሁ ብሎ አዘነ:: /እራሱን ዝቅ አደረገ/ በዚህን ጊዜ ከኢየሩሳሌም የመጡትም እኛ እዚህ የመጣነው በአንተ ብቃት በአንተ ጸሎት ነው ስንቅ አልያዝን፣ አልተጓዝን አሉት በዚህን ጊዜ ሙሴን ቃል በቃል እንዳነጋገረው ጌታ ለቅዱስ ይምርሐነክርስቶስም ቅርብ ነበርና የመጡት በአንተ ጸሎት ነውና አቁርባቸው ብሎ አዘዘው::

ቅዱስ ሩፋኤል እንዲያቆርባቸው ቅዳሜ ጠዋት ቅዳሴ ገብተው ሲያቆርባቸው ብዛት ነበራቸውና ጀንበር ዘቀዘቀች! እያሱ ዕርስት ሲያካፍል አላልቅለት ቢለው ወደ ጌታው ጸልዮ 3 ቀን ገዝቶ ፀሐይን እንዳስቆማት ይምርሐነክርስቶስም እንዲሁ ፀሐይን ገዝቷት ቆማ ቁርባኑ 3 ቀን ሙሉ ፈጀ እነዚያ ቆራቢዎች ከእንግዲህ ወዲያ እህልም አንበላ፣ ውኃም አንጠጣም ሰማያዊውን የዘላለሙን መብል በልተናልና ካንተ ጋር እንኖራለን ብለው ወደ ሀገራቸውም አልተመለሱም ግማሾቹ ምድራዊውን ሞት ሲሞቱ፣ ግማሾቹም ተሰውረዋል የእነዚህ ቅዱሳን አፅም /የሞቱት/ ዛሬም ሳይፈርስና ሳይበሰብስ በዋሻው ውስጥ በግልጽ ይታያል::

የቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ የዚህ ዓለም ዕረፍት

ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ በእግዚአብሔር ፈቃድ፣ ቸርነት ካህን ሆኖ እየቀደሰ፣ ሰማያዊ መና ከሰማይ እየወረደለት አርባ ዓመት ከነገሠ በኋላ የሠራትን ቤተመቅደስ እንዳትፈርስ፣ እንዳትበሰብስ፣ የበለጠ ለማስጌጥ ፈልጐ በወርቅ እንዲለብጣትም የአምላኩን ፈቃድ ጠየቀ ጌታ ግን የስጠሁህ ከወርቅ ይበልጣልና ይህቺ እስከ ዕለተ ምጽአት አትፈርስም፣ አትበሰብስም እንደ ወርቅ ትሁንልህ በኋላ የሚመጡት ነገሥታት ነን የሚሉ በወርቅ ብትለብጠው ወርቁን ሲፈልጉ ቤተክርስቲያኗን እንዳያፈርሱብህ በወርቅ

አትለብጥ ብሎ ቢከለክለው ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ አምላክ ጥበቡን ቸሮት የሠራትን ቤተመቅደስ የበለጠ ለማክበርና ድንቅ ለማድረግ የአምላኩን ትዕዛዝ እምቢ ብሎ ጓዙን ጠቅልሎ ሠራዊቱንም አስከትሎ ወርቅ ለማምጣት ወደ ምድረ ዓረብ ጉዞ ጀመረ ገና ከኢትዮጵያ ምድር ሳይወጣ በመንገድ ላይ ሳለ ትንሽ ህመም ታመመ:: ወደ ፈጣሪውም እንዲህ ብሎ ጸለየ «ጌታዬ ሆይ ዕለተ ሞቴ መቅረቧን ተረዳሁ ጻዕረ ሞትን እንዳታሳየኝ እለምንሃለሁ እባክህ ትዕዛዝህን ጥሼ ወጥቼአለሁና ይቅር በለኝ ፈቃድህ ሆኖ በሠራሁት ቦታ ልቀበር ብሎ በኃዘን ወደ ፈጣሪው አለቀሰ:: ጌታ ሆይ ለምን መጣሁ? ብሎ አለቀሰ» ጌታችንም ይህች ለፈተና የተፈጠረች ዓለም በቃችህ የክብር ቦታህን ውረስ ሥጋህም እንደለመንከኝ በፈቀድከው በሠራህት ቦታ አሣርፋታለሁ ብሎ ቃል ኪዳን ሰጥቶት በቦታው ለሚመጡት፣ ለሚረግጡት ትውልዶች በመንገር አጽናንቶት ሄደ::

ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስም ተከትሎት የነበረው ሕዝብ ሲያልቅስ ተመልክቶ እሱም ያለቅስ ነበርና ለሕዝቡ እጅግ አዝኖ ወዳጆች ሆይ ስለምን ታለቅሳላችሁ አይዞአችሁ የፈጠረኝ ያውቃል አባቶቼ፣ እናቶቼ፣ ወንደሞቼ፣ እህቴቼ ያለአግባብ የበደልኳችሁ ወገኖቼ ይቅር በሉኝ፣ ያስቀየምኳችሁ ይቅር በሉኝ .... አላቸው እነሱም እኛን ከማብላት: ከማጠጣት፣ በጐ ከመሥራት በቀር ምን የበደልከን ነገር አለና አንተ ብቻ አትሙትብን ለማን ጥለኸን ልትሄድ ሌላ ቢገዛን ጉድ ፈላብን ወዮታ አለብን እያሉ ከፊቱ እየተላቀሱ ቅዱስ ይምርሐነክርስቶስም የሕዝቡ ፍቅር ሳይለየው ጥቅምት 19 ቀን አረፈ:: አእላፍ መላእክት በድኑን /ሥጋውን/ ተሸክመው ከለፋበትና በፈቃደ እግዚአብሔር ካነጸት ቤተ መቅደስ አምጥተው ቀበሩት:: ጌታችን ለቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ የሰጠውን ቃል ኪዳን ከአባቶች በመረዳት ምዕመናን ዛሬም ቦታውን ሲረግጡ መቃብሩን እየዞረ ፍትሐነ ይምርሐነክርስቶስ በማለት ይጸልያሉ::

እግዚአብሔር አምላክ ለቅዱስ ይምርሐነክርስቶስ የሰጠው ቃል ኪዳን

- ገና በእናታቸው ማህፀን ሲፈጠሩ ለገነት ለሲኦል የመረጥኳቸው ፍጥረቶችን ለሲኦል የተመረጡትን ይህችን ቦታ እንዲረግጡ አሳሳስባቸውም ቢያስቡ እንኳን እንዲመጡብህ አላደርግም ነገር ግን መንግስተ ሰማያትን የሚወርሷትን ኃጢያተኞች እልክልሀለሁ በገነት እንዲሆኑና ቦታህን እንዲወርሱ አስረግጥልሃለሁ::

- ወደዚች ቦታ የሚመጣውን ሁሉ ከእናቱ መህፀን እንደተወለደ ህፃን ልጅ አደርገዋለሁ:: ወንዱም በአርባ ቀን እንደተጠመቀ፣ ሴቷም በሰማንያ ቀን እንደተጠመቀች ከኃጢአት ይነፃሉ::

- በዚህች ቦታ መጥቶ የችግሩን የሀሳብ እንዲቀልለት የለመነኝን እንዳለመነኝ እሰጠዋለሁ፣ እኔም በማውቀው ጸሎቱን ሰምቼ የልቦናውን እፈፅምለታለሁ::

- በዚህች ቦታ አምኖ የመጣውን እጣን፣ ጧፍ፣ ዘይት /መብራት/ ወዘተ... የሰጠ ሰባት ሰማይት ነፍሱ እያበራች ትኖራለች::

- ይህችን መቅደስ ትቀድስባት ዘንድ የሰጠሁህን ቦታ ከሌሎች ቅዱሳን ቦታዎች ጋር እያመሳሰለ ክብሩን እንዳያሳንሱብህ አድርጌልሃለሁ::

- በዚህች ስፍራ ላይ አንተን ብሎ የሚመጣውን፣ እንግዳህን ሁሉ ካላሰበበት ቦታ አላሳድርብህም መንገድህንም የረዘመውን እየጠቀለልኩ አሳጥረታለሁ፣ በዚህ ቦታ የሚያድሩትንም እባርክልሃለሁ፣ የአንተንም በረከት ይቀበላሉ ቦታቸውም /የነፍሳቸው/ ማረፊያ ሄሮድስ ካስገደላቸው የቤተልሔም ሕፃናት ጋር ነው::

ወስበሐት ለእግዚአብሐር
ወለወላዲቱ ድንግል

ተፈፀመ

ምዕራፍ ሰባት

ሜሮን ምንድን ነው?

ሜሮን በፀሎት ኃይል በመንፈስ ቅዱስ ሥራ የከበረ ቅዱስ ቅባት ወይም ዘይት ነው::

አገልግሎቱና ጥቅሙ ምንድን ነው?

አማኙ በጥምቀት የሰጠውን ልጅነት ለማጽናት የመንፈስ ቅዱስ ሀብት የሚያሳድር ምሥጢር ከጥምቀት ቀጥሎ የሚሰጥ ሲሆን አንድ ጊዜ ከተቀቡት በኋላ ስለማይደገም በአፈጻጸሙ ምሥጢረ ጥምቀትን ይመስላል:: ይኸውም ቅብዓ ዘይትና ቅብዓ ሜሮን ተብሎ በሁለት ይከፈላል::

ምሥጢረ ሜሮን መቼና በማን ተጀመረ?

መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚያፀናን መንፈስ ቅዱስ ወይም ጰራቅሊጦስ ልዩ ልዩ ተስፋዎችን በተናገረ ጊዜ በእርሱ ተጀመረ::

ምሥጢረ ሜሮን አፈጻጸሙ እንዴት ነው?

በተዋህዶ ቤተክርስቲያናችን ሥርዓት ምሥጢረ ሜሮን አፈፃፀሙ ምሥጢረ ጥምቀት በሚፈፀምበት ጊዜ ሲሆን አጥማቂው ቄስ ተጠማቂውን በውኃው አንፃር ፊቱን ወደምስራቅ እንዲመልስ አዞ ሲመልስ የሰይጣንን መንፈስ አርቅለት፣ የጣኦት አምልኮ ቅሬታን አጥፋለት፣ ቅዱስ መንፈስህንም አሳድርበት የሚል ፀሎት ይፀለይበታል ፀሎቱም ሲያበቃ ፊቱን ወደምዕራብ እንዲመልስ በድጋሚ ያዘዋል ለምን ቢሉ በምዕራብ ጨለማ ይፀናበታል ድንቁርናም በጨለማ ይመሰሳል::

ትንቢተ ኢሳያይስ 9:2 ተጠማቂው ሊጠመቅ ቀርቦ ሳለ ዲያብሎስንና ሠራዊቱን መካዱን በሃይማኖትና በጥምቀት ከሲኦል ግዛት ነፃ መውጣቱን ይናገራል ከዚህ በኋላ ቄሱ የመጀመሪያውን ቅብዓ ዘይት ይቀብላል:: ቅብዓ ዘይት መቀባቱም በድንቁርና ተይዞ በሰይጣን ግዛት ስር ሳለ የወንጌልን ትምህርት ሰምቶ ከዲያብሎስ ለመላቀቁ ፈጣሪውን እግዚአብሔርን እንዳወቀ መንፈስ ቅዱስ እንደረዳው ለማመልከት ነው::

ቅብዓ ዘይት ከተቀባ በኋላ ቄሱ እጁን ይዞ ዳግመኛ በውሃ አንፃር ፊቱን ወደ ምሥራቅ ይመልሰዋል ለምን ብንል ምሥራቅ የብርሃን መገኛ ነው ወንጌልም በምሥራቅ ተመስላለች፣ ከምሥራቅ ብርሃን እንደሚገኝ በወንጌል ሥላሴን ማወቅ ይገኛል ቄሱም ተጠማቂውን እጁን ይዞ ወደ ምሥራቅ መመለሱ እግዚአብሐር በረድኤት አንድነቱንና ሦስትነቱን ወደማወቅ ወደ ሕገ ወንጌል እንደመለሰው ለማስታወስ ነው::

ተጠማቂው ፊቱን ወደምሥራቅ መልሶ ሳለ ቄሱ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ታምናለህ ብሎ ሃይማኖቱን ለማስገለጽ ይጠይቀዋል ተጠማቂውም አዎ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አምናለሁ ሲል ሃይማኖቱን ይመሰክራል ከዚያም በኋላ ቄሱም በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቆ የመጨረሻውን ደረጃ ቅብዓ ሜሮን ይቀባል:: እዚህ ላይ ግን ሕፃኑ ከአንደበቱ ቃል አውጥቶ ይናገራል ማለት አይደለም ያው ያቀፈው ዲያቆን ነው በሕፃኑ ምትክ መልስ የሚሰጠው ለምን ቢሉ በአዳምና በሔዋን ያገኘነውን ሀብተ ጸጋ እንዲሁ ይህም ልጅ በአባቱና በእናቱ ተወራራሽ የማይቋረጥ ሀብተ መንፈስ ቅዱስና የልዑል እግዚአብሔርን የልጅነት ጸጋ ይቀበላል ማለት ነው::

ከተጠመቀም በኋላ ሜሮን መቀባቱም ጥምቀት የክርስቶስ ሞት ምሳሌ ነውና ከክርስቶስ ሞት በኋላ ከመንፈስ ቅዱስ መወለድ እንደተሰጠው ለማሳየት ነው ይህ

በሁለት የተከፈለው ምሥጢረ ሜሮን በአንብሮተ እድ /እድ በመጫን/ ፋንታ መንፈስ ቅዱስን ለማሳደር የተተካ ቅዱስ ቅባት መሆኑን መረዳት፣ ማመን፣ ማወቅ፣ የተዋህዶ ልጆች ግዴታ ነው:: የሐዋ. 6:6-7፣ ሉቃ. 24:50-53

እንግዲህ እነዚህ ሰባቱ /7/ ምሥጢራተ ቤተክርስቲያንን አንብቦ የተረዳና ያወቀ ክርስቲያን በሚገባ ሃይማኖቱን መጠበቅና እግዚአብሔርን በመፍራት የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች እንድንሆንም ጭምር ሲያስገነዝበን፤ ሌላው የአደራ ቃል ደግሞ ፍጹም እምነት እንዲኖረን ማሳሰቡም ነው:: እንግዲህ እኛም ክርስቲያኖች በተቀደሰችው በተዋህዶ ሃይማኖት ፀንተን መገኘትና መልካም ሥራን በመሥራት የርስቱ ወራሾት እንድንሆን የአምላካችን ቅዱስ ፍቃዱ ይሁንልን አሜን! የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን አሜን!

ምዕራፍ ስምንት
ምሥጢረ ቀንዲል

ምሥጢረ ቀንዲል ምንደን ነው?

ምሥጢረ

ምሥጢረ ቀንዲል ከሰባቱ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምሥጢራት አንዱ ነው:: ይህም በልዩ ልዩ ደዌ የታመመ ሰው ነፍሱና ሥጋው ይድን ዘንድ ቅብዓ ዘይት የሚቀቡበት ምሥጢር ነው በቀንዲል ሰው ከሥጋ ደዌ ይድናል የታመመ ሰው ድኖ ፍጹም ጤነኛ ይሆናል ከዚህም ጋር ድውዩ ሰው የነፍስ ደዌ ወይም ኃጢያት ቢኖርበት ተናዞ /ንስሀ ገብቶ/ ኃጢያቱ ይሰረይለታል::

ቀንዲል ለምን ምሥጢር ተባለ?

ቀንዲል ምሥጢር የተባለበት ዋናው ምክንያት የታመመ ሰው ቅብዓ ዘይቱን ከተቀባ በኋላ ፍጹም ጤነኛ ሲሆን እንጂ በሽታው እንዴት እንደሚጠፋ ወይም ኃጢያቱ እንዴት እንደሚሰረይለት በዓይነ ሥጋ የማይታይ በመሆኑ ነው::

የቀንዲልን ሥርዓት የሚፈጽመው ማንው?

የቀንዲል ምሥጢር የሚፈፀመው በመንፈስ ቅዱስ ሥራና በፀሎት ኃይል ነው ይህም በመሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን ከተሰጣቸውና በፀሎት ታምነው ከሚያገለግሉ የቤተክርስቲያን አባቶች /ካህናት/ በስተቀር ሥርዓቱ በሥጋውያን ጠበብት ሊከናወን አይችልም:: /በዲያቆናትም ሊፈፀም አይችልም/

ቀንዲል በአፈፃፀሙ ምሥጢረ ንስሀን ይመስላል ይኸውም በሽተኛው ከደዌ ነፍስ መፈወሱ ነው:: ልዩነት ቢኖር ንስሀ ከነፍስ በሽታ ይፈውስ ዘንድ ለክርስቲያኖች ሁሉ ሲፈፀም ቀንዲል ግን የነፍስንና የሥጋን በሽታ ለማንጻት ለበሽተኞች ብቻ የሚፈጸም ነው::

ስለምሥጢረ ቀንዲል መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

የያዕቆብ መልዕክት ምዕራፍ 5:14-15 እንዲህ ይላል ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተክርስቲያንን ሽማግሌዎች /ካህናት/ ወደሱ ይጥራ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይፀልዩለት የእምነትም ፀሎት ድውዩን ያድናል፣ ጌታም ያስነሳዋል፣ ኃጢያትም ሰርቶ እንደሆነ ይሰረይለታል በማለት ቁልጭ አድርጎ አስቀምጦልናል::

ምሥጢረ ቀንዲል መቼ ተጀመረ?

የቀንዲል ሥርዓት የተጀመረው ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ምድር በሥጋ ይመላለስበት በነበረበት ዘመን ሲሆን ይህንንም ሥርዓት ለሐዋርያት አስተምሮ እነሱም ተጠቅመውበታል ይኸውም ማር.6:13

«ወጥተውም ንስሀ እንዲገቡ ሰበኩ ብዙ አጋንንትንም አወጡ ካለ በኋላ በዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሷቸው» ይላል::

ምሥጢረ ቀንዲል ይደገማልን? የሚል ጥያቄ እንኳ ቢነሳ መልሱን በአጭሩ እነሆ! ከሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን አራቱ ማለትም ምሥጢረ ጥምቀት፣ ምሥጢረ ክህነት፣ ምሥጢረ ተክሊል፣ ምሥጢረ ሜሮን የማይደገሙ ሲሆን ሦስቱን /3/ ግን ማለትም ምሥጢረ ንስሀ፣ ምሥጢረ ቁርባንና ምሥጢረ ቀንዲል እንደየአስፈላጊነታቸው ተደጋግመው የሚፈፀሙ ናቸው::

ከሠማዕታት አበው ውስጥ በዋናነት ከሚታወቁት ሦስቱን እነሆ

- ሰማዕቱ ሊቀ ዲያቆን ቅዱስ እስጢፋኖስ አባቱ «ስምዖን» እናቱ «ሐና» ይባላሉ:: የስሙም ትርጉም አክሊል

ይባላል:: ያረፈው ጥር 1 ቀን ነው ሀገሩም «ሐኖስ» በተባለ ሥፍራ በኢየሩሳሌም አካባቢ ነው::

- የቅዱስ ጊዮርጊስ አባት «ዘሮንቶስ» እናቱ «ቴዎብስታ» ሀገሩም «ልዳ» ነው በሰማዕትነት ያረፈው በ20 ዓመቱ ነው ሰማዕቱ ቅዱስ ጊዮርጊስን ያስገደለው ንጉሥ ዱድያኖስ በመባል ይታወቃል::

- የቅዱስ መርቆርዮስ አባት «ኖኅ» እናቱ «ታቦት» ይባላሉ:: ያረፈው ህዳር 25 ነው ሀገሩም «ሮም» ሲሆን በ29 ዓመቱ በሰማዕትነት አርፏል ሰማዕቱ ቅዱስ መርቆርዮስን ያስገደለው ንጉሥ ዳኪሮስ ይባላል:: የሰማዕቱ ቅዱስ መርቆርዮስን ቤተክርስቲያን ያገለግሉ የነበሩት /ባስልዮስና ጎርጎርዮስ/ ነበሩ::

ከቅዱሳን አበው ውስጥ በዋናነት ከሚታወቁት ሦስቱን እነሆ

- ጻድቁ አቡነ አረጋዊ ሀገራቸው ሮም ሲሆን አባታቸው «ይስሐቅ» እናታቸው «እድና» በመባል ይታወቃሉ በዘንዶ ተራራውን የወጡት ጥቅምት 14 ቀን ነው፤ ተሰወሩ እንጂ አልሞቱም::

- ጻድቁ አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ አባታቸው «ስምዖን» እናታቸው «አቅሌሲያ? ይባላል ሀገራቸው ግብፃዊ ሲሆኑ ያረፉትም መጋቢት 5 ቀን ነው::

- ጻደቁ አቡነ ተክለሃይማኖት አባታቸው «ፀጋዘአብ» እናታቸው «እግዚሃርያ» ይባላሉ ያረፉትም ነሐሴ 24 ቀን ነው፤ የትውልድ ቦታቸውም ኢቲሳ ገዳም ሲሆን ሀገራቸው ኢትዮጵያ ነው::

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!

ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይሁን፤ አሜን::

ለማጽሐፉ ድጋፍ የሆኑን መጻሕፍት

- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ታሪክ፣ በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀጳጳስ የተዘጋጀ፤ በ1974 ዓ.ምና «የቤተክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ» በ1978 ዓ.ም፣

- ከመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ሰንበት ተማሪዎች ደብተር በማውጣጣት «ምንጭ» በመንፈሳዊ ወንድማችን ጥላሁን ዋቅጅራ በስብከት መልክ ካስተማረው፣

- በአዲስ አበባ አድበራት ከሚሰጡት የቀዳማይ፣ የካልዓይ፣ የሣልሳይ ኮርስ በመማርም /በመሰልጠንም/ ጭምርና ከተለያዩ ተማሪዎች ደብተር በማገናዘብ፣

- መጽሐፍ ቅዱስ በአማርኛ ቋንቋ ከብሉይ ኪዳንና ከሐዲስ ኪዳን በማቀናጅት 15ቱን የብሉይ ኪዳን 2ኛ የቀኖና መጻሕፍት በአጠቃላይ /ከ80 አህዱ መጽሐፍ ቅዱስ/ ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራእይ ባሉት ላይ ተመርኩዘን ነው::

- ዮኀተ ሃይማኖት በብርሃኑ ጉበና የተዘጋጀ፣ መስከረም 1986 ዓ.ም አዲስ አበባ

- ሐዲስ ኪዳን /በግእዝና በአማርኛ/ በሊቃውንት ጉባ. ታርሞ የተዘጋጀ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት አ. አበባ 1975 ዓ.ም

- ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ /ሊቀ መዘምራን/ መርኆ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ኮከበጽብሐ ዘመንበረ ሐዋርያት ፍ.ሃ ማተሚያ ቤት

- ስለሙሴ ጸሊም ዋቤ መጻሕፍት:-
  ሰኔ 24 ስንክሳር
  ፊሊክ. 40:29
  ፊሊክ. 41:29 «ተስእሎ»

እርማት

ከገጽ 1 ጀምሮ ያለውን የመቅድም እና የመግቢያ «መርጎ ለኢየሩሳሌም» የሚለውን ርዕስ በሐመሮኃ ፊደል ተክታችሁ አንብቡት «ኀ» በዚህፊንታ «ሕ» ን ተኩት፤
መታሰቢያነቷ ገጽ 8 «ተራዳዩን» በሚለው «ተራዳኢ»
መግለጫ ገጽ 11 «በዚች መጻሕፍት» የሚለውን «በዚች መጽሐፍ»
መግቢያ ገጽ 16 «ፅውርተ» የሚለውን - «ዕውርተ»
ገጽ 17 በድንግል ማህደር «የሚለውን» «በድንግል ማኅጸን» በሚለው ይተካ፤
ገጽ 29 «ዐጋን ያገኘሽ» በሚለው ፈንታ «ጸጋን ያገኘሽ»
ገጽ 39 «ሉቃ.83:5-56» በሚለው ፈንታ «ሉቃ. 8:5-56» ይተካ

ስለምሥጢረ ተክሊል ጥያቄ ደግሞ ገጽ 71 ሙሉውን ጥያቄ እነሆ፤
በቤተክርስቲያናችን ሥርዓትና ደንብ መሠረት የወንድና የሴት በር መግቢያ ለብቻ መሆን አለበት ተብሎ ተወስኗል:: ይህ ሆኖ ሳለ አብዛኛውን ጊዜ ተክሊል ፈጻሚዎች በወንድ በር መግቢያ በኩል ሲወጡ ይታያልና ይህ ሕግን መጣስ አይሆንም?

ገጽ 59 «ኤጲሲምስ /ሲድራኮስ/ «በሚለው» ኤጴሲምስ /ሲድራኮስ/»
ገጽ 69 « የቤተክርስቲያን /ካህናት/» በሚለው ፈንታ « የቤተክርስቲያን አገልጋይ ካህናት « ተብሎ ይነበብ፤
ገጽ - 78 « የሚስጢረ » የሚለውን /የምሥጢረ » ይተካል::
ገጽ - 81 « ቁጥር 3 » ጠንጠውድም » በሚለው ፈንታ « ጠጠውድም» ይተካ
ገጽ - 86 « መሬት» በሚለው ፈንታ « / በመሬቱ/ ተብሎ ይተካል::
ገጽ - 88 ርዕስ « እጻሜ» «ፍጻሜ»
ገጽ - 89 «እንደረሰእና» የሚለውን «እንደደረሰና»
ገጽ - 92 «የለመነኝ እንዳለመነኝ» በሚለው ፈንታ «የለመነኝን እንደለመነኝ» ይተ...
ገጽ - 99 «አቅሌሲያ? ይባላል» የሚለውን «አቅሌሲያ» «ይባላሉ» ተብሎ ይነበብ
ገጽ - 99 «ዳኪሮስ» በማለት ፈንታ «ዳኬምስ»
ገጽ - 99 «እግዚሃርያ» በሚለው «እግዚአሃረያ» ይባል